በፌደራል የጥብቅና ስራ የግብር አስተዳደር ስርዐት የህግና አተገባበር ጉድለቶችና መፍትሄዎች

(በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር፤ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ፌደራል ጠበቆች ማህበር አማካኝነት የተሰራ ጥናት)

የጥናት ቡድኑ አባላት፤

1. አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው (የኢትዮጵያ ፌደራል ጠበቆች ማህበር ተ/ፕሬዚደንትና የጥናቱ አስተባባሪ/ሰብሳቢ)
2. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር (ም/ሰብሳቢ ከገንዘብ ሚኒስቴር)
3. ወ/ሮ ሀመልማል በቀለ (ከፍትህ ሚኒስቴር ዐቃቤ ህግ እና ጸሀፊ)
4. አቶ በላይ ከተማ (አባል ከኢትዮጵያ ፌ/ጠ/ማህበር)
5. አቶ ዳዊት ኪዳኔ " "
6. ገብርኤላ አብርሃም " "
7. ዮናስ ግርማ(ዶ/ር) " "
8. አቶ ሀይለገብርኤል አያሌው (ከፍትህ ሚ/ር ዐቃቤ ህግ እና አባል)

ታህሳስ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ማውጫ

ምእራፍ አንድ 3

1.1. መግቢያ 3
1.2. የጥናቱ ዓላማ 4
1.3. የጥናቱ ችግር መግለጫ 4
1.4. የጥናቱ ወሰን 6
1.5. የጥናቱ ስልት (RESEARCH METHODLOGY) 6
1.6. የናሙና አወሳሰድ ዘዴ እና የመረጃ ምንጮች 6
1.6.1. የህጎች እና ጽሁፎች ዳሰሳ 7
1.6.2. ቃለ መጠይቅ 7
1.6.3. መጠይቅ 7
1.6.4. የትኩረት ቡድን ውይይት 8
1.6.5. የክልሎችና የሌሎች ሀገራት ልምድ 8
1.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ 9

ምእራፍ ሁለት 10

2. *የታክስ ህጎች ማዕቀፍ ከጥብቅና አገልግሎት አንጻር* 10

2.1. መግቢያ 10
2.2. ግብር የመሰብሰብ ስልጣን 10
2.3. ከጠበቆች እና ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች የሚሰበሰብ ግብር 12
2.3.1. የገቢ ግብር 12
2.3.2. ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ 20
2.4. የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶችን የታክስ አከፋፈል በተመለከተ የውጭ አገራት ልምዶች 25
2.4.1. ናይጄሪያ፤ 25
2.4.2. ኬንያ፤ 27
2.4.4. ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፤ 29
2.4.5. ዮናይትድ ኪንግደም፤ አይርላንድ እና ቱርክ፤ 30
2.4.6. የጥብቅና ድርጅቶች እና የሽሪች የገቢ ግብርን በተመለከተ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ 32
2.5. የክልሎች ልምድ 34
2.5.1. አስተዳደራዊ ክፍያ 35
2.5.2. የግብር ክፍያ 36
2.5.3. የጥብቅና ገቢ ግብር አመዳደብ 36
2.5.4. ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ 37
2.5.5. ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ አከፋፈል 38

2.5.6. ስለ ወጪ አያያዝ 39

ምእራፍ ሶስት 41

3. የጥናቱ ግኝት እና ትንተና 41

3.1. የጥብቅና አገልግሎት በገቢ ግብር አዋጅ ያለው አመዳደብ 41
3.2. የሂሳብ መዝገብ መያዝ 47
3.3. ወጪ አያያዝ እና የጥብቅና አገልግሎት 58
3.4. ስለ ደረሰኝ ምንነት፣ ዓይነትና አጠቃቀም 63
3.5. የጥብቅና ስራ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች 69
3.6. በተጨማሪ ሌላ ስራ የተሰማሩ ጠበቆች 71
3.7. በህግ ድርጅቶች የግብር አከፋፈል ስርዓት 73

ምእራፍ-4 75

4. መደምደሚያ እና መጠቁም፤ 75

4.1. መደምደሚያ 75
4.2. መጠቁም /RECOMMENDATIONS/ 78

ምእራፍ አንድ

1.1. መግቢያ

የፌደራል ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች በሥራ ላይ ያለውን ግብር አከፋፈል በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ለበርካታ አመታት ሲያነሱ መቆየታቸው የሚታወቅ ነው። የቅሬታዎቹ ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም መነሻ የሚደርጉት ግን የጥብቅና ሥራን ልዩ ባህሪ ከግምት ካለማስገባት ጋር የተያዙ የግብር አከፋፈል ትግበራ እንደሆነ በጠበቆች በኩል ይነሳል። እነዚህም የአሰራር ወጥነትና የፍትሃዊነት ችግሮች፣ የተለዩ የአሰራር መመሪያዎች/ህጎች አለመኖርና ያሉትንም ያለማክበር/ያለመፈጸም፤ ከዚሁ ጋር ተያይዘው ያሉ ከሒሳብ መዝገብ እና ከወጭ አያያዝ ጋር የተገናኙ ችግሮች፤ የደረሰኝ አጠቃቀምና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሆኑ ይነሳል። በሌላ በኩል በግብር ሰብሳቢዉ ተቋም ዘንድ አንዳንድ ጠበቆች የሚጠበቅባቸዉን አመታዊ የግብር ግዴታ በአግባቡ እየተወጡ እንዳልሆነ ይነሳል።

በእነዚህ ሁለት አካላት ለረጅም ጊዜ ሲነሱ የቆዩት ችግሮች መፍትሄ ሳይሰጣቸዉ ከአመት አመት ሲነሱ ቆይተዋል። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በጥናት በመለየት ዘላቂ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ በአጠቃላይ በጥብቅና አገልግሎት የግብር አስተዳደር ስርዓት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ የሚያመላክት ጥናት ማከናወን አስፈላጊ ሆኗል። በዚህም ከፍትህ ሚኒስቴር፤ ከገንዘብ ሚኒስቴር፤ እና ከኢትዮጵያ ፌደራል ጠበቆች ማህበር የተውጣጡ ባለሙያዎች የተዋቀረ ቡድን ተቋቁሞ ይህን ጥናት አከናዉኗል።

የጥናቱን አደረጃጀት በተመለከተ የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱን አላማ፤ የችግር መግለጫ፤ የጥናቱ ወሰን እና ዘዴን ያካትታል። ሁለተኛው ክፍል በዋናነት ከፌደራል የታክስ ህግ ማእቀፎች በተለይም ከቀጥታ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች የተመለከተ ዳሰሳ የተደረገ ሲሆን እንዲሁም የውጭ ሀገራት የህግ አገልግሎት የግብር አስተዳር ህግና አተገባበሩ ጋር በተያያዘ እና በተመረጡ ክልሎች ያሉ የግብር አከፋፋልን የተመለከቱ ልምዶች ተተንትነው ተዳሰዋል። በጥናቱ ሶስተኛው ክፍል በጥናቱ የተገኙ ግኝቶች ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር ተዛምደው የተተነተኑበት ክፍል ሲሆን የጥናቱ የመጨረሻው ክፍል ደግሞ የጥናቱን መደምደሚያና የመፍትሔ ታሳቦችን የሚያመላክት ነዉ።

1.2. የጥናቱ ዓላማ

በዋናነት የዚህ ጥናት ዓላማ ጠበቆች በየጊዜዉ እያጋጠሟቸዉ ላለዉ የግብር አከፋፈል ችግር መነሻ ምክንያቶችን በስራ ላይ ካሉ ህጎች እና በተግባር ካለዉ አሰራር አንጻር በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ ማመለካት ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉት ሶስት ንኡስ አላማዎች ይኖሩታል።

- ጠበቆች በግብር እና ታክስ መክፈያ ወቅት እያጋጠማቸዉ ላለዉ ወጥነትና ተገማችነት አለመኖር ችግር እንዲሁም ፍትሀዊ ያልሆነ የግብር አከፋፈል ችግር መነሻ ምክንያቶችን መለየት እና ወጥ፤ ተገማችና ፍትሃዊ የግብር አሰባሰብ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ አማራጭ መፍትሄዎችን ማቅረብ።
- በስራ ላይ ያሉ የግብር እና ታክስ ህግ ማእቀፎች ከጥብቅና አገልግሎት የሚገኝን ገቢ በምን አይነት መንገዶች እያስተናገዱ እንደሚገኙ ለመዳሰስ እና የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ።
- የጠበቆች ግብር አከፋፈል ስርዓትን ከጥብቅና የስራ ባህሪ አንጻር በማገናዘብ ከሂሳብ መዝገብ፤ የወጪ አያያዝ፤ የእርጅና ቅናሽ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎችን በመፈተሽ እና ተግዳሮቶችን በመለየት ለሚመለከተዉ የመንግስት አካል ምክረ ሃሳብ ማቅረብ።
- መንግስት ከጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ግልጽ፤ ፍትሃዊና ለዘርፉ ውጤታማ የታክስ አስተዳደር መስተንግዶ በማበጀትና የተለየ መመሪያ በመዘጋጀት የሚገኘውን ገቢ በተጨባጭ እንዲጨምር ማስቻል ነው።

1.3. የጥናቱ ችግር መግለጫ

- በሀገራችን የጥብቅና አገልገሎት የግብር መሰረቱ፤ ምጣኔዉ እና በአጠቃላይ የአስተዳደር ሂደቱ ላይ የወጥነት፣ የፍትሀዊነት እና የዉስብስብነት ችግሮች እንዳለ በጠበቆች ዘንድ በተደጋጋሚ እንዲሁም በግብር ሰብሳቢዉ ተቋም አልፎ አልፎ ይነሳል። እነዚህ ችግሮች ጥናቱን ለማካሄድ መነሻ ነጥቦች ሲሆኑ ዘርዘር ተደርገዉ ሲታዩ፡-
    - አብዛኛዉ የፌደራል የጥብቅና ፍቃድ ያላቸዉ ጠበቆች ግብር የሚከፍሉት በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ስር ባሉ ቅርንጫፍ የገቢ ጽ/ቤቶች ሲሆን በእነዚህ ጽ/ቤቶች የሚስተናገዱ

ጠበቆች እንደየ ጽ/ቤቱ በተለያ መንገድ ወይም ወጥነት በሌለዉ መንገድ እየተስተናገዱ መሆኑ፤ ለምሳሌ በአንዳንድ ክፍለ ከተማ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ እና በሚያቀርቡት ሂሳብ መዝገብ መሰረት ግብር እንዲከፍሉ የሚያስገድዱ ሲሆን ሌሎች ክፍለ ከተሞች ደግሞ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ እንደማያስገድዱ እና በቁርጥ ግብር እንደሚያስከፍሉ በጠበቆች በኩል ይነሳል፤

- ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የግብር ሰብሳው ተቋም ቢያስገድድም በሂሳብ መዝገብ ላይ ጠበቆች በወጪነት የሚያቀርቧቸዉ ወጪዎች ገቢዎች ቢሮ በወጪነት እንደማይዝላቸዉ ያነሳሉ። ይኸዉም ጠበቆች የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጡ የመኪና ነዳጅ፣ የስልክ፣ የቤት ኪራይ እና የመሳመሉ ወጪዎችን እንደሚያወጡ ነገር ግን የመኪና እና የስልክ ወጪዎችን መኪናዉ ኮድ ሶስት ካልሆነ ስልኩም በድርጅት ያልተመዘገበ ከሆነ በወጪነት እንደማይያዝላቸዉ ይህም የፍትሀዊነት ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን ያነሳሉ። በሌላ በኩል በገቢዎች ቢሮ በኩል ጠበቆች ከሌሎች ግብር ከፋዮች ጋር ሲነጻጸሩ ከሚያገኙት ገቢ ተመጣጣኝ የሆነ ግብር እየከፈሉ እንዳልሆነ ይነሳል። በጠበቆች በኩል የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ወጪ አለመያዝ ብቻ ሳይሆን የጥብቅና ስራ ባህሪያት እና ከሙያው ጋር የተያያዙ ግዴታዎች የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታነት እና ወጪ አያያዝን አስቸጋሪ ያደርገዋል የሚል ሀሳብ ያነሳሉ።

- ጠበቆች በወጪነት የሚያነሷቸዉ እንደ የመኪና ነዳጅ ወጪ እና የስልክ ወጪዎችን ለመያዝ የንግድ ፍቃድ ማዉጣትን የሚፈልጉ ተግባራት መሆናቸዉ እና ሌሎች ጠበቆች የሚያወጧቸዉ ወጪዎች ከግል ወጪዎች ለይቶ ለመያዝ ስለሚስቸግር የጠበቆች ወጪ አያዝን ዉስብስብ አድርጎታል፤

የሚሉ ሲሆን እነዚህ እና ሌሎች መሰል በጠበቆች እና በግብር ሰብሳቢዉ ተቋም የሚነሱ ችግሮችን በእርግጥም ችግሮቹ መኖራቸዉን ማረጋገጥ፤ የችግሮቹ ምንጭ ምን እንደሆነ መለየት እና በመፍትሄነት የሚያገለግሉ አማራጮችን ማመላከት በዚህ ጥናት ያስፈልጋል።

1.4. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን የፌደራል የጥብቅና ፍቃድ ያላቸዉ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች አመታዊ የግብር ግዴታቸዉን በሚወጡበት ወቅት የሚስተዋሉ የአሰራር ችግሮችን እና በግብር ህጎች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ጠበቆች በተሻለ ሁኔታ የግብር ግዴታቸዉን እንዲወጡ፤ መንግስትም የተሻለ ግብር የሚሰበስብበትን የተሻሉ አማራጮችን ማመላከት ድረስ የተወሰነ ነው።

1.5. የጥናቱ ስልት (Research Methodlogy)

ይህ ጥናት ጥምር የጥናት ዘዴን ይከተላል። ይህም አይነታዊ (qualitative) እና መጠናዊ (quantitative) የጥናት ዘዴዎች እንደየሁኔታው ተግባራዊ ተደርገዋል። የጠበቆች የግብር አከፋፈል ጋር በተያየዘ በተግባር እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን እና የህግ ክፍተቶች የተተነተኑት አይነታዊ ዘዴን በመከተል ሲሆን የግብር ህጎች በተጨማሪ ከጠበቆች እና ከታክስ ተቋማት ሃላፊዎች በመጠይቅ እና በቃለ-መጠይቅ የተገኙ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ጥቅም ላይ ዉለዋል።

1.6. የናሙና አወሳሰድ ዘዴ እና የመረጃ ምንጮች

በጥናቱ ውስጥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተካተቱት በፌደራል ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ኖሯቸዉ በተግባር የጥብቅና አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች፣ በአዲስ አበባ ከተማ የግብር ተቋማት ሀላፊዎች እና የክልል ጠበቆች ማህበሮች ናቸዉ። አብዛኞቹ የፌደራል ጠበቆች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን አንዳንድ ተሳታፊዎችን በተለያዩ ጊዜያት መጠይቆችን በአካል እንዲሞሉ በማድረግ እና አብዛኞቹ ደግሞ በኦንላይን መጠይቆችን በመሙላት በአጭር ጊዜ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል። በመሰረቱ የጥናቱ አላማ በዋናነት የፌደራል ጠበቆች በግብር አከፋፈል ላይ እያገጠሟቸዉ ያሉትን ችግሮች በመለየት እና በጥብቅና አገልግሎት ላይ የሚጣል ግብር የህግ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማመላከት የፖሊሲ፣ የህግ ወይም የአሰራር ማሻሻያዎች ግብአት መስጠት እንደመሆኑ መጠን የፌደራል ጠበቆች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናቱን ማካሄድ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል። ለጥናቱ መጠይቅ እና የትኩረት ቡድን ውይይት ተሳታፊነት የተመረጡት ጠበቆችም በግብታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ(Random Sampling Technique) ነዉ።

1.6.1. የህጎች እና ድሁፎች ዳሰሳ

የጥብቅና አገልግሎትን የተመለከቱ ሕጎች እና የግብር ህጎች ተዳሰዋል። በዚህም የፌዴራል የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1249/2014፣ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008፣ የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008፣ የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2010፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና ማሻሻያዎቹ አዋጅ ቁጥር 609/2001 እና 1157/2011፣ ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ 308/1995 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 እና እነዚህን ሕጎች ለማስፈጸም በገንዘብ ሚኒስቴርና በገቢዎች ሚኒስቴር የወጡ መመሪያዎች እንደ አግባብነታቸው በጥብቅና አገልግሎት እና ጠበቆች መክፈል ስለሚገባቸዉ ግብር እንዲሁም አሰራሩን በሚመለከት የሚኖራቸው ተፈጻሚነትና ክፈተቶቻቸው ተዳሰዋል። ከጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥና ግብር አከፋፈል በተያያዘ የተሰሩ ጥናቶችና በአስፈጻሚ ተቋማት የተጻፉ ማብራሪያዎች ለዚህ ጥናት እንደሁለተኛ የመረጃ ምንጭ ጥቅም ላይ ውለዋል።

1.6.2. ቃለ መጠይቅ

ከጥብቅና አገልግሎት እና የግብር አከፋፈል ጋር በተያያዘ ያለውን አተገባበር በተመለከተ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፤እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ጠበቆች ማህበር ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጎ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

1.6.3. መጠይቅ

የፌደራል የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች እንዲሞሉት በተዘጋጀ መጠይቅ መሰረት መረጃዎች ተሰብስበዋል። በመጠይቁ የሚሳተፉ ጠበቆችን በግብታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (random sampling) ተመርጠዉ ዳሳሳዊ መጠይቅ (survey questionaries) ተሟልቷል አይነታዊ (qualitative) እና መጠናዊ(Quantitative) መርጃዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በድብልቅ አይነታዊ እና መጠናዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ ትንተና ተደርጎባቸዋል። ስለሆነም ምን ያክል ናሙና መሰብሰብ እንዳለበት ለመወሰን ብዙ ጊዜ ለሰርቬይ ጥናት ተግባር ላይ የሚዉለዉ የናሙና መጠን መለያ የሆነዉን የየማን ፎርሙላ ተጠቅመን በ10 በመቶ ብቻ የስህተት አጋጣሚ ቢኖር የሚለውን ወስደን ከ3000 አጠቃላይ ጠበቆች 97 ለሚሆኑ ጠበቆች መጠይቁን እንዲሞሉ በትነናል። በአጠቃላይ የተሳትፎ ሽፋን ሲታይ ጥናቱን ለማካሄድ ከተመረጡት 97 ናሙናዎች ዉስጥ በተሰራጨዉ መጠይቅ መሰረት 87 ጠበቆች የተሟላ መረጃ

በመሰብሰብ ከፍተኛ የተሳትፎ ሽፋን (89.69%) ማግኘት ተችሏል። መጠይቆች ከሞሉት ሰዎች ዉስጥ ከአንድ አመት በታች አገልግሎት የሰጡ ጠበቆች ብዛት 5፣ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት አገልግሎት የሰጡ ጠበቆች ብዛት 17፣ ከአምስት አመት በላይ አገልግሎት የሰጡ ጠበቆች ብዛት 61 የተሳተፉ በመሆኑ ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ልምድ ያላቸዉ ጠበቆች አጠቃላይ 90% የሚሆኑት ተሳታፊ ጠበቆች በቂ ልምድ ያላቸዉ ናቸዉ።

1.6.4. የትኩረት ቡድን ውይይት

ለትኩረት ቡድን ውይይት ከተመረጡ የፌዴራል ጠበቆች የግብር አከፋፈል ሁኔታን፣ የግብር ምጣኔ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ እይታን ለማግኘት ተከናወነዋል። በዚህ ዘዴ በተለይም ጠበቆች በታክስ አከፋፈል ዙሪያ እያጋጠሟቸዉ የሉትን ችግሮች በስፋት ተዳሰዋል። የትኩረት ቡድኑ ተሳታፊዎች ብዛት 6 (ስድስት) ሲሆን የፆታ ስብጥር 33.3 (ሰላሳ ሶስት ነጥብ ሶስት) በመቶ ሴቶች 66.6 (ስልሳ ስድስት ነጥብ ስድስት) በመቶ ወንዶች ነው። የተሳታፊዎች የስራ ዘመን ከ6 (ስድስት) አመት እስከ 28 (ሀያ ስምንት) አመት በመሆናቸዉ 100% ሁሉም የትኩረት ቡድኑ ተሳታፊዎች በሙያዉ በቂ ልምድ ያላቸዉ ናቸዉ ለማለት ያስችላል። ተሳታፊዎች ከንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ኮልፌ ቀራንዮ፣ ቦሌ፣ጉለሌ፣ቂርቆስ፣ ልደታ እና የካ ክፍለ-ከተማ የተዉጣጡ በመሆናቸዉ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተሞች እንዲካተቱ ተደርጓል።

1.6.5. የክልሎችና የሌሎች ሀገራት ልምድ

የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት በሚገኝ ገቢ ላይ ስለሚጣል የግብር ዓይነትና አሰባሰብ ጋር በተያያዘ የኦሮሚያና የአማራ ክልል አሰራር ለመዳሰስ የተሞከረ ቢሆንም ከአማራ ክልል መረጃ ለማግኘት የተደረገዉ ጥረት ስላልተሳካ በኦሮሚያ ክልል የክልሉን ገቢዎች ቢሮ እና ፍትህ ቢሮ ሀላፊዎችን ቃለመጠይቅ በማድረግ በክልሉ ያሉትን ህጎች እና አሰራርን በተመለከተ የተገኘዉን ልምድ በጥናቱ ተካቷል። እንዲሁም በታክስ ሕግ የዳበረ ሕግና አሰራር ያላቸው እና ከሀገራችን ጋር ተቀራራቢ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አከባቢያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት የተመረጡ ሀገራት ልምድ በንጽጽር እንዲቀርብ ተደርጓል። ለንጽጽር የቀረቡት ሀገሮች የተመረጡት ባላቸዉ የህግ ስርዓት እድገት፣ የጥብቅና እና ህግ አገልግሎት ረጅም ጊዜ ልምድ(ታሪክ)፣ በህዝብ ብዛት ወይም ኢኮኖሚ ከኢትዮጵያ ጋር ባላቸዉ ቅርበት ግምት ዉስጥ በማስገባት ነዉ።

1.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከጠበቆች በመጠይቅ (survey questionaries) የተሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ ዓላማ አኳያ በመጠናዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ ተተንትነዉ በፓይ ቻርት እንዲቀመጡ ተደርጓል። መጠናዊ መረጃን መሰብሰብ ያስፈለገዉ ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ችግሮችን ምን ያህል ጠበቆች እንደሚጋሩት ለማወቅ ወይም ችግሩ የምን ያክል ጠበቆች/የጥብቅና ድርጅቶች ችግር እንደሆነ ለመረዳት በማሰብ ነዉ። በተጨማሪም መረጃዎቹ በመጠይቁ፣ በቃለመጠይቁ እና በትኩረት ቡድን ዉይይቱ ከቀረቡት ዋና ዋና ጥያቄዎች አንጻር በተቀራራቢ እና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር እንዲደራጁ ተደርገዉ ጥናቱ ትኩረት ካደረገባቸዉ አላማዎች ጋር በማዋሃድ እንዲተነተኑ ተደርጓል።

ምእራፍ ሁለት

2. *የታክስ ህጎች ማዕቀፍ ከጥብቅና አገልግሎት አንጻር*

2.1. መግቢያ

በፌዴራል ደረጃ ባለው የግብር ህግ ማዕቀፍ ጠበቆችንና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶችን የሚመለከቱት የኢ.ፌ.ዴ. ሪ ህገመንግስት፣ የፌዴራል የገቢ ግብር ህጎች፣ የፌዴራል ተርን ኦቨር ታክስ ህጎች፣ የፌዴራል የተጨማሪ እሴት ታክስ ህጎች እና የፌዴራል የግብር አስተዳደር አዋጅ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249-2013 እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ 57/1992 በጥብቅና ስራ አሰራር ላይ ተጨማሪ የህግ ማዕቀፍ ይሰጣሉ።

ሆኖም ከላይ የተገለፁት የግብር ህግ ማዕቀፎች በስራ ዘርፍ የተመሰረተ የግብር አከፋፈል ስርዓትን የዘረጉ ባለመሆናቸው ጠበቆችንና የጥምብቅና ድርጅቶችን በብቸኝነት የሚመለከት ግልፅ አሰራር የለም። በዚህ መሰረት በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የፌዴራል የግብር ህግ ማዕቀፍ እንደሚከተለው መዳሰስ ይቻላል።

ለመንግስት ግብር መክፈል ማንኛውም ገቢ ከሚያገኝ ሰው የሚጠበቅ ግዴታ ሲሆን መሰረታዊ መርሆቹም ከህገ-መንግስቱ እና ከመደበኛ ህጎች የሚመነጩ ናቸው። የአለም ልምድ እንደሚያሳየው የሚወሰኑ የግብር አይነቶችና መጠናቸው ከምንጩ ጋር የተያያዙ መሆን ያለባቸው፤ በአግባቡ ተጠንተው መወሰን የሚገባቸው ስለመሆናቸው መገንዘብ የሚቻል ነው። በ1987 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት የተካተቱ መሰረታዊ መርሆችም ከዚሁ ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

2.2. ግብር የመሰብሰብ ስልጣን

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አዋጅ ቁ. 1/1987[1] የግብር ሥልጣን ክፍፍል ዘርዘር ባለ መልኩ ከአንቀጽ 95-100 ተደንግጓል። ሕገ መንግሥቱ የታክስ ሥልጣንን በሶስት መደቦች የከፋፈለ ሲሆን፣ እነሱም የፌደራል መንግስት የታክስ ብቸኛ ሥልጣን፣ የክልል መንግስት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን እና የፌደራልና የክልል

[1] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አዋጅ ቁ. 1/1987፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ነሐሴ 13 ቀን 1987ዓ.ም. ፣ አዲስ አበባ።

መንግስሥታት የጋራ የታክስ ስልጣን ናቸው። በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት የፌደራል መንግስት ለፌደራሉ መንግስት በተሰጡ የገቢ ምንጮች ግብርና ቀረጥ መጣልና መሰብሰብ እንደሚችል በአንቀጽ 51(10) ተቀምጥዋል[2]። እንዲሁም የክልል መንግስታት በተመሣሣይ በአንቀጽ 52(2) (ሠ)[3] በተሰጣቸው የገቢ ምንጮች ግብርና ቀረጥ መጣልና መሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።

ወደ ጠበቆች ስንመለስ ከላይ በጠቀስናቸው ድንጋጌዎች መሰረት ጠበቆች በየትኛው የመንግስት ግብር ሊከፍሉ ይገባል የሚለውን ስንመለከት፡-

የፌደራል ጠበቆች በሚተዳደሩበት በፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ[4] አንቀጽ 9 መሰረት የፌደራል የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጠው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአሁኑ አጠራር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር መሆኑን ያስቀምጣል። ምንም እንኳን የፌዴራል የጥብቅና ፍቃድን የሚሰጠው የፌዴራል መንግስት አካል ቢሆን በአገልግሎቱ የተገኘ ገቢ ላይ ግን ግብር የሚሰበስበው የከተማው አስተዳደር ወይም ክልሎች ናቸው። የፌዴራል መንግስት አካል ፍቃድ ከሰጣቸው ስራዎች የተገኘ ገቢ ላይ ግብርን የፌዴራል መንግስት ይሰበስባል የሚል የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የጥብቅና ፍቃዱን የፌዴራል ተቋም መስጠቱ ብቻውን ግብር የመሰብሰብ ስልጣን የፌዴራል መንግስት ነው የሚያስብል አይደለም።

ክልሎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 97(4)[5] መሰረት ግለሰቦች ላይ የገቢ ግብርና የሽያጭ ግብር ግለሰቡ የሚኖርበት ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳድሮች ይጥላሉ፤ ይሰበስባሉ። ድርጅቶችን በተመለከተ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 98(2)[6] መሰረት በድርጅቶች ትርፍ ላይ የግብር እና የሽያጭ ታክስ መሰብሰብ የክልሎች እና የፌዴራል መንግስት የጋራ ስልጣን ነው። ስለዚህ የግለሰብ ጠበቆች ገቢ ላይ ግብር የመሰብሰብ ስልጣን የክልሎች እና የሁለቱ ከተማ አስተዳድሮች ሲሆን ከጥብቅና ድርጅቶች ገቢ ላይ ግብር መሰብሰብ ደግሞ የክልሎችና የፌዴራል መንግስት የጋራ ስልጣን ነው።

[2] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 51(10)

[3] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 52(2)(ሠ)

[4] የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249-2013፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 27ኛ ዓመት፣ ቁጥር 42፣ ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ አንቀጽ 9

[5] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አዋጅ ቁ. 1/1987፣ *ግርጌ ማስታወሻ 1* ፣ አንቀጽ 97(4)

[6] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 98(2)

2.3. ከጠበቆች እና ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች የሚሰበሰብ ግብር

ጠበቆችና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች ሁለት አይነት ግብሮች ይጣልባቸዋል። እነሱም ቀጥተኛ የሆነ (የገቢ ግብር) እና ቀጥተኛ ያልሆኑ የግብር አይነቶች (ተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ተርን ኦቨር ታክስ) ናቸው። የገቢ ግብር በቀጥታ ከጠበቆች ወይም ከጥበቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች የሚቆረጥ ሲሆን ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር ደግሞ የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆነ ደንበኛ ተሰብሳቦ የሚከፈል የግብር አይነት ነው። ከዚህ በታች የጠበቆች የገቢ ግብር አከፋፈል ከገቢ ግብር አዋጅ አንፃር ያለው ማዕቀፍ፣ እንዲሁም ጠበቆች ከደንበኞቻቸው ሰብስበው ለመንግስት የሚያስገቡት ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮችን የሚመለከት ዝርዝር የህግ ትንታኔ ተመልክቷል።

2.3.1. የገቢ ግብር

2.3.1.1. የገቢ ትርጉም እና የገቢ ግብር አመዳደብ ከገቢ ግብር አዋጁ አንጻር

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ግብር የመክፈል ኃላፊነት[7] አለበት። በዚህም መሰረት ጠበቆች በሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው።

የገቢ ግብር አዋጁ የግብር አከፋፈል ከዚህ በታች በተዘረዘሩት 5 ሠንጠረዦች መሰረት እንደሚከፈል ናቸው፣ እነዚህም፡-

- ሠንጠረዥ ''ሀ'' ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣
- ሠንጠረዥ ''ለ'' ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፣
- ሠንጠረዥ ''ሐ'' ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ፣
- ሠንጠረዥ ''መ'' ሌሎች ገቢዎች፣
- ሠንጠረዥ ''ሠ'' ከገቢ ግብር ነጻ የሆኑ ገቢዎች ናቸው።

[7] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 104፣ ነሐሴ 02 ቀን 2008 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ አንቀጽ 9

ግብር ከፋዮች ከዚህ በላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ በተቀመጡት ሰንጠረዦች በተቀመጡት ስሌቶች መሰረት የሚያገኙት ትርፍ ላይ የገቢ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን የግብር ከፋዮች ደረጃ ደግሞ በሚሰሩት የስራ አይነት ሳይሆን በሚያገኙት ገቢ መጠን መሰረት ከዚህ በታች በተመለከቱት ሶስት ደረጃዎች ያስቀምጣቸዋል። እነዚህም፡-

- የደረጃ ''ሀ'' ግብር ከፋይ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ከአንድ ሚሊዮን ብር ወይም ከዚህ በላይ፤
- የደረጃ ''ለ'' ግብር ከፋይ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ከአንድ ሚሊዮን ብር የሚያንስ ነገር ግን ብር አምስት መቶ ሺ ብር እና ከዚህ በላይ፤
- የደረጃ ''ሐ'' ግብር ከፋይ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር አምስት መቶ ሺ ብር የሚያንስ በማለት የሚከፋፈል ነው።

ጠበቆች እንደማንኛውም ግብር ከፋይ የሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር የሚከፍሉበት ስሌት በየትኛው ሰንጠረዥ ስር ይመደባል የሚለውን በምንመለከትበት ወቅት የገቢ ግብር ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 2/2 መመልከት ይኖርብናል። የገቢ ግብር አዋጁ ለግብር አከፋፈል ይረዳው ዘንድ ግብር ከፋዮችን ከላይ በተመለከተው ከሀ-ሠ ባሉት አምስት ሰንጠረዦች ስር የመደባቸው ሲሆን የጥብቅና አገልግሎት ስራም የሙያ ስራ በመሆኑ እና በገቢ ግብር አዋጁ 979/2/ በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ከሚያገኙት ትርፍ ላይ የግብር ክፍያቸውን የሚፈጽሙት በሰንጠረዥ ሐ ስር ይሆናል። በዚህ መልኩ እየተከፈለ ስለመሆኑም በዚሁ ጥናት ወቅት የተረጋገጠ ነው።

2.3.1.2. የሰንጠረዥ "ሐ" የተፈጻሚነት ወሰን፣ አመዳደብና ውጤቱ

ከላይ እንደተገለፀው የሰንጠረዥ "ሐ" የግብር ክፍያ የሚሰበሰበው በንግድ ስራ ከሚገኝ ገቢ ነው። በገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 2(2) መሰረት የንግድ ስራ ማለት "በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ **<u>የሙያ</u>** ወይም ቨኬሽናል ስራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም።"

በሰንጠረዥ "ሐ" ስር ሁለት አይነት የግብር ምጣኔዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። የመጀመሪያው በድርጅቶች ወይም በጠበቆች ድርጅት ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን አመታዊ ገቢው ከግምት ሳይገባ ቋሚ የሆነ የ30% የሆነ የግብር ምጣኔ ተግባራዊ ይደረጋል። ሆኖም 'ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች' በዚህ ምጣኔ ውስጥ አይካተቱም።

ሁለተኛው ምጣኔ በግለሰብ (የግለሰብ ጠበቆች) ላይ የሚፈፀም ሲሆን እንደግለሰቡ አመታዊ ገቢ ከ0% እስከ 35% የሚደረስ የግብር ምጣኔ ተግባራዊ ይደረጋል።

ከንግድ ስራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በዓመት	የንግድ ስራ ገቢ ግብር ምጣኔ
0 – 7,200 ብር	0%
7,201 – 19,800 ብር	10%
19,801 – 38,400 ብር	15%
38,401 – 63,000 ብር	20%
63,001 – 93,600 ብር	25%
93,601 – 130,800 ብር	30%
ከ130,801 ብር በላይ	35%

ግብር የሚጣልበት የንግድ ስራ ገቢ ከጠቅላላው አመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱ ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረገ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ላይ መሆኑን የገቢ ግብር አዋጅ በአንቀፅ 20 ላይ አስቀምጧል። በዚህ መሰረት ተቀናሽ የሚደረጉና የማይደረጉ ኪሳራዎችና ወጪዎች ይኖራሉ። የግብር ከፋዩ በሚያቀርበው የሒሳብ መዝገብ መሰረት ተቀናሽ መሆን የሚችሉ ወጪዎች በህግ በተወሰነ አግባብ ተቀናሽ ተደርገው በተቀረው ገቢ ላይ ግብር ይጣላል።

ከላይ የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ በደረጃ "ሐ" ስር ያሉ የደረጃ "ሐ" ግብር የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የለባቸውም። የሒሳብ መዝገብ የማይይዙ ከሆነ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በግምት ላይ የተመሰረተ የንግድ ስራ ግብር በገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 49 መሰረት ይጣልባቸዋል። ለዚህ አሰራር እንዲያመች የሚኒስትሮች ምክርቤት ያወጣው ደንብ ሲኖር በዚያ ደንብ በተዘረዘረው የስራ ዘርፍ አንፃር በቁርጥ የተጣራ ገቢያቸውን የሚገመትበት አሰራር አለ። ይህ አሰራር ከታች ባሉ ንዑስ ምዕራፎች የተሸፈነ ሲሆን በደንብ ቁጥር 410/2009 መሰረት የሂሳብ መዝገብ ያልያዙ ጠበቆች እንደ ሌሎች ግብር ከፋዮች ሁሉ (የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች እና መዝገብ መያዝ ኖሮባቸው ግን ያልያዙ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች) ካሳወቁት አመታዊ ገቢ 25% የሚሆነው እንደትርፍ ወይም እንደተጣራ ገቢ ተወስዶ በዚህ ገቢ ላይ ብቻ ግብር ይጣላል።

2.3.1.3. <u>የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ስራ የተለዩ ባህሪያት ያለው ስለመሆኑ</u>

ከላይ የተብራሩት የግብር የህግ ማዕቀፎች ዝርዝር የስራ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ሳይሆን በገቢ መጠን እና በአምስት ሰንጠረዦች በተከፋፈሉ የስራ አይነቶች ላይ የተቀመጡ ናቸው። ከጠበቆችና የስራ ባህሪይ አንፃር ለአሰራር አመቺ እና ተግባቢ የሆነ ልዩ የህግ ማዕቀፍ የለም።

ስራ ላይ ያሉት የፌደራል ጠበቆች የሚመለከቱ ሕጎች፣ የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013[8] እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ 57/1992[9] ናቸው፡ ፡ እነዚህም የፌደራል ጠበቆች የሚመለከቱ ህጎች የፌደራል ጠበቃ ስራ ከሌሎች ሥራዎች ምን እንደሚለየው፣ የተለዩ ባሕሪዎች እና አላማ በግልጽ እና በዝርዝር ያስቀምጣሉ። የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ከሌሎች የሙያ ስራዎች ወይም የንግድ ስራዎች የሚለይባቸው የተለያዩ ነጥቦች ያሉ ቢሆንም የግብር አከፋፈሉን የገቢ ግብር ህጎች ከዚህ በላይ በተመለከተው የጥናቱ ክፍል እንደተመለከተው የስራ ባህሪን መነሻ ያደረጉ ባለመሆናቸው ምክንያት የጠበቆች የግብር አከፋፈል ላይ የተለያዩ ችግሮች ሲታዩ ይስተዋላል።

የጥብቅና ስራ ከሌሎች የሙያ እና የንግድ ስራዎች የተለየ የሚያደርጋቸው ባህሪያት በመኖራቸው ምክንያት ይሄንኑ መነሻ ያደረገ የግብር አከፋፈል ስርአት ሊኖረው ይገባል። የጥብቅና ስራ ለማከናውን ተገቢው የሙያ ፍቃድ ከፍትህ ሚ/ር የሚሰጥ ሲሆን ምንም አይነት የንግድ ፍቃድም ሆነ ሌላ አይነት የሙያ ፍቃድ ማውጣት ሳይፈለግ የሚከናወን ስራ ነው። በንግድ ሚኒስቴር በንግድ ፍቃድ መስጫ እና ማውጫ መድብል ዝርዝር ላይም የጥብቅና አገልግሎት ስራ አለመኖሩ ለዚህ ሌላ ማረጋገጫ ነው።

የጥብቅና ሙያ ስራ ራሱን በቻለ አዋጅ ፣ ደንብ እና መመሪያዎች የሚመራ፣ በፍትህ አካላት ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ከንግድ ስራ የተለየ ባህሪ ያለው አገልግሎት ነው። ጠበቆች ከስራው ሊከፈላቸው የሚገባው ክፍያ መጠን የክፍያ ጣሪያ የወጣለት በመሆኑ፣ በየአመቱ የሚጠበቅባቸው የነጻ አገልግሎት ፣ የጥብቅና ሰራ በሚከናወንበት ወቅት ከጠበቆች የሚጠበቁ ግዴታዎች ፣ የጠበቃ እና የደንበኛ መካከል ስለሚኖረው

[8] የፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249-2013፣ *የግርጌ ማስታወሻ 4*

[9] የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ 57/1992፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ መስከረም 13 ቀን1992 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ግንኙነት እና የውል ይዘት እንዲሁም ሌሎች የጥብቅና አገልግሎት በሚከናወንበት ወቅት ከጠበቃው እና የሚጠበቅ ሌሎች የሙያ ስነምግባሮች በእነዚህ ህጎች ተመልክተዋል።

በቅርቡ በጸደቀው የፌዴራል ጠበቆች አዋጅ ላይ የጥበቅና ድርጅት የሚከናወን ስራ የጥብቅና ስራ እንደ ንግድ እና ኢንቨስትመንት የማይቆጠር ስለመሆኑ የተመለከተው የህግ ድንጋጌም የጥብቅና አገልግሎት ስራ የተለየ ባህሪ ያለው ስለመሆኑ በሕግ አውጪው ጭምር የተረጋገጠበት መሆኑን መመልከት ይቻላል።

የጥብቅና አገልግሎት ስራ እንደሌሎች የፍትህ አካላት ሁሉ የህግ መርህን እና ሕግን የማስከበር እንደሁም የፍትህ አስተዳደሩን የማገዝ ሃላፊነት የተጣለበት ስራ መሆኑ ራሱ የስራውን የተለየ ባህሪ ማሳያ ነው።

የጥብቅና ስራ ከሌሎች የንግድ ስራዎች ወይም ሌሎች ስራዎች የተለየ ባህሪ ያለው ቢሆንም የግብር አከፋፈሉን በተመለከተ የተለየ የግብር አከፋፈል ስርአት ባለመኖሩ ምክንያት ጠበቆች ግብር በሚከፍሉበት ውት የተለያዩ ችግሮች እያጋጠማቸው ይገኛል።

አግባብነት ያለው የግብር ህግ በተለይም ከወጪ አያያዝ ጋር እና ስራው ከሚፈጀው ጊዜ አንጻር በተያያዘ የወጡት ህጎች የንግድ ስራን መሰረት ያደረጉ በመሆን ከጥብቅና የስራ ባህሪ አንጻር የተለያዩ ችግሮች ይስተዋላሉ።

2.3.1.4. <u>ከገቢ ግብር በተቀናሽነት የሚያዙ ወጪዎች</u>

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 82 መሰረት የታክስ ሒሳብ መዝገብ የመያዝ ኃላፊነት ያለባቸው የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮችና በፈቃደኝነት የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ናቸው። በተመሳሳይ የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ የታክስ ሒሳብ መዝገብ ስለመያዝ የወጣው መመሪያ [10] በተደነገገው መሰረት፣ የደረጃ ''ሀ'' እና ''ለ'' ግብር ከፋይ በታክስ ሕግና በዚህ መመሪያ፣ በፈቃደኝነት የሒሳብ መዝገብ የሚይዝ ''ሐ'' ግብር ከፋይ የታክስ ሒሳብ መዝገብ መያዝ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህ ግዴታ ኖሮበት የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ጠበቃ ደግሞ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ሰነዶችን ባለመያዝ ቅጣት የሚከፍል

[10] የታክስ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ፣ አዲስ አበባ፣ አንቀጽ 3

መሆኑን የታክስ አስተዳደር አዋጁ ደንግጎ እናገኘዋለን።[11] እንዲሁም በደረጃ ''ሀ'' ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው የደረጃ ''ሀ'' ግለሰብ ከፋዮችን፣ ማለትም የደረጃ ''ሀ'' ለሆነ ጠበቃ ተግባራዊ ይሆናል ማለት ነው።[12]

በ"ታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011" መሰረትም ከሒሳብ መዝገብ በተጨማሪ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ታክስ ከፋዮች እንዲሁም በፍላጎት የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ የደረጃ "ሐ" የግብር ከፋዮች የታክስ ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው።[13] የገቢ ግብር ወይም ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸውም ወኪሎችም በዚህ መመሪያ መሰረት የኤሌክትሮኒክስ ወይም የማኑዋል ደረሰኞችን በመጠቀም 'ግብይቶችን' ማከናወን ይኖርባቸዋል።[14] ስለሆነም ጠበቃዎችና የጥብቅና ድርጅቶች የደረጃ "ሀ"፣ የደረጃ "ለ" ወይም ደግሞ በፍላጎት የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ ከሆነ እንዲሁም ደግሞ በስራቸው ሰዎችን ቀጥረው የገቢ ግብር የሚሰበስቡ ወይም ተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው ገቢ የሚያደርጉ ከሆነ ህጋዊ ደረሰኞችን በማሳተም "በግብይቶች" ወቅት መጠቀም አለባቸው። በታክስ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀፅ 9(2) መሰረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሆነው በልዩ ሁኔታ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለመጠቀም የማይገደዱ የንግድ ዘርፎች አሉ። በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ባወጣው ሰርኩላር ቁጥር 1/202/10 ዝርዝር ውስጥ ጠበቆች በመካተታቸው የኤሌክትሮኒክስ የሽያጭ መሳሪያ እንዲጠቀሙ አይገደዱም፤ የማኑዋል ደረሰኝ የመጠቅም ግዴታቸው በገቢ ግብር አዋጁ እና በጠበቆች ስነምግባር ደንብ አግባብ እንደተጠበቀ ነው።

[11] የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ ዕትም፣ 22 ዓመት ቁጥር 103፣ ነሐሴ 14 2008 ፣አዲስ አበባ፣ አንቀጽ 102

[12] ፌዴራል ገቢዎች መመሪያ፡- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ታክስ ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁ. 145-2011፣ አንቀጽ 3

[13] የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ አንቀፅ 3

[14] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 3፣ 7፣ 8 እና መግቢያ

በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት የግብር ከፋዩ ጠበቃን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽነት የሚያዙ ወጪዎች በአዋጁ ተቀምጠዋል።[15] እነዚህ ተቀናሾች 'ከጠበቃ ስራ ጋር በተጨባጭ ትክክለኛ ገቢውን ለመወሰን ተገቢ መለኪያ ናቸው' የሚለው አከራካሪ ቢሆንም በአዋጁ የተቀመጡት ተቀናሾች ለማየት ያክል በንግድ ስራው ገቢውን ውስጥ የተካተቱን ገቢዎች ለማግኘት ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር አመት ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ ወጪዎች፣ የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሐብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣ ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች[16] እንደተቀናሽ የሚያዙ ናቸው።

በገቢ ግብር ደንብ መሰረትም "የውክልና ወጪ" ማለትም አንድ ግብር ከፋይ ሠራተኛ የንግድ ሥራውን ለማስተዋወቅ እና ለማሳደግ፣ እንግዶች ከንግድ ሥራ ቦታው ውጪ ለመቀበል የሚያወጣ የመስተንግዶ ወጪ[17] ተቀናሽ ወጪ ተደርጎ ተቀምጧል። ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረግ ስጦታ[18]፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ለሰራተኞች የተደረገ የህክምና ወጪ፣ የንግድ ስራ ማስታወቂያ ወጪ፣ የንግድ ቦታ እድሳት ወጪ፣ የካፒታል እቃዎች ኪራይ[19] የመሳሰሉትም የተቀናሽ ወጪ አይነቶች ናቸው። በዚህ ረገድ የገቢዎች ሚኒስቴር ስለ ተቀናሽ ወጪዎች ያወጣው መመሪያ[20] በጥልቀት የተቀናሽ አሰራር እና አቀናነስ የሚያስቀምጥ ነው። ሆኖም ከአዋጁ እና ከደንቡ በተጨማሪ የሚያዙ ተቀናሽ ወጪዎች የሌሉ መሆናቸውንና ከጥብቅና አገልግሎት ስራ ጋር ተዛማችነት ያላቸው ወጪዎች አለመኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል።

ከተቀናሽ ወጪዎች በተጨማሪም ከገቢ ግብር ነጻ የተደረጉ ገቢዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም በመመሪያው[21] መሰረት ተቀጣሪዎች የትራንስፖርት አበል እና የመጓጓዣ ወጪ፣ የውሎ አበል፣ ሽልማት ላይ የሚደረግ

[15] የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 23ኛ ዓመት፣ ቁጥር 82፣ ነሐሴ 19 2009 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ፣ ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 22

[16] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 24

[17] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 27

[18] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 33

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ከአንቀጽ 31-35

[20] ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ።

[21] ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ከግብር ነጻ የሚደረግበት ሁኔታ አስቀምጧል። ይሄ መመሪያ በገቢ ግብር አዋጁ አንቀፅ 65(1) መሰረት የተዘረዘሩትን ከግብር ነፃ የሆኑ ወጪዎችን በዝርዝር ያብራራል። ጠበቃዎች በግልም ሆነ በህዝብ ትራንስፖርት ተጠቅመው ከቦታ ቦታ በብዛት የሚጓዙ ሲሆን እንዲሁም በውሎዋቸው ደግሞ ከመደበኛ የመስሪያ ቦታ ወይም ቢሮ ውጪ በተለያዩ ፍርድ ቤቶችና የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአካል በመገኘት የሚሰሩ ናቸው። ሆኖም የዚህ መመሪያ እና የገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 65(1) ታሳቢ ያደረገው ተቀጣሪዎችን እንጂ እንደጠበቃ ያሉ የሙያ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን አለመሆኑ ከዚህ እነዚህ ወጪዎች በግብር ወቅት ታሳቢ እንዳይደረጉ ያደርገዋል።

የሒሳብ መዝገብ አያያዝ አሰራር ለጠበቆች አመቺ ባለመሆኑ ምክንያት ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ሲቸገሩ ይስተዋላል። በዚህ መሰረት ደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋይ የሆኑ ጠበቃዎች የሂሳብ መዝገብ ባለመያዛቸው ቅጣት በመክፈል እንደደረጃ 'ሐ' ከፋዮች በመመሪያ ቁጥር 138/2010 መሰረት ግብር ይከፍላሉ። በዚህ መመሪያ ስር ባለው ሰንጠረዥ መሰረት የጠበቃ የተጠራ ትርፉ 25% እንደሆነ ተቀምጧል። ስለሆነም አንድ ጠበቃ ምንም እንኳን የሂሳብ መዝገብ ባይይዝም በአመት ውስጥ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ 25% የሚሆነው የተጣራ ትርፍ (ገቢ) ተደገጎ ይወሰዳል። የገቢ ግብር የሚጣለውም በዚህ የተጣራ ገቢ ላይ ይሆናል።

2.3.1.5. ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች እና የአመታዊ ገቢ አወሳሰን

ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል ማለት ስራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ12 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዓመት ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ስራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ማለት እንደሆነ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 32(6) ያስቀምጣል። በአንቀፅ 32 መሰረት አንድ ግብር ከፋይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል ፈፅሞ ስራውን እያከናወነ ካለ፣ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሰረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ስራ ገቢው ውስጥ በማካተት ወጪው በዚያው መቶኛ ልክ በተቀናሽነት እንዲያዝ ይደረጋል።

ከአዋጁ ትርጉም የምንረዳው የጥብቅና አገልግሎት ስራን 'ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል' ውስጥ ታሳቢ እንዳላደረገው ነው። የዚህ አንቀፅ ትኩረት ከማምረት፣ መትከል እና መገንባት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች ላይ እንደሆነ በእዚያው አንቀፅ የተቀመጠው ትርጓሜ ያስረዳል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በመስከረም 2014ዓ.ም ያወጣው "በግብር እና በታክስ ህጎች አፈፃፀም ረገድ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ"

ሰነድ በተመሳሳይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውልን ከሪል እስቴት እና ከግንባታ ጋር አገናኝቶ ማብራሪያ ሰጥቶበታል።

የጥብቅና ስራን ባህሪይ ስናየው አንድ ስራ ወይም አንድ ውል ለረጅም አመታት ይቆያል። በውሉም ላይ እንደግንባታ ውል የጊዜ ገደብ አይቀመጥም። ስራው የሚጠናቀቅበት ጊዜ ተገማች አይደለም። ሆኖም ስራው ከአንድ የግብር አመት አልፎ ወደሌላ የግብር አመት መዝለቁ የማይቀር ነው። ደንበኞች የሚከፍሉበት አግባብም በየጊዜው በሚፈፀም ክፍያ (installment payment) መሰረት ነው።

የአንቀፅ 32 አተገባበር ለጥብቅና ስራ ለመጠቀም እጅግ አዳጋች መሆኑ ሌላው የጥብቅና ስራ ሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ቢሆን በህጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ክፍተት ያለበት መሆኑን አንዱ አስረጂ ነው። ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሰው የገንዘብ ሚኒስቴር ማብራሪያ እንደሚያሳየው የግንባታ ስራዎች በተቆጣጣሪ መሀንዲስ በሚሰጥ የምስክር ወረቀት ስራው ስንት በመቶ እንደተጠናቀቀ ማወቅ ይቻላል። በጥብቅና ሙያ አገልግሎት ግን አንድ ጠበቃ የያዘው የፍርድ ቤት ጉዳይ ወይም ማናቸውም ሌላ ስራዎች ምን ያህል እንደተጠናቀቀ ማወቅ አይቻልም። ስለዚህ ለአንድ ጠበቃ አንቀፅ 32ን መሰረት በማድረግ በግብር አመቱ የተሰራውን ስራ፣ የተከፈለውን ክፍያ እና የወጣውን ወጪ ግምት በማስላት የተጣራ አመታዊ ገቢን ማሳወቅ አስቸጋሪ ይሆናል፤ አንቀፁም የተቀመጠው የማምረት እና የግንባታ ስራዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። የጥብቅና ሥራ በተለይም የፍ/ቤት ሙግት ሥራ በቀጥታ ከፍርድ ቤቶች ሥራ አፈፃፀም ጋር የተያያዘ በመሆኑና የፍርድ ቤቶች የፍርድ ሥራ ሂደት ደግሞ በባህሪው ረጅም ጊዜ የሚወስድና ተገማች ባለመሆኑ ጠበቆች ከደንበኞቻቸው ጋር በሚያደርጉት የጥብቅና አገልግሎት ውል ውስጥ የሚጠቀስ ክፍያ ላይ የሚጣል ግብር አፈፃፀምና አከፋፈል ላይ በግብር ሰብሳቢው መ/ቤትና በጠበቆች መካከል ተደጋጋሚ አለመግባባት አስከትሏል።

2.3.2. ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ

ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ በአምራች፣ አከፋፋዮች ወይም አገልግሎት ሰጭዎች ላይ የሚጣል ቢሆንም በተዘዋዋሪ ወደ ሌላ ከፋይ የሚሸጋገር እና አብዛኛውን ጊዜ የመጨረሻ ከፋዩ ተጠቃሚዉ የሚሆንበት የታክስ አይነት ነዉ። ከቀጥታ ታክሶች በተለየ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች የሚጣሉት በሸቀጦች እና አገልግሎቶች ላይ እንጂ በግለሰብ ግብር ከፋዮች ላይ ባለመሆኑ ታክሱ የሚሰበሰበውም በችርቻሪዉ፣ አገልግሎት ሰጭዉ ወይም በአምራቹ ነው። የሽያጭ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተእታ) ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ሁለት ምሳሌዎች

ናቸው። የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ አይነቶች የሚመደቡ ሲሆኑ ለፌደራል መንግስቱ ገቢ የሚደረጉም ናቸዉ። እነዚህ የታክስ አይነቶች የመጨረሻ ከፋዩ ተጠቃሚዉ በመሆኑ የፍጆታ ታክስ በመባልም ይታወቃሉ። አላማቸዉም የመንግስትን ገቢ ከፍ ከማድረግ በተጨማሪ ሰዎች ገንዘብ እንዲቆጥቡ ማበረታት እና ፍጆታን እንዲቀንሱ ማድረግ ነዉ። በህግ አገልግሎትም የሚሰበሰቡ የሽያጭ ታክሶች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ናቸው።

2.3.2.1. <u>ተርን ኦቨር ታክስ፤</u>

የፌዴራል ተርን ኦቨር ታክስ የሚመራው በአዋጅ 308/1995[22] እና እሱን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ 611/2001[23] መሰረት ነው። የተርን ኦቨር ታክስ አገልግሎትን የዕቃዎች ዝውውር ሳይጨምር በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው በማለት በጠቅላላው የጥብቅና ሙያ እና የጥብቅና አገልግሎትን ጨምሮ ትርጉም የሰጠበት ነው።

ከተርን ኦቸር ታክስ ነፃ የሆኑ የአገልግሎት ሽያጮች የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ የህክምና አገልግሎቶችና በሀኪም የሚታዘዙ መድሀኒቶች፣ የትምህርት አገልግሎቶች፣ ፖስታ አገልግሎቶች እና የትራንስፖርት አገልግሎቶች የመሳሰሉት ናቸው።[24] የተቀሩት አገልግሎቶች በሁለት የተለያዩ ምጣኔዎች በ2% እና በ10% የተርን ኦቨር ታክስ የሚጣልባቸው ናቸው።

አገልግሎቶች ላይ በተጣለው የተርን ኦቨር ታክስ ተመን መሰረት የህግ አገልግሎት ሁለት ፐርሰንት የተርን ኦቨር ታክስ ከሚሰበሰብባቸው የአገልግሎት አይነቶች ውስጥ የሌለ በመሆኑ አሥር ፐርሰንት ከሚጣልባቸው ሌሎች ምድብ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል።[25]

የተርን ኦቨር ታክስን በተመለከተ የተርን ኦቨር ታክሱን ስሌት በትክክል የማከናወን፣ የታክሱን ማስታወቂያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣን የማቅረብና ታክሱን በጊዜው የመክፈል ኃላፊነት የታክስ

[22] የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ አመት፣ ቁጥር 21፣ ታህሳስ 22 1995፣ አዲስ አበባ።

[23] የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ አመት፣ ቁጥር 8፣ ታህሳስ 16 2001፣ አዲስ አበባ።

[24] የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣ *ግርጌ ማስታወሻ 34*፣ አንቀጽ 7(1)

[25] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 4

ከፋዩ መሆኑን ህጉ ይደነግጋል።[26] የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ መቅረብ እና ታክሱን መከፈል ያለበት የተሻሻለው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ እያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ ለሚወክለው ተቋም የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ መክፈል እንዳለበት ይደነግጋል።[27]

2.3.2.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ

የፌደራል የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጅ[28] ቁጥር 285/1994፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 609/2001[29]፤ በአዋጅ ቁጥር 1157/2011፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ [30]፤ እንዲሁም የፌዴራል ገቢዎች መመሪያ በሆነዉ የተ.ዕ.ታ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ቁ. 148/2011[31] የሚመራ ነው።

እነዚህም ህጎች ጠበቆች ላይ ተግባራዊ የሚሆኑ ሲሆኑ በሕጎቹም የታክስ ከፋዮች፣ አገልግሎት ማቅረብ ትርጉም፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ፣ ታክሱ ስለሚጣልባቸው ሽያጭ እና አገልግሎቶች፣ የመመዝገብ ግዴታ እና ታክስን ስለማቀናነስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በተጨማሪም የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ የሕክምና አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች፣ የትምህርት አገልግሎት ከታክስ ነጻ መደረግ እና ሌሎች ድንጋጌዎች ከጠበቆች ስራ አኳያ ያላቸው እድምታ እና ተግባራዊነትን ማየት ያስፈልጋል።

---

[26] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 8(1)

[27] የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ *ግርጌ ማስታወሻ 35* ፣ አንቀጽ 2

[28] የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ አመት፣ ቁጥር 33፣ ሰኔ 27 ቀን 1994፣ አዲስ አበባ።

[29] የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ 609/2001፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ አመት፣ ቁጥር 6፣ ታህሳስ 16 ቀን 2001፣ አዲስ አበባ።

[30] የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1993፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ አመት ቁጥር 19፣ ታህሳስ 22 ቀን 1993፣ አዲስ አበባ።

[31] የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 148/2011፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011፣ አዲስ አበባ።

የተጨማሪ እሴት ታክስ ህጎች ከታክስ ነፃ፣ ዜሮ ምጣኔ እና 15% ምጣኔ ብለው ለሶስት አገልግሎቶችንና የእቃ ሽያጮችን ይመድባሉ። በዚህ መሰረት በዜሮ ምጣኔ የሚስተናገዱት ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ የዕቃዎች ወይም የመንገደኞች ዓለምአቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅና በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅትን መሸጥ ናቸው።[32] ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑት የእቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጮች ደግሞ ያገለገሉ መኖሪያ ቤቶች ሽያጭና ኪራይ፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ የህክምና አገልግሎቶችና በሀኪም የሚታዘዙ መድሀኒቶች፣ የትምህርት አገልግሎቶች፣ ፖስታ አገልግሎቶች እና የትራንስፖርት አገልግሎቶችና የመሳሰሉት ናቸው።[33]

ስለዚህ የጥብቅና ስራ ከታክስ ነፃ ያልተባለ ወይም ዜሮ ምጣኔ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ ጠበቆችና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች ዓመታዊ የገቢ መጠናቸው ከአንድ ሚሊየን ብር በላይ (ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ) እስከሆኑ ድረስ ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የ15% የተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበስባሉ።[34]

2.3.2.3. በጥብቅና ሙያ አገልግሎት ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ አግባብነት

ከዚህ ቀደም እንደተገለፀው የጥብቅና አገልግሎት ላይ የ15% የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ደግሞ የ10 % የተርን ኦቨር ታክስ በተገልጋዮች ላይ ይጣላል። በሌላ ጎን እንደትምህርት፣ ትራንስፖርት እና ህክምና ያሉ አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የተርን ኦቨር ታክስ ያልተጣለባቸው መሆኑ አገልግሎቶቹ ለማህበረሰቡ ካላቸው ጥቅም አንፃር ተገቢ መሆኑ እሙን ነው።

ከዚህ አንፃር የህግ አገልግሎት ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴትና የተርን ኦቨር ታክስ በሕገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች የሚገድብ መሆኑን አንስቶ የህጉን አግባብነት መመርመር ይቻላል። ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር "የሕግ አገልግሎት ተጠቃሚው ወደ ባለሙያው የሚሄደው ተገዶ እንጅ እንደሌሎች አቅርቦቶች ፈልጎ ባለመሆኑ፣ ፍትሕ ደግሞ እንደሌሎች ሸቀጦች አለመሆኑ ታሳቢ ተደርጎ የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ

[32] የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994፣ *ግርጌ ማስታወሻ 40* ፣ አንቀጽ 7(1)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1993፣ *ግርጌ ማስታወሻ 42* ፣ አንቀጽ 34-38

[33] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 8(2)

[34] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 7(1)

የተርን ኦቨር ታክስ ሊሰበሰብበት አይገባም።" [35] የሚል የመከራከሪያ ነጥብ ሊነሳ ይችላል። በሌላ አገላለፅ እነዚህ ታክሶች የዜጎችን ፍትሕ የማግኘት ሕገ-መንግስታዊ መብት በአሉታዊ መልኩ ይጎዳዋል። በተቃራኒው ደግሞ "እነዚህ ታክሶች ከቀሩ የመንግስትን የፋይናንስ አቅም በማዳከም ሌሎች ሕገ-መንግስታዊ መብቶችን ለማስከበርና የመንግስትን መሰረታዊ ስራዎች እንዳይፈፅም እንከን ይፈጥራል" የሚል ነጥብም ሊነሳ ይችላል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሀገራችን ኢትዮጵያ በ World Justice Project rule of law index – ሰዎች ከፍትሐብሄር ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ፍትህን ለማግኘት እና ለመስጠት ያለባቸዉን የገንዘብ ጫና ግምት ዉስጥ በማስገባት በሚሰጠዉ ደረጃ ከ140 ሀገሮች 120ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች[36]። የፍትህ ተደራሽነትን እና ጥራቱን የጠበቀ የህግ አገልግሎት ለማስፋት ጠበቆች ከደንበኞቻቸዉ የሚጠይቁት ክፍያ ተመጣጣኝ መሆን አንዱ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና እንደ ተ.እ.ታ ያሉ ቀጥተኛ ያለሆኑ ታክሶች በቀጥታ በጠበቃዉ ሳይሆን በተገልጋዩ የሚከፈሉ በመሆኑ የጥብቅና ክፍያዉ ከፍ ሊል እንደሚችል ይታመናል። ይህም ከሌሎች ሀገሮች አንጻር ኢትዮጵያ ለፍትህ ተደራሽነት መሳካት ያላትን ትኩረት አናሳ ያደርገዋል።

የእነዚህ የሽያጭ ታክሶች ለተገልጋዮች ከሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅእኖ እንዳለ ሆነ ለጠበቆችም አሉታዊ ጎኖች አሏቸው። ሌሎች (ነጋዴዎች) በአገልግሎት ወይም በእቃ ሽያጭ ወቅት ከሌላ ነጋዴ ሲገበያዩ የከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ በቀጣይ እራሳቸው ለሌላ ገዢ በሚሸጡበት ወቅት ተጨማሪ እሴት ታክስ በማስከፈል ያወራርዱታል። የሽያጭ ታክስ አላማም ብዙ ግብይቶች ሲደረጉ የሚጨመሩ ተጨማሪ እሴቶች እንደሚኖሩ ታሳቢ ያደረገ ነው። ወደ ጥብቅና ስራ ስንመጣ ግን ጠበቆች የሚያወራርዱት ግብይት የለም። የሰበሰቡትን ግብር ቀጥታ ለመንግስት ይሰጣሉ። ይህም ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች በጠበቃው ላይ የሚያመጡት ጫና ባይኖርም በፍትህ ተደራሽነት ላይ ግን አሉታዊ ተፅዕኖ መሳደሩ አይቀርም።

[35] ሙሐመድ ዳዉድ አልቃድር፣ *በኢትዮጵያ ከሕግ አገልግሎት የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ፤ አዙሪት ጥያቄዎችና መዉሰብሰቦች፣* Bahir Dar University Journal of Law, Vol.8, No.2 (June 2018), ገፆች 271-275

[36] https://worldjusticeproject.org/rule-of-law-index/country/2022/Ethiopia/Civil%20Justice/ - ህዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም የተገኘ።

2.4. የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶችን የታክስ አከፋፈል በተመለከተ የውጭ አገራት ልምዶች

በፌደራል ጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች በሥራ ላይ ያለውን የግብር አከፋፈል በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ሲነሱ መቆየታቸው የሚታወስ ነው። የቅሬታዎቹ መነሻዎቹ የጥብቅና ሥራን እንደሌሎች የንግድ ሥራዎች በመቆጠርና የሙያውም (የአገልግሎቱን) ልዩ ባህሪ ከግምት ያለማስገባት የአመለካከትና የግንዛቤ ችግር አንዱ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዘው ያሉ የአሰራር ወጥነት ችግሮች ግልጽ የሆኑ ሕጐች አለመኖር ያሉትንም ያለማክበር፤ ከሒሳብ መዝገብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ ከወጭ አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። የሌሎች አገሮችን ልምድን መፈተሽ በጥናት ዘዴው የተመለከተ እንደመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በተመለከተ የሀገራት ልምድ ምን እንደሚመስል ማየት ለችግሮቹ መፍትሄ ለማመላከት እስፈላጊ ነዉ። በዚህም መሰረት በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ፤ እንዲሁም በህግ ስርዓታቸው በተሻለ ምሳሌ ይሆናሉ በሚል ከአፍሪካ አህጉር፤ ከአውሮፓና አሜሪካ የተመረጡ ሀገራትን ልምድ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ፤ እንዲሁም በህግ ስርዓታቸው በተሻለ ምሳሌ ይሆናሉ በሚል ከአፍሪካ አህጉር፤ ከአውሮፓና አሜሪካ የተመረጡ ሀገራትን ልምድ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በዚህም የናይጄሪያ፤ ኬንያ፤ ታንዛኒያ፤ ሩዋንዳ፤ ዩናይትድ ኪንግደም፤ አየር ላንድ፤ ቱርክ እና ዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ ተመርጠዋል። በዚሁ አግባብ የአገራቱ የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የታክስ አከፋፈል ዳሰሳ እንደሚከተለው ይቀርባል።

2.4.1. ናይጄሪያ፤

ናይጄሪያ የፌደራል ስርአት የምትከተል ስትሆን በአፍሪካ አህጉር ጠንካራ የጠበቆች ማህበር ካላቸው ሀገራት ተርታ የምትመደብ ሀገር ነች። NBA /Nigerian Bar Association/ በአህጉሩ ተጽእኖ ፈጣሪ ከሚባሉ ተቋማት አንዱ ለመሆን የቻለ ሲሆን በ36 ቱ የናይጄሪያ ግዛቶች ከ130,000 የሚጠጉ አባላት ያሉት ነባር የሙያ ማህበር ነው። ከላይ የተነሳው ለመግቢያ ያህል እንዲረዳና የኛይጄሪያ ልምድ ለምን እንደተመረጠ በጥቂቱ ለመጠቆም እንጂ የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማ ስለሆነ አይደለም።

የጥብቅና ስራ የታክስ አስተዳደር ስርአትን በሚመለከት በናይጄሪያ አግባብነት ያላቸው የህግ ማእቀፎች እ.ኤ.አ በ1999 የወጣው ከናይጄሪያ ህገመንግስት የሚጀምር ነው። በዚሁ ህገመንግስት ክፍል 24 ሁሉም

ዜጋ ገቢውን በማሳወቅ በታማኝነት የግብር ግዴታውን ሊወጣ እንደሚገባ ያዛል። በሌላ በኩል በህገመንግስቱ መሰረት የታክስ አይነቶችን የፌደራል ታክስ፤ የክልል/State/ ታክስ እና የአካባቢ /local government tax/ ታክስ በሚል ተከፋፍለው ተሰጥተዋል። ለምሳሌም የፌደራል መንግስቱ በክፍል 1 ዝርዝር ውስጥ በቀረጥ፣ ኤክሳይስ ታክስ፤ኤክስፖርት እና ስታምፕ ግብር፤ የድርጅቶችን ታክስ እና መሰሎችን ለመሰብሰብ ግልጽ ስልጣን ተሰጥቶታል። በሌላ በኩል ክልሎች የግለሰቦችን የገቢ እና የስታምፕ ግብር /ግለሰብ ጠበቆችን ይጨምራል/ ለመሰብሰብ ስልጣን አላቸው።

ከህገመንግስቱ በመለስ እ.ኤ.አ በ2004 የወጡት የግለሰብ የገቢ ግብር ህግ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ፤ የስታምፕ ቀረጥ ህግ፤ ካፒታል ጌይን ግብር ህግ፤ የካምፓኒዎች የገቢ ግብር አዋጅ፤ የቀረጥና ኤክሳይስ አስተዳደር ህግ እና ሌሎች የሚጠቀሱ ናቸው። ከላይ በዝርዝር በተጠቀሱ የታክስ የህግ ማእቀፎች መሰረት የናይጄሪያ የግብር መ/ቤት በሚከተሉት አይነቶች ከጠበቆችና ከጥብቅና ድርጅቶች የገቢ ግብር ታክስ ይሰበስባሉ።

1/ ከተቀጣሪ ጠበቆች በወር በደሞዝ ደረጃቸው ልክ የግብር ግዴታቸውን የሚወጡ ይሆናል።

2/ የማማከር፤ የአስተዳደር አገልግሎት፤ ኪራይ፤ የዳይሬክተር ክፍያ እና ወለድ የሚያገኙ ሲሆን ዊዝ ሆልድ የሚደረጉ ይሆናል።

3/ ያለ ቀጣሪ ራሳቸውን ችለው ለሚሰሩ ጠበቆች ከገቢያቸው ላይ በቀጥታ እየተሰላ የግብር ግዴታቸውን የሚወጡ ይሆናል።

ቀጥተኛ ያልሆኑ የግብር ግዴታዎችን በተመለከተ፤

ግብሩን የናይጀሪያ ልምድ እንደሚያሳየው ሁሉም ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች የቫት ምዝገባ እንዲያደርጉ፤ ታክስ እንዲሰበስቡ እና የግብይት መዝገብ እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም ባለፈ ጠበቆቹም ሆኑ የጥብቅና ድርጅቶቹ ለታክስ/ቫት የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው። ይህ ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ የመጀመሪያው ወር ብር 10 ሺ ናይራ ቅጣት የሚጣልባቸው ይሆናል። ይኸው መተላለፍ ከቀጠለ ቀጥሎ ላሉት ወራቶች ከቀጠለ በየወሩ 5 ሺ ናይራ በቅጣት መልክ የሚታሰብ ይሆናል።

ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን በተመለከተ በተመሳሳይ የጥብቅና ድርጅቶች እና ጠበቆች ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን ይከፍላሉ። በዚህም እ.ኤ.አ በ2004 በወጣው Value Added Tax Act Cap VI LFN መሰረት በናይጄሪያ በጠበቆች የሚሰበሰበው የቫት ክፍያ መጠን 5 በመቶ ነው። Stamp Duties የቴምብር ግብር ግዴታዎችን በተመለከተ ሁሉም ጠበቆች በሕግ በተለያዩ ሰነዶች ላይ ግብር ይከፍላሉ። ለምሳሌ፤ የባንክ ዋስትናዎች፤ የስቶክ ሰነዶች፤ ምደባ ሰነዶች፤ ኦኩፖንሲ ሰርተፊኬት፤ ደረሰኞች፤ የጠበቆች ዋስትናና የመሳሰሉት ሰነዶች ላይ ግብር እንዲከፍሉ ይጠበቃል። ይህ አይነቱ የታክስ ግዴታ በግብይቱ ላይ እንደሚሳተፉት አካላት ማንነት (ግለሰብ እና ድርጅቶች) ለፌደራሉ መንግስት እና ለክልል የግብር መ/ቤቶች የሚከፈል ይሆናል። ካፒታል ጌይን ታክስን በተመለከትም እ.ኤ.አ በ2004 የወጣው የናይጄሪያ የካፒታል ጌይን አክት መሰረት ጠበቆች ንብረት ሲያስተላለፉና ሲቀበሉ (በተለይ በመሬትና ሕንፃ) የካፒታል ጌይን ግብር እንዲከፍሉ ይጠበቃል።

የወጪ አያያዝ እና የእርጅና ተቀናሽን በተመለከተም የግለሰብ ግብር ከፋይ ጠበቆችም ሆኑ ግብር ከፋይ የጥብቅና ድርጅት capital allowance መጠየቅ የሚችሉ ናቸው። ማናቸውም ከስራቸው ጋር የተያያዘ ወጪዎቻቸውም /ለግል ወጪን ሳይጨምር/ ከታክስ በፊት ተቀናሽ ነው። የእርጅና ቅናሽም Depreciation Cost በተመለከተ በተመሳሳይ ከተሽከርካሪዎቻቸው፤ ከቢሮ/ግንባታ፤ ከማሽነሪና ቁሳቁሶች እና የመሳሰሉት ላይ እየተሰሉ ከታክስ ውሳኔ በፊት ተቀናናሽ የሚሆኑ ናቸው።

2.4.2. ኬንያ፤

ጎረቤት ሀገር ኬንያ በተመሳሳይ በምስራቅ አፍሪካ በንጽጽር ያደገ የህግ አገልግሎት የሚሰጥባት ሀገር ስትሆን የኬንያ ሎው ሶሳይቲ በሀገሪቱ ጠንካራ እንቅስቃሴ ያደርጋል። የህግ ማእቀፎችን በተመለከተ ከህገመንግስቱ በመለስ እ.ኤ.አ 2013 የወጣው የኬንያ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ፤ የገቢ ግብር ህግ (Cap 470)፤ የኤክሳይስ ታክስ ህግ የሚጠቀሱ ናቸው።

ተቀጣሪ ጠበቆችን በተመለከተ የግብር ክፍያው በየወሩ እንደሚከፈል የሚገመት ሆኖ እንደ ደረጃቸው Tax bracket ትልቁ 30 በመቶ ሆኖ የግቢ ግብር ግዴታቸውን የሚወጡ ይሆናል። ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በተመለከተም ማናቸውም የሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ በስራ ውሉ መሰረት በአሰሪው ዊዝሆልድ ይደረጋል። ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን በተመለከተ በኬንያ ከ 5 ሚሊዮን ሽልንግ በላይ አመታዊ ግብይት

የሚያከናውን ሰው ለቫት የመመዝገብ ግዴታ አለበት። የኬንያ የታክስ ባለስልጣን ቫት ከሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ 16 በመቶ ታክስ ይሰበስባል። ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው። ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የታክስ ግዴታዎችን በተመለከተ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ግዴታ አለባቸው።

ከወጭ አያያዝ ጋር በተያያዘ ከኢንተርቴይንመንት ወጭ ጀምሮ በርካታ ወጭዎቻቸው ተቀናሽ የሚሆኑና ግብር የማይጣልባቸው ናቸው። የግብር ስርአቱን ፍትሃዊና ተዓማኒ ለማድረግ በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል። እ.ኤ.አ ከ1995 በፊት በኬንያ የነበረው የግብር ስርአት የተበታተነ፤ ወጥነት የሌለው ደካማ የነበረ በመሆኑ ይታማል። ከ1995 ጀምሮ Kenya Revenue Authority KRA ተቋቁሞ የግብር ስርአቱን ፍትሃዊነት፤ ወጥነት፤ ግልጽነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መዋቅሮችን ዘርግቷል። ከነዚህም በግብር ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች የይግባኝ መብታቸውን ሳይጠቀሙ ግብር እንዲከፍሉ ያለመገደድን የሚከለክለውን ህግ ከማሻሻል ጀምሮ በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል።

2.4.3. ታንዛኒያ እና ሩዋንዳ፤

በታንዛንያና ሩዋንዳ ያለው የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የታክስ አከፋፈል ስርአት በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ነው። ጠበቆች ቀጥተኛ የሆኑና ያልሆኑ የግብር ግዴታዎች አሉባቸው። የታንዛኒያ እና የሩዋንዳ የታክስ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ቫት ከሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበስባሉ፡ ፡ በሁለቱም ሀገራት የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠኑ 16% ነው።

ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የታክስ ግዴታዎችን በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ግዴታ አለባቸው። የተወሰኑትን ብንመለከት ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በ7 ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት። የፕሮፌሽናል ውል የዊዝ ሆልዲንግ ከሚከፈልባቸው ዘርፎች አንዱ ነው። ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በታንዛንያ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል።

1ኛ/ Final ዊዝሆልዲንግ ታክስ- here the withholdee cannot claim tax credit when calculating the income tax payable for a year of income

2ኛ/ Non-final ዊዝሆልዲንግ ታክስ- the withholdee is entitled for tax credit and amount equal to the tax treated as paid for the year of income in which the amount is derived. በታንዛኒያ የዊዝ ሆልዲንግ ታክስ መጠን ትንሹ 5 በመቶ ሲሆን በተለይም የታንዛኒያ ነዋሪ ላልሆኑ እስከ 15 በመቶ ይደርሳል። በታንዛንያ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ ሲሆን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የታክስ ግዴታዎችን በተመለከተ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ግዴታ አለባቸው። ቫትን በተመለከተ በታንዛኒያ እና በሩዋንዳ የህግ አገልግሎትን ጨምሮ የቫት መጠኑ የግብይቱን 16 በመቶ ነው።

ከወጭ አያያዝ ጋር በተያያዘ ከኢንተርቴይመንት ወጭ ጀምሮ በርካታ ወጭዎቻቸው ተቀናሽ የሚሆኑና ግብር የማይጣልባቸው ሲሆኑ በታንዛኒያ የኢንተርቴይመንት ወጪ ተቀባይነት የሚኖረው ጣራ/ገደብ ተቀምጦለት ነው። በዚህም ከተቀመጠው በላይ የተጋነኑ የመዝናኛ/መስተንግድአ ወጪዎች ተቀናሽ የማይደረጉበት አሰራር መሆኑን ለመመልከት ተችሏል።

2.4.4. ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፤

በአሜሪካን ሀገር የህግ ስረዓት የጠበቆች የታክስ ግዴታን በተመለከተ፤ በአሜሪካን ሀገር በወሰድናቸው የተወሰኑ ግዛቶች ልምድ ጠበቆች በመሰረቱ ሁለት አይነት Compliance ግዴታ አለባቸው። የመጀመሪያው Ethical Standards አንጻር ያለባቸው ግዴታ ሲሆን ሌላኛው በፌደራሉ የታክስ ባለስልጣን IRS በኩል ያሉባቸው ግዴታዎች ናቸው። በዚህም የስነምግባር ኮድ Ethics & Professional requirements የሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች ውስጥ ከአደራ ሂሳብ ጋር ተያይዞ ያለው ዋነኛው ነው። በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ላይ ለሚኖረው የቁጥጥር ስርአት አንዱ ማሳያ ሲሆን ጠበቆች ከደንበኞቻቸው ጋር ለሚኖራቸው ግብይት ተገቢውን ሰነድ እንዲይዙ መስፈርት ያስቀምጣል።

የአሜሪካኑ የፌደራል ታክስ ባለስልጣን መ/ቤት በበኩሉ በየበጀት አመቱ የጠበቆችን ሂሳብ አዲት አይደርግም፤ በዚህም ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች መዝገባቸውን እንዲያሳዩ የሚጠልባቸው ግዴታ የለም። ሆኖም አይ አር ኤስ በዘፈቀደ/በድንገት በሚመርጣቸው ላይ የኦዲት ምርመራ ሊደረግ እንደሚችል የዩናይትድ ስቴትስ የታክስ አስተዳደር ልምድ ያሳያል። ሌላው ልንመለከተው የሚገባ ጠቃሚ ጉዳይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የሚመለከተው ነው። ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች የምንላቸው VAT, ToT, Excise tax የመሳሰሉት ሲሆኑ በዩናትድ ስቴትስ የታክስ አስተዳደር የህግ አገልግሎት ላይ ምንም አይነት ቀጥተኛ ያልሆኑ

ታክሶች አይጣልም። በአሜሪካን የህግ ስርዓት ሌላው እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል አሰራር የደንበኞች የአደራ ሂሳብ አፈጻጸምን የሚመለከተው የህጉ ክፍል ነው። ጠበቆች ሪቴይን ከሚደረገው ክፍያ ውስጥ በተሰራው ስራ ልክ እየተቀነሰ ወደ አካውንታቸው የሚገባ ይሆናል። ይህም በየክፍለ ሀገሩ የጠበቆች ማህበር ክትትል ይደረግበታል።

በሌላ በኩል ዩናይትድ ስቴትስ የኮመን ሎው ስርአት ተከታይ ሀገር ነች። አብዛኞቹ ስቴቶችም በመሰረታዊነት ተቀራራቢ የታክስ አስተዳደር ስርአት አላቸው። በተለየ ሁኔታ ሊታይ ከቻለ ሉዚያና የተባለው ግዛት ነው። ይህም የሲቪል ሎው ስርአትን ስለሚከተል ቀደም ብለው ከተጠቀሱት የአውሮፓ ሀገራት ተቀራራቢ የሆነ አሰራርን የሚተገብር ሆኖ ይገኛል። ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የፌደራል ስርአት ከሚከተሉ ሀገሮች አንዷ ነች። በዚህም ከአንድ ስቴት ወደ ሌላኛው ልዩነቶች ቢኖሩም መሰረታዊ የሚባሉ ባለመሆናቸው ከላይ ለማሳያ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ጥናት ሌሎች ክፍለ ግዛቶችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

2.4.5. ዮናይትድ ኪንግደም፤ አይርላንድ እና ቱርክ፤

በዩናይትድና ኬንግደምና በአየርላንድ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የመሰብሰብ ግዴታ አለባቸው። በአየርላንድ የሕግ አገልግሎት የተጨማሪ እሴት ታክስ የክፍያ መጠን እስታንዳርድ ሬት የሚሉ ላይ የሚመደብ ሲሆን፤ ይኸውም ከ20 እስከ 23 በመቶ የሚደርስ ነው። በሌላ በኩል ለተመረጡ የአገልግሎት ዘርፎች ከላይ ከተጠቀሰው ከመደበኛው ሕዳግ የቀነሰ ምጣኔ (reduced rate) የሚባል የተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ ያላቸው ሲሆን የእነዚህም ተፈፃሚነት ለሕብረተሰብ አስፈላጊ በሆኑ አገልግሎቶች ላይ ተፈፀሚ የሚሆኑ ናቸው። በተጨማሪም በአብዛኛዎች የአውሮፖ አገራት Partial Exemption እና የዜሮ ምጣኔ ታክስ አሰራሮች እንደሕክምና ባሉ ለሕብረተሰብ መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑበት አሰራት እንዳለ ለማየት ተችሏል።

ዩናይትድ ኪንግደምን ጨምሮ በርካቶቹ የአውሮፖ አገራት የፋይናንስ እና የኢንሹራንስ፤ የትምሕርትና ሥልጠና እንዲሁም ሕክምናን ጨምሮ መሰል ዘርፎችን ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ ግዴታዎች ነፃ አድርገው

ይገኛሉ። እንደ አየርላንድ ያሉ የአውሮፖ አገራት ደግሞ የአንድን የሙያ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን የተወሰኑትን የአገልግሎት ዓይነቶች በመለየት ከታክስ ግዴታ ነፃ ያደርጋሉ።

ለምሳሌ፤ ከሕክምና ዘርፎች አኩፓንቸር፤ የአመጋገብ ሕክምና፤ ማሳጅ፤የጭንቀት ሕክምና ሙሉ ለሙሉ ከታክስ ነፃ ሳይደረጉ በቅናሽ የታክስ ምጣኔ ህዳግ የሚስተናገዱበት አሰራር ይገኝበታል።

በተመሳሳይ በአየርላንድ በእድሜ ገደብ (ከ65 አመት በላይ ያሉ ዜጎች ግብር ግዴታ አይኖርባቸውም)፤ በመነሻ የገቢ መጠን (ከዚህ በታች ገቢ ያለው...)፤ በጋብቻ ሁኔታ (ያላገቡ) እና በመሳሰሉት ዜጎች ከታክስ ግዴታ ነጻ የሚደረጉበት የተለያየ አሰራር ስለመኖሩ ተመልክተናል።

የፍርድ ቤት ውሳኔዎችንና Case laws በተወሰነ መልኩ ለመከለስ ጥረት የተደረገ ሲሆን ከነዚህም የአውሮፓ ሕብረት ኮርት ኦፍ ጀስቲስ /European Court of Justice/ ከታክስ ነፃ የማድረግ አተገባበሮች በጠባቡ ሊተረጉሙ እንደሚገባ ውሳኔ የሰጠበት የፍርድ መዝገብ ይገኝበታል። ለዚህም የአውሮፓ ሕብረት ኮርት ኦፍ ጀስቲስ መሰረት ያደረገው ይህ አሰራር ከመደበኛው የታክስ አሰራር በልዩ ሁኔታ የሚተገበር exception በመሆኑ ነው። ቱርክን በተመለከተ ሌላኛዋ በጥናቱ ለመዳሰስ የተሞከረች አውሮፓ ህብረት አባል ሀገር ስትሆን በቱርክ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ቀጥተኛ ለሆኑና ቀጥተኛ ላልሆኑ የታክስ ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል። እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ በቱርክ ሀገር በህግ አገልግሎት ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን 18 በመቶ ነበር።

በሀገሪቱ እየተተገበረ ባለው የ Judicial Reform Strategy ጋር በተያያዘ ለዜጎች የህግ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት ሲባል ቀጥተኛ ባልሆነው የታክስ መጠን ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። የቱርክ የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር አብድልሃሚት ጉል በቲዊተር ገጻቸው እንዳሰፈሩት በተወሰኑ የህግ አገልግሎቶች ላይ መከፈል የሚኖርበት የቫት መጠን ከ18 % ወደ 8 % እንዲቀነስ መደረጉን ገልጸው ይህም የህግ አገልግሎት ተደራሽነትን ለመስፋት ያግዛል ብለዋል። የቱርኩ ፕሬዝደንት ረሲብ ጣይብ ኤርዶጋንም "የፕሬዝደንታዊ ውሳኔ ቁጥር 4862" ፈርመው ያጸደቁ ሲሆን ይህውም "With Presidents decision no. 4862 published in the official gazzete dates 26/11/2021 and numbered 31671`` በሚል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከኖቬምበር 26 ቀን 2021 ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል።

2.4.6. የጥብቅና ድርጅቶች እና የሽሪች የገቢ ግብርን በተመለከተ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ

ሃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማህበራት የሽርክና እና የድርጅት (ማህበር) ባህሪያት ያላቸው የንግድ ተቋማት ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች ኢትዮጵያን ጨምሮ እንደ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ህንድ እና ሲንጋፖር ባሉ በብዙ አገሮች በሕግ ድርጅቶች እና በሌሎች ሙያዊ አገልግሎት ድርጅቶች በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላሉ። ነገር ግን፣ የእነዚህ ድርጅቶችን የግብር አከፋፈል እንደየሀገሩ ይለያያል።

በኃላ/የተ/የሽርክና ማህበራት በሆኑ የጥብቅና ድርጅቶች ግብር አወሳሰን ውስጥ ካሉት ዋና ጉዳዮች አንዱ ለግብር ዓላማ ሲባል እነዚህ ድርጅቶች እንደ አስተላላፊ (transparent) ወይም አስተላላፊ ያልሆነ (opaque) ታክስ ከፋይ ተደርገው ይወሰዳሉ። አስተላላፊ የሆነ አካል (transparent entity) በድርጅት ደረጃ ታክስ የማይከፈልበት ነገር ግን ገቢውን እና ወጪውን ለአባላቱ በማለፍ በሽሪኮች ላይ ታክስ የሚከፈልበት ነው። አስተላላፊ ያልሆነ አካል (opaque entity) በድርጅቱ ደረጃ ታክስ የሚጣልበት ሲሆን ከታክስ በኋላ የሚያገኘውን ትርፍ ለአባላቱ ማከፋፈል ይችላል፤ ሆኖም ለአባላቱ የተከፋፈለው ትርፍ እንደየሀገሩ ተጨማሪ ቀረጥ ሊጣልበት ወይም ላይጣልበት ይችላል።

ሀ) ሽሪኮች እንደግለሰብ ነጋዴ ከማህበሩ ትርፍ ክፍፍል ላይ የገቢ ግብር የሚከፍሉበት አሰራር (Pass – Through Taxation/ Taxation of Tansparent Entities)

በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ውስጥ አንድ የጥብቅና ድርጅት ለፌዴራል የገቢ ታክስ ዓላማዎች እንደ አስተላላፊ አካል (transparent entity) ይወሰዳል። ይህም ማለት ድርጅቱ የግብር አመቱን ገቢ፣ ወጪ እና ትርፍ በሚያሳውቅ ወቅት የእያንዳንዱን ሽሪክ (አባል) ገቢ፣ ወጪ እና ትርፍ አብሮ ያሳውቃል። እነዚህ ሽሪኮችም በግላቸው የሚጠበቅባቸውን ግብር ሲከፍል ከድርጅቱ ያገኙት ገቢ ላይም አብረው አመታዊ ግብራቸውን ይከፍላሉ። በዚህ መሰረት የገቢ ግብር የሚከፍሉት ግለሰብ አባላቱ እንጂ የጥብቅና ድርጅቱ አይደለም። ሌላው ጠቃሚ ነጥብ የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የባንክ አካውንትን የሚመለከተው ክፍል ነው። ይህንንም በተመለከተ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የባንክ ሂሳባቸውን ከግል አካውንታቸው ለይተው መያዝ የሚጠበቅባቸው ይሆናል። ተቀላቅለው ቢገኙ እንደሁኔታው በባሩ ፊት ቀርቦ መልስ ከመስጠት ጀምሮ እስከ እገዳ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድ የሚችልበት አሰራር አለ።

ለ) የአባላቱ የትርፍ ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የሽርክና ማህበራት ገቢ ግብር የሚከፍሉበትና አሰራር

የጥብቅና ድርጅቶች አስተላላፊ እንዳልሆነ አካል **(opaque entity)** ተወስዶ ግብር ሲጣልበት ድርጅቱ በራሱ የድርጅት ትርፍ የሚከፍል ይሆናል። ሸሪኮችን በተመለከተ ከትርፍ ክፍፍል የሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ግብር በሸሪኮች ላይ ተግባራዊ ሊደረግም ላይደረግም ይችላል።

በድርጅትም በሸሪክም ላይ ግብር የሚጥሉ ሀገራት አሰራር፦

በኬንያ በሚሰሩ ድርጅቶች ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን ዝቅተኛው 30 በመቶ ነው። ይህ አይነቱ ታክስ በኬንያ ቢያንስ በአመት ሁለት ግዜ የሚከፈል ነው። በድርሻ ክፍፍል ለሸሪኮች በሚከፈልበት ወቅት ከሚደርሳቸው መጠን ላይ 5 በመቶ ታክስ ይከፈልበታል።

ይህ አሰራር አንድን ጠበቃ ሙሉ ጊዜውንና ጉልበቱን ተጠቅሞ በሰጠው የሙያ አገልግሎት ሁለት ጊዜ ግብር እንዲከፍል ያስገድደዋል። ከግብር አስተዳደር ምቹነት አንፃር ይህ አሰራር ሲታይ አመቺ አይደለም። የጥብቅና ድርጅቱ ከሚከፍለው ግብር በተጨማሪ አባላቱም የትርፍ ክፍፍል ግብር በሚከፍሉ ጊዜ በአንዳንድ ሀገራት የስራው በግል ያወጡት ወጪም እንዲያዝላቸው ይደረጋል። ይህም ወጪዎችን የድርጅት ወጪዎች እና የአባላት ወጪዎች ተብሎ እንዲከፈሉ ያደርጋል።

በድርጅትም ላይ ብቻ ግብር የሚጥሉ ሀገራት አሰራር፦

በህንድ የሽርክና ማህበራት ከሚያገኙት ትርፍ 30% የገቢ ግብር ቢከፍሉም አባላት (ሸሪኮች) ግን ከትርፍ ክፍፍል የተገኘ ገቢ ላይ ግብር እንዲከፍሉ አይደረግም። የሽርክና ማህበራት ካገኙት ትርፍ ላይ ተቀናሽ ወጪዎችን በመቀነስ ከትርፋቸው የገቢ ግብር ይከፍላሉ። ከዚያም አስቀጥሎ ከግብር በኋላ የተረፈው ገቢ በአባላት መካከል ይከፋፈላል። በዚህ አሰራር የሂሳብ መዝገብ የመያዝ፣ ወጪዎችን የመመዝገብ እና የመቀነስ እንዲሁም ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የጥብቅና ድርጅቱ ብቻ ነው። ስለሆነም ግብር አስተዳደር ምቹ እና ተመራጭ አሰራር ነው።

2.5. የክልሎች ልምድ

በክፍል አንድ የጥናቱ ስልት ላይ እንደተገለጸዉ በጥናቱ ዉስጥ የክልሎችን ልምድ ለመዳሰስ ጥረት የተደረገ ሲሆን የፌደራል ጥብቅና ፍቃድ ያላቸዉ ጠበቆች ብዛት አንጻር የአማራ እና የኦሮሚያ ክልል ልምዶችን ለማየት ተሞክሯል። በአማራ ክልል ያለዉን ተሞክሮ ለማየት መረጃ ለመሰብሰብ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎችን እና መጠይቆችን ለሚመለከታቸዉ አካላት ብናደርስም ምላሽ ማግኘት ስላልተቻለ የኦሮሚያ ክልል ልምድን ብቻ በመቃኘት የክልሉ ልምድ ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

በኦሮሚያ ክልል ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 182/2005 መሰረት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ማለት ክፍያ ለማግኘት ወይም በማግኘት ወይም ያለክፍያ ደምበኛን በመወከል ፍርድ ቤት ቀርቦ መከራከርና ማንኛዉንም የህግ ምክር አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ዉሎችን ወይም ፍርድ ቤት ሊቀርቡ የሚችሉ የተለያዩ ሰነዶችን ወይም አንድን ድርጅት የሚያቋቁም የመመስረቻ፣ የማሻሻያ ወይም የማፍረሻ ፅሑፍ ማዘጋጀትን የሚያካትት እንደሆነ ተደንግጓል። የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ (በበፊት ስያሜው የፍትህ ቢሮ) ለጠበቆች ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድ፣ የመሰረዝና የማስተዳደር ስልጣን አለው። አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት በሕግ የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች አሟልቶ በመገኘት ከቢሮው የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት እንደሚችል ተመልክቷል። የክልሉ ጠበቆች ማህበር ፕሬዝዳንትን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ያገኘነዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ በክልሉ ለጥብቅና አገልግሎት የሚከፈል ሁለት አይነት የአከፋፈል ስርዓት እንዳለ አንስተዋል። ይኸዉም አንድ ጠበቃ ለወንጀል ጉዳይ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር እንዲሁም ለፍትሀብሄር ጉዳይ የጉዳዩን 15 ፐርሰንት መጠን ማስከፈል እንደሚችል(ከዚህ የበለጠ ክፍያ መቀበል እንደማይችል) ገልጸዉልናል።

በዚህ አዋጅ መሰረት በጥብቅና ሙያ አገልግሎት የተሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ካሉበት ግዴታዎች ውስጥ አሁን ከሚደረገው ጥናት ጋር የሚያያዘው የገቢ ግብርን ጨምሮ ከፍቃድ አሰጣጥና እድሳት የሚመለከቱ ሌሎች አስተዳደራዊ ክፍያዎችን መክፈል ይጠበቅበታል።

2.5.1. <u>አስተዳደራዊ ክፍያ</u>

በክልሉ የጥብቅና ፍቃድ አውጥተው የሚሰሩ ጠበቆች በክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለሚያገኙት አስተዳደራዊ አገልግሎት ስለሚከፍሉት ክፍያ በተመለከተ በደንብ ቁጥር 177/2008 ከአንቀጽ 18 እስከ 27 ያሉት ዝርዝር ድንጋጌዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃለው ቀርበዋል። ጠበቆች ከክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ለሚያገኙት አስተዳደራዊ አገልግሎቶች የሚከፍሉት አስተዳደራዊ ክፍያ የግብር ክፍያን እንደማያካትት ወይም እንደማይተካ በደንቡ አንቀጽ 46 ላይ ተመልክቷል።

የአገልግሎት ዓይነት	**የክፍያ መጠን**
የአንደኛ ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት	1000(አንድ ሺ)ብር
ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት	500(አምስት መቶ)ብር
የድርጅት ጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት	2000(ሁለት ሺ)ብር
ልዩ የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት	ክፍያ አይጠየቅም
የአንደኛ ደረጃ ጥብቅና ፍቃድ እድሳት	500(አምስት መቶ)ብር
የሁለተኛ ደረጃ ጥብቅና ፍቃድ እድሳት	300(ሶስት መቶ) ብር
የድርጅት ጥብቅና ፍቃድ እድሳት	1000(አንድ ሺ)ብር
የልዩ ጥብቅና ፍቃድ እድሳት	ክፍያ አይጠየቅም
ከሁለተኛ ደረጃ ጥብቅና ወደ አንደኛ ደረጃ ጥብቅና ፍቃድ ለማደግ ወይም ለማሻሻል	800(ስምንት መቶ)ብር
በአደራ የተቀመጠ ፈቃድ መልሶ ለመውሰድ	200(ሁለት መቶ)ብር
ታግዶ የነበረ ፍቃድ መልሶ ለመውሰድ	300(ሶስት መቶ)ብር
የተሰረዘ የጥብቅና ፈቃድ መልሶ ለመውሰድ	500(አምስት መቶ)ብር
ለፍቃድ ፈተና ለመቀመጥ መመዝገቢያ	200(ሁለት መቶ)ብር
የጥብቅና ድርጅት ለማስመዘገብና ለማረጋገጥ	250(ሁለት መቶ ሃምሳ)ብር
የጥብቅና ድርጅት መመስረቻ ጽሁፍ ለማሻሻል	300(ሶስት መቶ)ብር
የጥብቅና ፍቃድ የማሳደሻ ገዜ ያሳላፈ	• እስከ ሁለት ወር ድረስ ለእያንዳንዱ ወር 200(ሁለት መቶ) ብር መቀጫ • ከሁለት ወር በላይ በበቂ ምክነያት ሳያሳድስ ቢቀር የበጀት አመቱ እስኪያልቅ በየወሩ 400(አራት መቶ) ብር እንዲከፍል ይደረጋል

2.5.2. <u>የግብር ክፍያ</u>

የክልሉ ጠበቆች ማህበር ፕሬዝዳንት እንደገለጹት እስከ 2008 ዓ.ም. ድረስ ጠበቆች የቁርጥ ግብር ይከፍሉ እንደነበር በዚህም 1ኛ ደረጃ ጠበቆች 2800 ብር 2ኛ ደረጃ ጠበቆች 2350 ብር ይከፍሉ ነበር፡፡ እነዚህ ግብሮች ይሰበሰቡ የነበረዉም በክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ በኩል ነበር፡፡ይሁንና ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ገቢዉን መሰብሰብ የጀመረ ሲሆን ከዚህ ግዜ ጀምሮ በቁርጥ ወይም በደረሰኝ ግብር የሚከፍሉ ጠበቆች እንዲለዩ ተደርጓል፤ እንዲሁም ጠበቆች ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንዲሰበስቡ ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል፡ ፡

ለጠበቆችና የሕግ ጉዳዮች ጸሃፊ ፍቃድ ለመስጠትና ለማስተዳደር የወጣው አዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 28 መሰረት ግብር አለመክፈል ለፍቃድ መሰረዝ እንደሚያበቃ ተደንግጓል። በተጨማሪም ማንኛውም የጥብቅና ፈቃድ የማሳደስ ጥያቄ ሲቀርብ የዚያን ዓመት ግብር የከፈለበት ደረሰኝ ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 33(4)(ሀ) ላይ ተደንግጓል። በክልሉ የጥብቅና ፍቃድ የሚታደሰው በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሀምሌ 1 እስከ 30 ባለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው። የነሃሴና የመስከረም ወር በእያንዳንዱ ወር ሁለት ሁለት መቶ ብር በቅጣት የሚታደስ መሆኑ በሕጉ ተመልክቷል። ከሁለት ወር በኋላ በበቂ ምክነያት ፍቃድ ሳያሳድስ የቀረ ጠበቃ የበጀት ዓመቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየወሩ አራት አራት መቶ ብር እንዲከፍል ተደርጎ ፍቃዱ እንደሚታደስ ተደነግጓል።

የክልሉ ጠበቆች ግብር የሚከፍሉት በክልሉ አደረጃጀት መሰረት በሚቀርባቸው የክልል ገቢዎች ባለስልጣን መስሪያ-ቤት እንደሆነ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

2.5.3. የጥብቅና ገቢ ግብር አመዳደብ

እንደፌደራሉ የገቢ ግብር አዋጅ ሁሉ የክልሉ ገቢ ግብር አመዳደብ ሰንጠረዥ ተመሳሳይ ነው። ይህም ሠንጠረዥ "ሀ" ከሕንጻ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ግብር፣ ሠንጠረዥ "ለ" በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ግብር፣ ሠንጠረዥ "ሐ" በንግድ ስራ ላይ የሚጣል ግብር፣ ሰኝጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች እና ሰንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር በጻ የሆኑ ገቢዎች የሚሉት ናቸው።[37] በዚህ አመዳደብ መሰረት ድርጅቶች 30% የንግድ ስራ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን ግለሰቦች ደግሞ ገቢያቸውን መሰረት በማድረግ ከ10% እስከ 35% በሚደርስ ምጣኔ

[37] የኦሮሚያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 202/2009 አንቀጽ 9

እንዲከፍሉ በሕጉ ተመልክቷል።[38] ምንም እንኳን ይህ ሰንጠረዥ ከንግድ በሚገኝ ገቢ ላይ ስለሚጣል ግብር የሚመለከት ቢሆንም እና የጥብቅና አገልግሎት እንደ ንግድ ስራ የማይቆጠር ቢሆንም ከጥብቅና አገልግሎት በመስጠት የሚገኝ ገቢ ግብር በሰንጠረዥ "ሐ" ስር የሚመደብ እንደሆነ ከክልሉ ገቢዎች ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።[39]

2.5.4. ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ

ከግብር ተመን አወሳሰን እና አከፋፈል ጋር በተያያዘ ግብር ከፋዮች በሶስት የግብር አከፋፈል ደረጃዎች የሚመደቡ ስለመሆኑ በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ላይ ተመልክቷል።[40] የመጀመሪያው የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ሲሆኑ እነርሱም ድርጅት ወይም ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው አንድ ሚሊዮን ብር ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው የሚያካትት ነው። ሁለተኛው በደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ስር የሚመደቡት ደግሞ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው አምስት መቶ ሺ ብር በላይ የሆነ እና አንድ ሚሊዮን ብር ገቢ ያላቸውን እንደሚያካትት ተመልክቷል። ሶስተኛው የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ሲሆኑ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው እስከ አምስት መቶ ሺ ብር የሆኑትን የሚያካትት ነው።

በዚህ አመዳደብ መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የሚገደዱት የደረጃ "ሀ" እና የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች እንደሆኑ በሕጉ ላይ የተመለከተ ሲሆን የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸውን የሚያሳይ ወይም ሌላ አስፈላጊ መዝገብ ሊይዙ እንደሚችሉ ተመላክቷል።[41] ከዚህ አንጻር የጠበቆችም የደረጃ አወሳሰን እንደማንኛውም ግብር ከፋይ የሚያገኙትን ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መሰረት በማድረግ የሚወሰን እንደሆነ ከክልሉ ገቢዎች ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።[42] በክልሉ እስካሁን ምን ያህል ጠበቆች የደረጃ "ሀ" እና ደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች እንዳሉ በውል ቁጥራቸውን ለማወቅ አዳጋች በመሆኑ መረጃውን ማግኘት አልተቻለም። ከደረጃ አመዳደብ ጋር በተያያዘ የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቀውን ግብር ወይም የሚያገኘውን ሌላ መረጃ

[38] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20
[39] ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ታክስ አስተዳደርና ክትትል እና ከታክስ አወሳሰን የተገኘ መረጃ
[40] የኦሮሚያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 202/2009 አንቀጽ 5

[41] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 78(1)፣(2)
[42] ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ታክስ አስተዳደርና ክትትል እና ከታክስ አወሳሰን የተገኘ መረጃ

መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን እንደሚወስን በሕጉ ተደንግጓል።[43] ይሁን እንጂ የጠበቆችን ደረጃ ለመወሰን ወይም ለማሻሻል የሚያገኙትን ትክክለኛ ገቢ ለማወቅ አደጋች እንደሆነ ከቢሮው የተገኘው መረጃ ያሳያል።[44] ምክነያቱም ጠበቃ ነጋዴ ስላልሆነ የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ አይገደድም የሚል እምነት በአብዛኛው ጠበቃ በመኖሩና የሂሳብ መዝገብ ስለማይዙ ትክክለኛውን ገቢ ለማወቅ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገለጻል። በሌላ በኩል ስለገቢያቸው ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከፍ/ቤት እና ከተከፋይ ላይ ቀንሰው የመያዝ ግዴታ ካለባቸው ድርጅቶች የሚገኝ መረጃ ቢኖርም ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ የተሟላ መረጃ ማግኘት እንደማይቻል ይገለጻል። በመሆኑም ደረጃቸው የሚወሰነው ጠበቆቹ በሚያቀርቡት ዓመታዊ ገቢ ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህ በክልሉ የሚገኘው አብዛኛው ጠበቃ በደረጃ "ሐ" ግብር ካፋይ ስር የሚመደብ በመሆኑ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 202/2010 ሰንጠረዥ ላይ ለደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በተቀመጠው ስሌት መሰረት ነው። ይሁንና የክልሉ ጠበቆች ፕሬዝዳንት ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚገደዱ ቢሆንም በአንጻሩ ጠበቆች ወጪዎቻቸዉ እንዲያዙላቸዉ ቢጠይቁም ተቀባይነት እያገኙ እንዳልሆነ አንስተዋል።

2.5.5. ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ አከፋፈል

እንደሚታወቀው ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ ዓይነቶች ውስጥ የተጨማሪ ዕሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ ዋንኛ ተጠቃሾች ናቸው። ከዚህ አንጻር ክልሉ ያራሱ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ የሌለው በመሆኑ በፌደራል መንግስቱ የወጣውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ማሻሻያዎቹን የሚያስፈጽም ሲሆን ክልሉ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አውጥቶ ስራ ላይ አውሏል።

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በተመለከተ ዓመታዊ የሽያጭ መጠናቸው ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ መመዝገብ እንዳለባቸውና በሚያከናውኑት እያንዳንዱ ግብይት ክፍያ ላይ 15% ገዢው ላይ በመጨመር ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ገቢ የማድረግ ግዴታ በሕጉ ተጥሎባቸዋል።[45] በዚህ ሕግ መሰረት ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ግዴታ ነጻ የተደረጉ እንደትምህርት፣ ጤናና የፋይናንስ አገልግሎት ቢኖሩም የጥብቅና አገልግሎት በዚህ ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም። በዚህ ረገድ ከክልሉ ቢሮ

[43] የኦሮሚያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 202/2009 አንቀጽ 78(1)፣(2)
[44] ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ታክስ አስተዳደርና ክትትል እና ከታክስ አወሳሰን የተገኘ መረጃ
[45] የተጨ.ዕ.ታ. አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ7፣

ያገኘነው መረጃ የሚያሳየው ጠበቆች ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው በሕጉ ላይ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን አስካሚላ ድረስ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ የመመዝገብና የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው ግንዛቤ መኖሩን ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጂ በክልሉ ምን ያህል ጠበቆች ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ የተመዘገቡና እየከፈሉ እንደሆኑ መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም። ይልቁንም የክልሉ አብዛኛው ጠበቃ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ በመሆናቸው የሚያሳውቁት ዓመታዊ ገቢ ከአምስት መቶ ሺ ብር በታች መሆኑን ያሳያል።

ከተርን ኦቨር ታክስ ጋር በተያያዘ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ላይ እንደፌደራል ተ.እ.ታ. አዋጁ አገልግሎት በመስጠት በሚገኝ ገቢ ላይ 10% ታክስ እንደሚከፈልበት ተመልክቷል።[46] በዚሁ መሰረት ገቢያቸው ከአምስት መቶ ሺ ብር በታች በመሆኑ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ሰባት ወይም ሌላ አግባብነት ባለው መመሪያ መሰረት ነጻ ከተደረጉ ስራዎች ውስጥ እስካልተካተቱ ድረስ የተርን ኦቨር ታክስ እንደሚከፍሉ ተደንግጓል። የታክስ መጠን አወሳሰን በተመለከተ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች በሚያቀርቡት የሂሳብ መዝገብ መሰረት ከጠቅላላ ገቢያቸው ላይ የሚሰላ ሲሆን የደረጃ "ሐ" ግብረ ከፋዮች ሆነው የሂሳብ መዝገብ የማይዙ ከሆነ ለገቢ ግብር ዓላማ ዓመታዊ ገቢያቸው ተብሎ የቀረበው መጠን ላይ በቁርጥ እንደሚሰላ ተመልክቷል።[47] ከዚህ አንጻር በክልሉ በጥብቅና አገልግሎት የተሰማሩ ሰዎች በአብዛኛው የሂሳብ መዝገብ የማይዙ እና የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ በመሆናቸው ባሳወቁት ዓመታዊ ገቢ መሰረት ተ.እ.ታ. እንዲከፍሉ የሚደረግ መሆኑን ያገኘነው መረጃ ያሳያል።[48] ይሁን እንጂ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ የማይዙ ከመሆኑ አንጻርና ከሶስተኛ ወገን የሚገኘው መረጃ በቂ ባለመሆኑ ቢሮው ትክክለኛ ገቢያቸውን ለመወሰን እንደሚቸገር ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል።

2.5.6. ስለ ወጪ አያያዝ

የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የንግድ ሥራ ገቢ ነው የሚባለው ከንግድ ሥራ ከተገኘ ጠቅላላ የግብር ዓመቱ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱት ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ላይ እንደሆነ በክልሉ የገቢ አዋጅ ተመልክቷል።[49] ከዚህ ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረጉት ወጪዎች በንግድ ሥራው ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ

[46] የኦሮሚያ ክልል ተ.እ.ታ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 4(2)(ለ)፣ የፌደራል ተ.እ.ታ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀጽ 4(2)(ለ)
[47] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 13
[48] ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ታክስ አስተዳደርና ክትትል እና ከታክስ አወሳሰን የተገኘ መረጃ
[49] የኦሮሚያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 202/2009 አንቀጽ 21(1)


ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፣ የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ እና ሌሎች በአዋጁ መሰረት እንደተቀናሽ ሊያዙ የሚገቡ ወጪዎችን እንደሚያካትት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ማንኛውም ጠበቃ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝና ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎችን ማለትም የቢሮ ኪራይ፣ የሰራተኛ ወጪ፣ የጽህፈት መሳሪያዎችና የመሳሰሉት ወጪዎች በተቀናሽ የሚያዙለት እንደሆነ ከክልሉ ገቢዎች ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ ጠበቆች የሚጠቀሙት መኪና ኮድ ሁለት በመሆኑ ለነዳጅና ጥገና የሚያወጡት ወጪዎች አይያዝላቸውም። ይሁን እንጂ አብዛኛው ጠበቃ የሂሳብ መዝገብ የማይዝ በመሆኑና የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ በመሆኑ የግብር አከፋፈልና ወጪ አያያዝ ስሌት ጠበቃው በአጠቃላይ ካሳወቀው ዓመታዊ ገቢ 25% ብቻ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ ሲወሰድ ቀሪው 75% እንደወጪ የሚያዝበት አሰራር ተግበራዊ እንደሚደረግ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

ምእራፍ ሶስት

3. የጥናቱ ግኝት እና ትንተና

3.1. የጥብቅና አገልግሎት በገቢ ግብር አዋጅ ያለው አመዳደብ

ከላይ በምዕራፍ ሁለት እንደተተነተነው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የገቢ ግብር አመዳደብን በተመለከተ የገቢ ግብር በአምስት ሰንጠረዥ እንደሚከፈል ይደነግጋል።[50] እነዚህም ሰንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣ ሰንጠረዥ "ለ" ከሕንጻ ክራይ የሚገኝ ገቢ፣ ሰንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ፣ ሰንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች፣ እና ሰንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች ናቸው። የጥብቅና አገልግሎት ከእነዚህ ሰንጠረዦች የትኛው ውስጥ እንደሚወድቅ በግልፅ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም ሰንጠረዥ "ሐ" የንግድ ስራ ገቢን የሚመለከት ሲሆን የንግድ ስራ ገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ማንኛውም በተከታታይም ሆነ ለአጭር ግዜ ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ፣ የንግድ እና የሙያ ወይም ቮኬሽናል ስራን ያካትታል ተብሎ ተተርጉሟል።[51] በዚህ ክፍፍል መሰረት መላሾች ጠበቆች በተግባር በየትኛው ሰንጠረዥ ግብር እንደሚከፍሉ ተጠይቀው ከ75 በመቶ በላይ ተሳታፊዎች በሰንጠረዥ ሐ ያሉ ሲሆን የተቀሩት ሰንጠረዥ ለ እና ሰንጠረዥ መ መሰረት እንደሚከፍሉ ምላሽ ሰጥተዋል።




ምስል 1 የመላሾችን መልሶች በመቶኛ ያሳያል።

[50] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፣ አንቀፅ 8፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 104፣ ነሀሴ 2 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

[51] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 22 (2).

በዚህ ምላሽ መሰረት ቁጥራቸው ትንሽ ሚሆኑት በሰንጠረዥ ለ እና መ ስር እንደሚመደብ የገለጹ ቢሆንም ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ግን የጥብቅና አገልግሎት በሰንጠረዥ ሐ ስር የሚመደብ መሆኑን ነው። የሰንጠረዥ አመዳደቡ መሰረት የሚያደርገው ግብር የሚከፈልበት የገቢ ምንጭ ላይ ሲሆን በሰንጠረዥ "ለ" የሚመደበው ከሕንጻ ኪራይ የሚገኝ ገቢ በመሆኑ የጥብቅና አግልግሎት በመስጠት የሚገኝ ገቢ በዚህ ሰንጠረዥ ስር ሊመደብ አይችልም። በሰንጠረዥ "መ" ስር የሚጣለው ግብር የአንድ ግዜ ክፍያ የሆኑ ቴክኒካዊ ክፍያ፣ ሮያሊቲ፣ ወለድ የመሳሰሉ ገቢዎች ላይ የሚጣል ግብር ነው። በሌላ በኩል በሰንጠረዥ "ሐ" ስር የሚመደቡ የገቢ አይነቶች የተዘረዘሩ ሲሆን በእነዚህ ዝርዝር ውስጥ የጥብቅና አገልግሎት በግልጽ ባይካተትም በሰንጠረዥ "ሐ" ስር በግልጽ የንግድ ስራ ስለሚል እና ጥብቅና የንግድ ስራ ባይሆንም የሞያ አገልግትሎ በመሆኑ በሰንጠረዥ "ሐ" የሚስተናገድ የአገልግሎት ዘርፍ ነው።

በገቢ ግብር አዋጁ ሰንጠረዥ አመዳደብ መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ከጥብቅና ስራ ባህሪያት ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ተሳታፊዎች የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት 76 በመቶ በላይ መላሾች የግብር አመዳደቡ ከስራው ባህሪ ጋር ይጋጫል ብለው የመለሱ ሲሆን የተቀሩት አይጋጭም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።



ምስል 3 የመላሾችን መልስ በመቶኛ ያሳያል

ከጥብቅና አገልግሎት የሚገኝ ገቢ ሰንጠረዥ አመዳደብ ይጋጫል በሚል ምላሽ የሰጡት ተሳታፊዎች ምክንያታቸውን ሲጠቅሱ የሠንጠረዥ "ሐ" ስር የሚመደቡ በንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ (INCOME FROM BUSINESS) ስለመሆኑ የድንጋጌው ርዕስ ያለመክታል። ይሁን እንጂ የጥብቅና አገልግሎት እንደንግድ ስራ


የማይቆጠር ሆኖ እያለ በሰንጠረዥ ሐ ስር እንዲመደብ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው። የንግድ ሕጉ የጥብቅና አገልግሎት የንግድ ስራ እንደሆነ አያስቀምጥም። በተግባርም ጠበቆች በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ 980/2008[52] እና በንግድ የስራ መደብ መስጫ መመሪያ ቁጥር 17/2011 መሰረት የንግድ ምዝገባ[53] የማያደርጉና የንግድ ፍቃድ የማያወጡ ከመሆኑ አንጻር አገልግሎቱ እንደንግድ ስራ የማይቆጠር ስለመሆኑ ማሳያ ነው። በሌላ በኩል አዲስ የወጣው የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1249/2013 የጥብቅና ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት እንደንግድና ኢንቨስትመንት ስራ አያስቆጥረም የሚል ድንጋጌ ይዞ የመጣ በመሆኑ አገልግሎቱ የንግድ ስራ ስላለመሆኑ አመላካች ነው።[54] ከዚህ አንጻር የጥብቅና አገልግሎት በሰንጠረዥ ሐ ስር ከንግድ የሚገኙ ገቢዎች ስር መመደቡ የትርጉም ተፋልሶ አለው የሚል ነው፡ ፡ በመጠይቁም ሆነ በትኩረት ቡድን ውይይቱ የጥብቅና አገልግሎቱ ሰንጠረዥ አመዳደብ ይጋጫል በሚል አብዛኛው ምላሽ የተሰጠው በዚሁ አግባብ መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ጠበቆች በሰንጠረዥ ሐ ስር ግብር እንዲከፍሉ መደረጉ ለግብር ዓላማ እንጂ አንድን ስራ የንግድ ስራ ነው ወይም አይደለም የሚለው የሕጉ ዋና ዓላማ አለመሆኑ መረዳት ያስፈልጋል። ከመጠይቁ ተሳታፊዎች ውስጥ አንድ አራተኛ የሚሆኑት አመዳደቡ አይጋጭም በሚል የለመሱት ከዚህኛው ሃሳብ ጋር የሚስማሙ ይመስላል። በሌሎች ሕጎችና በገቢ ግብር አዋጁ መካከል የጥብቅና አገልግሎት አረዳድና ትርጉም ማጣጣሙ ተገቢ ነው።

የጥብቅና አገልግሎት በሰንጠረዥ ሐ መመደቡ ከስራው ባህሪ ጋር ይጋጫል ብለው የመለሱ ተሳታፊዎች በየትኛው ሰንጠረዥ መመደብ እንደሚገባው ለተጠየቁት ጥያቄ ከ85 በመቶ በላይ መላሾች የተለየ አመዳደብ ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን፣ 6 በመቶ ሰንጠረዥ ሀ፣ 2 በመቶ ሰንጠረዥ ለ፣ እና የተቀሩት 5 በመቶ የሆኑት ሰንጠረዥ ሐ ብለው መልሰዋል።

[52] የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ 980/2008፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 101፣ ሀምሌ 28 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

[53] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚንስትር፣ የኢትዩጵያ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጫ መድብ መመሪያ ቁጥር 556/2013፣ ሰኔ 2011.

[54] የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አስጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013፣ 27ኛ አመት ቁጥር 42፣ ሀምሌ 28 ቀን 2013።



ምስል 4 የመላሾችን መልስ በመቶኛ ያሳያል

የተለየ አመዳደብ ያስፈልገዋል የሚል ምላሽ የሰጡ መላሾች ይህን ምላሽ የሰጡበትን ምክንያቶች ሲያብራሩ የጥብቅና ስራ የሙያውን ባህሪ መሰረት ያደረገ የግብር አመዳደብ እንደሚያስፈልገው ገልፀዋል። ስራው የሙያ ስራ እና ከፍትህ መረጋገጥ ጋር የሚገናኝ በተለይም የነፃ የህግ አገልግሎት መስጠት ጨምሮ ጠበቅ ያሉ ግዴታዎች ያሉበት በመሆኑ እንደ ንግድ ስራ መታየት የለበትም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል። ከጥብቅና ስራ ባህሪያት አንፃር ስራው በገንዘብ የማይተመን የህሊና ስራ በመሆኑ፣ ካፒታል ላይ መሰረት ያደረገ ስራ ባለመሆኑ፣ ሌሎች ውጫዊ ጉዳዮች ተፅዕኖ ስር የሚወድቅ በመሆኑ እንዲሁም ለስራው እንቅስቃሴ ሲደረግ የሚወጣው ወጪ ከሚገኘው ገቢ አንፃር የማይመጣጠን በመሆኑ የግብር አከፋፈሉም ይህን ባህሪውን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት ብለዋል።

በተጨማሪም የጥብቅና ስራ ገቢ በቋሚነት የሚገኝ ገቢ ባለመሆኑ፣ የግብር አመዳደቡም ይህን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት። ከፍትህ ጋር የተገናኘን ስራ እንደ ሸቀጥ ንግድ መቁጠር ከስራው ጋር የሚጋጭ እና ሞራላዊ ባለመሆኑ ይህንን ባህሪያት መሰረት ያደረገ አመዳደብ መኖር አለበት የሚል ምላሽ ተሰቷል። የአመዳደብ ሁኔታውን በተመለከተ አብዛኖቹ መላሾች የስራውን ባህሪያት ከግምት በማስገባት ቁርጥ ግብር ቢጣልበት አግባብ እንደሆነ መልሰዋል። ሌሎች የስራውን ሁኔታ ከግምት ያስገባ እራሱን የቻለ ሰንጠረዥ ሊዘጋጅለት ወይም እራሱን የቻለ መመሪያ ሊወጣለት ይገባል የሚል ምላሽ ተሰጥቷል። በሌላ በኩል በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀፅ 63 ሰንጠረዥ "መ" **ሌሎች ገቢዎች** ስር ግብር ሊቆረጥ ይገባል የሚል ምላሽም ተሰጥቷል።

በሌላ በኩል የአዲስ ከአበባ ገቢዎች ቢሮ ጠበቆች እንደነጋዴ የማይቆጠሩ ከመሆኑ አንጻር የተለየ የግብር አከፋፈል ስርዓት የሚከተል ስለሆኑ ለቀረበለት ጥያቄ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 9 መሰረት ማንኛዉም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅ እና በግብር አስተዳደር አዋጅ መሰረት ግብር የመክፈል ግዴታ እንዳለበት የተደነገገ በመሆኑ እና ለጠበቆች የተለየ የግብር አከፋፈል ስርዓት (የተለየ ሰንጠረዥ) ስላልደነገጉ ጠበቆችን በነዚሁ አዋጆች አግባብ ግብር የሚያስከፍሉ መሆኑን እና የሚከተሉት የተለየ ግብር አከፋፈል ስርዓት እንደሌለ ጠቅሰዋል።[55]

ገቢ ሰብሳቢዉ ተቋምም የጥብቅና አገልግሎት በሰንጠረዥ ሐ ስር የሚመደብ ነዉ ሲልም ይህን ትርጓሜ በመያዝ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህም ትርጓሜ በጠበቆች እና ግብር ሰብሳቢዉ ተቋም የጥብቅና አገልግሎት የንግድ ስራ ነው ወይስ አይደለም የሚል መነሻ በመያዝ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸዉ ወይስ የለባቸውም ወደሚል መደምደሚያ ሲወስድ ቆይቷል። በግብር ሰብሳቢው ተቋም ዘንድ የጥብቅና ስራ የሙያ ስራ በመሆኑ፣ የሙያ ስራ ደግሞ በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት የንግድ ስራ እንደሆነ ስለሚደነግግ ጠበቆች እንደማንኛዉም ነጋዴ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸዉ ሲሉ፤ በጠበቆች በኩል ደግሞ የፌደራል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1249/2013 የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት መስጠቱ በኢትዮጵያ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ህጎች መሰረት አገልግሎቱን የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ሥራ አያሰኘውም የሚል ድንጋጌ አስቀምጧል።[56] ይህም የጥብቅና ድርጅት የሚሰራው ስራ በዋናነት የጥብቅና አገልግሎት መስጠት በመሆኑ እና ይህም አገልግሎት የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት እንዳልሆነ መደንገጉ በግል የሚሰራ ጥብቅና አገልግሎት የንግድ እንዳልሆነ እንደሚያመላክት፤ ከዚህም በተጨማሪ የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ በሚያደርግበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ እንዳለበት።[57] የዚሁ አዋጅ ማንኛውም ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፍቃድ ሳይኖረው የንግድ ሥራ መስራት አይችልም የሚል ድንጋጌ አስቀምጧል።[58] ይሁንና የጥብቅና አገልግሎት በተግባር የንግድ ፍቃድ የሚያወጣበት አሰራር የለም።

[55] አቶ ወንድምአገኝ ካሳ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና አቶ ጌታቸው ግርማ የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር።

[56] የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አስጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013፣ አንቀፅ 39 (5) ፣ 27ኛ አመት ቁጥር 42፣ ሀምሌ 28 ቀን 2013።

[57] የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ 980/2008፣ አንቀፅ 15 (5) ፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 101፣ ሀምሌ 28 ቀን 2008፣አዲስ አበባ።

[58] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 22 (1).

እንዲሁም በአዋጁ ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ ላይ ሳይመዘገብ የንግድ ስራ ፍቃድ ማግኘት እንደማይችል ደንግጓል።[59] የንግድ ስራ መደብን የሚለየው በንግድ ሚኒስቴር የተዘጋጀው የኢትዩጵያ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጫ መደቦች መመሪያ ቁጥር 17/2011 ላይ ከአምስት መቶ በላይ ዘርፎች ተዘርዝረው የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ ጥብቅና አገልግሎት አይገኝበትም።[60] ከዚህም በላይ የጥብቅና አገልግሎት የንግድ ስራ መሆን እና አለመሆኑን ለመወሰን ከላይ ከተጠቀሱት ህጎች በተሻለ አግባብነት ያለዉ ህግ የገቢ ግብር አዋጁ ሳይሆን የንግድ ህግ ሲሆን በዚህ ህግም የጥብቅና አገልግሎት የንግድ ስራ እንደሆነ ስላልተደነገገ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ መገደድ የለባቸውም የሚል ነዉ።

ከሁለቱም አካላት የተገኙት መረጃዎች የህግ መሰረት ያላቸው ሲሆን ገቢ ሰብሳቢዉ ተቋም የጥብቅና አገልግሎትን በሰንጠረዥ ሐ ላይ በመመደብ የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋይ ጠበቆች እንደ ማንኛዉም ንግድ ስራ ላይ እንደተሰማራ ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ቢያስገድድም ወጪ መያዝን በተመለከተ ግን ጠበቃዉ የሚያወጣዉን (እንደ ነዳጅ፣ የስልክ እና የመሳመሉትን ወጪዎች) ከሌላዉ ነጋዴ በተመሳሳይ እየተያዘለት አለመሆኑ የፍትሀዊነት ጥያቄ የሚያስነሳ ነዉ። ጠበቃዉ ለግብር አባሰብ ሲባል በሰንጠረዥ ሐ ስር ከንግድ ስራዎች ከሚገኝ ገቢ ጋር መመደቡ ሙያዉ የንግድ አገልግግሎት ነዉ ወይም አይደለም ወደሚል መደምደሚያ የሚዎስድ አይደለም። የገቢ ግብር አዋጁ ጥብቅና ናን ከንግድ ስራ ጋር ሲመድብ የንግድ ስራ ነዉ በሚል እሳቤ ሳይሆን ለግብር አሰባሰብ አመቺነት በማሰብ እንደሆነ እና በጥናቱ የታዩ ሌሎች ሀገራት ልምድም ከዚህ የተለየ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ አመዳደብ ላይ የሚነሳዉ ዋና ችገግር የጥበቅና አገልግሎት ከሌሎች የንግድ ስራዎች ጋር በአንድ ሰንጠረዥ መመደቡ ሳይሆን በግብር አከፋፈል ወቅት ሌሎች የንግድ ዘርፎች የሂሳብ መዝገብ ሲያቀርቡ ያስመዘገቧቸዉ ወጪዎች ተቀናሽ ሲደረግላቸዉ በጠበቃ በኩል የሚቀርቡ ዋና ዋና ወጪዎች ሳይቀር ተቀናሽ እየተደረጉ አለመሆኑ ነዉ። ስለሆነም ጠበቃዉ በሰንጠረዥ ሐ ስር ተመድቦ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዝ የሚገደድ ከሆነ ገቢ ለማግኘት የሚያወጣቸዉ ወጪዎች ሊያዙለት ይገባል። ጠበቃው ያወጣቸዉ ወጪዎችን መያዝ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የጥብቅና አገልግሎት በአዲስ ሰንጠረዥ እንዲመደብ በማድረግ ወይም በሰንጠረዥ መ ስር እንዲመደብ በማድረግ ከሂሳብ መዝገብ ዉጪ ግብር የሚከፍልበትን የህግ አማራጭ መከተል ያስፈልጋል።


[59] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 5 (1).

[60] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚንስትር፣ የኢትዩጵያ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጫ መድብ መመሪያ ቁጥር 556/2013፣ ሰኔ 2011.

ቀጥሎ ባሉት ንዑስ ክፍሎች ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና ወጪ አያያዝ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች በሰፊዉ ተዳሰዋል።

3.2. የሂሳብ መዝገብ መያዝ

ተሳታፊዎች በየትኛው የግብር ደረጃ ግብር እንደሚከፍሉ ተጠይቀው 70 በመቶ መላሾች ደረጃ ሐ የሚከፈሉ ሲሆን፣ የተቀሩት ደረጃ ለ እና ደረጃ ሀ እንደሚከፍሉ ገልፀዋል።



ምስል 2 የመላሾች መልስ ያሳያል

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታነትን ደንግጓል።[61] በዚህ አንቀጽ መሰረት ግብር መክፈል ግዴታ ያለባቸው የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት የተዘጋጀ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል። የሂሳብ መዝገቡ ይዘትን በተመለከተ ይህ አንቀፅ የሂሳብ መዝገብ የሚከተሉትን እንዲይዝ ይደነግጋል፡-

[61] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፣ አንቀፅ 82፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 104፣ ነሀሴ 2 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

- ቋሚ ሀብቶች የተገዙበት ቀን፣ ዋጋ፣ ሀብቱን ለማሻሻል የወጣው ወጪ እና የሀብቱን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድን ጨምሮ የንግድ ስራውን ሀብት እና ዕዳ የሚያሳይ ሰነድ፤
- ከግብር ከፋዩ ጋር በተገናኘ በየቀኑ የተገኘውን ማናቸውንም ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤
- ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ የንግድ ዕቃዎችን ግዢ እና ሽያጭ እንዲሁም በግብር ከፋዩ የተሰጡ እና የተገኙ አገልግሎቶች የሚያሳይ ሰነድ፤
- በግብር አመቱ መጨረሻ በግብር ከፋዩ እጅ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎች አይነት፣ መጠን እና ዋጋ እና መገመቻ ዘዴን የሚያሳይ ሰነድ፤

እንዲሁም ሌሎች ሰነዶችን ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል።

በሌላ በኩል የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታዎች እንደሆኑ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀፅ 82 (2) ይደነግጋል፣ እነዚህም


- የየቀኑን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ መዝገብ፣
- ሁሉም ግዢዎች እና ሽያጮችን የሚያሳይ መዝገብ፣
- የደሞዞች እና የአበሎች መዝገብ፣
- ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው ሰነድ፣[62]

የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ አይገደዱም። ነገር ግን በፍቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ ከያዙ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 መሰረት በሂሳብ መዝገቡ አማካኝነት ግብር ይከፍላሉ።[63] በዚሁ ደንብ አንቀፅ 60 (1) መሰረት የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በአመታዊ የሽያጭ መጠን ላይ የተመሰረተ የግምት መደበኛ የቁርጥ ግብር ወይም አመላካች ባላቸው የንግድ ስራ ዘርፎች የቁርጥ ግብር ዘዴዎች መሰረት ግብር ይከፍላል ብሎ ይደነግጋል።[64] በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወጣው የገቢዎች ሚኒስትር መመሪያ ታክስ በግምት ስለሚሰላበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ቁጥር 138/2010 ለ99 የስራ ዘርፎች የተጣራ ትርፍ፣ ያልተጣራ ትርፍ

[62] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 82 (2).
[63] የሚንስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 410/2008፣ 23ኛ እትም፣ ቁጥር 82፣ ነሀሴ 18 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።
[64] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 60 (1).

እና አማካኝ የስራ ቀናት ምንያህል እንደሆኑ ደንግጓል።[65] በዚህም መሰረት ጥብቅና የተጠራ ትርፉ ወይም ግብር የሚሰላበት ትርፍ የገቢው 25 በመቶ ሲሆን፣ ያልተጣራ ትርፍ 37.5 በመቶ አማካኝ አመታዊ የስራ ቀናት 300 ቀናት በሚል ተደንግጓል። ይሁንና አዋጁ ይህን ቢደነግግም ጠበቆች ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ ጋር በተገናኘ የገጠሟቸው ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን እና ችግሮችም ካሉ እንዲገልፁ ተጠይቀው አብዛኞቹ መላሾች ችግር እንደገጠማቸው መልሰዋል።

ምስል 5 የመልሱን በመቶኛ ያሳያል።



ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ ጋር በተገናኘ ችግር መኖሩን የጠቆሙት መላሾች ችግሮቹ ምን ምን እንደሆኑ ተጠይቀው አብዛኞቹ ከወጪ አያያዝ ጋር የተገናኙ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ጠቅሰዋል። ይህን ሲያብራሩ መዝገብ መያዝ ማለት ገቢ እና ወጪ መያዝ ማለት ነው። ይሁንና የግል ጠበቆች ምን አይነት ወጪ እና በምን አግባብ መያዝ እንዳለባቸው የተዘጋጀ ዝርዝር ህግ አለመኖሩ፣ ለጥብቅና ስራ አስፈላጊ የሆኑ ማለትም የመጓጓዣ ወጪዎች፣ አለም አቀፍ ትሥሥሮች (legal networks) ለምሳሌ አለም-አቀፍ የጠበቆች ማህበር የመሰሰሉት አባል ለመሆን የሚወጡ ወጪዎች፣ የስልጠና ወጪዎች፣ የመዝናኛ ወጪዎች፣ የትርጉም ወጪዎች፣ የነዳጅ እና የመኪና ወጪ ለስራው እጅግ አስፈላጊ ቢሆኑም እንደወጪ አለመያዛቸው የሂሳብ መዝገብን አያያዝ እጅግ አስቸጋሪ እንደሚያደርገዉ ገልጸዋል። በተጨማሪም የጥብቅና አገልግሎት ውል ተቋርጦ ገንዘብ ተመላሽ ቢደረግ የሂሳብ መዝገቡ ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ገልፀዋል።

[65] ታክስ በግምት የሚሰላበትን ሁኔታ ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 138/2010፣ ነሀሴ 2010፣ አዲስ አበባ።

የትኩረት ቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች የሂሳብ መዝገብ አያያዝን አስመልክቶ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል። የገቢ ግብር አዋጁ ጠበቆች በተግባር ከሚያከናውኗቸው ተግባሮች አንፃር የተቃኘ አይደለም። የገቢ ግብርን በሚመለከት አዋጁ የሂሳብ መዝገብ መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል። የሂሳብ መዝገብ ደግሞ የሚያዘው ከአካውንቲንግ ስታንዳርዶች አንፃር ነው። አካውንቲንግ ስታንዳርዶችን ስንመለከት asset (ሀብት) እና liability (ዕዳ) መሰረት ያደረገ አመዘጋገብ ነው። ይህን ከጥብቅና አንፃር ብንመለከተው በዋናነት ጠበቃ ያለው ሀብት እውቀቱ ነው። እውቀትን asset (ሀብት) በሚል ልንይዘው እንችላለን ወይ? አንድ ሰው እውቀት ስላለው ብቻ ገቢ ያገኛል ማለት ነው ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልስ አስቸጋሪ ነው። Liability (ዕዳ) ስንመለከት አንድ ጠበቃ አንድን ጉዳይ ሲይዝ ያለበትን ሀላፊነት በትክክል ማወቅ ይቻላል ወይ? በአካውንቲንግ ስታንዳርድ መሰረት ሁሉም ህግ ላይ የተቀመጡት ወጪ እና ገቢዎች በገንዘብ የሚተመኑ ናቸው። በጥብቅና ስራ ግን የጠበቃው ሀላፊነቶች ወደ ገንዘብ የሚቀየሩ (quantifiable) አይደሉም። ፍርድ ቤት ውሎ የሚመጣ ጠበቃ ለመጓጓዣ ከሚያወጣው ወጪ በስተቀር ለምሳሌ ፍርድ ቤት አጥፍቶት የሚመጣው ግዜ እንደወጪ ከግምት መግባት የሚችል አይደለም። ይህ የሚጠፋዉ ግዜ በጠበቃውም የሚወሰን ስላልሆነ ወጪ አድርጎ ለመመዝገብ ያስቸግራል። እንዲሁም በጥብቅና ውስጥ ፍርድ ቤት በመቆም እና ከፍርድ ቤት ውጪ በማማከር የሚሰጥ አገልግሎት አሉ። ፍርድ ቤት ብቻ የሚቆሙ አሉ። ማማከር ብቻ የሚሰሩ አሉ። ሁለቱንም የሚሰሩ አሉ። በተለይ ከማማከር ጋር የተያያዙ ወጪዎችን መመዝገብ በጣም አስቸጋሪ ነው በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል።[66]

በሌላ በኩል በተግባር እየገጠሙ ካሉ ችግሮች መካከል በየግዜው የገቢዎች መስሪያ ቤት ሰራተኞች መቀያየር ጋር ተያይዞ የሂሳብ መዝገብ ከመያዝ ጋር በአዋጁ አፈጻጸም ላይ የወጥነት ችግር እንዳለ በግብር ከፋይ ጠበቆች ዘንድ ይነሳል። ይህን በተመለከተ ለተሳታፊዎች በየትኛው ክፍለ-ከተማ ግብር እንደሚከፍሉ እና የሚከፍሉበት ክፍለ-ከተማ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚያስገድድ ስለመሆን አለመሆኑ ተጠይቀው በሰንጠረዥ 1 የተቀመጠውን ምላሽ ሰጥተዋል። ከእነዚህ መላሾች ዉስጥ 70% ግብር ከፋዮች ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሲሆኑ፣ 17% ደረጃ "ለ"፣ የተቀሩት 13% ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ናቸዉ።

[66] የትኩረት ቡድን ውይይት, የፌደራል ጠበቆች ማህበር ቢሮ, ጥቅምት 11, 2015, 8፡00 ሰዐት.

ሰንጠረዥ 1

ክፍለ-ከተማ	**የሂሳብ መዝገብ መያዝ**	**ምልከታ**
ንፋስ-ስልክ ላፍቶ	ያስገድዳል	አያስገድድም ያሉ መላሾችም አሉ
አዲስ-ከተማ	አያስገድድም	
ቂርቆስ	አያስገድድም	ወደ ህግ ቢሮ ከተቀየረ በኋላ ያስገድዳል
ኮልፌ-ቀራንዮ	አያስገድድም	ያስገድዳል ያሉ መላሾችም አሉ
ጉለሌ	አያስገድድም	ያስገድዳል ያሉ መላሾችም አሉ
ለሚ-ኩራ	አያስገድድም	ያስገድዳል ያሉ መላሾችም አሉ። አንድ መላሽ ከደረጃ ሐ በስተቀር ሌሎች ደረጃዎች ላይ ያስገድዳሉ የሚል ምላሽ ሰጥቷል።
ልደታ	ያስገድዳል	
ቦሌ	ያስገድዳል	
አራዳ	ያስገድዳል	
የካ	አያስገድድም	ያስገድዳል ያሉ መላሾችም አሉ

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የመጠይቁ መላሾች ከአቃቂ ቃሊቲ በስተቀር በአስር ክፍለ-ከተሞች ያሉ ግብር ከፋዮች ናቸው። ከእነዚህ ክፍለ-ከተሞች ውስጥ በልደታ፣ ቦሌ እና አራዳ ክፍለ-ከተሞች ውስጥ ሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ሲሆን፣ አዲስ ከተማ ክፍለ-ከተማ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ አይደለም። ከዚህ በተቃራኒ በተቀሩት ክፍለ-ከተሞች ማለትም በንፋስ-ስልክ ላፍቶ፣ በኮልፌ ቀራንዮ፣ በጉለሌ፣ እና በለሚ-ኩራ ክፍለ-ከተማ ወጥነት የሌለው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መስፈርት መቀመጡን ያሳያል። በእነዚህ ክፍለ-ከተሞች አንዳንድ መላሾች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ መገደዳቸውን ሲገልፁ ሌሎች መላሾች ደግሞ

መዝገብ ለመያዝ አለመገደዳቸውን ገልፀዋል። በተለይ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ-ከተማ ግብር የሚከፍሉ መላሾች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የሂሳብ መዝገብ ባለመያዝ ቅጣት ተጥሎባቸው የገቢ ግብር መክፈላቸውን ገልፀዋል። ከወጥነት አለመኖር ጋር በተያያዘ የትኩረት ቡድን ወይይት ተሳታፊዎች ተመሳሳይ የወጥነት ችግር እንዳስተዋሉ ገልፀዋል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጠበቆች ክፍለ-ከተማ ለመቀየር እንደተገደዱ ገልጸዋል።

ይሁንና የዚህ በክፍለ-ከተሞች መካከል የሚታየዉ የወጥነት ችግር እንዳለ ሆኖ በአራት በሚንስትር መስሪያ ቤቶችም የወጥነት ችግር እና አራት የተለያየ አቋም እንዳለ የትኩረት ቡድን ተወያዮች ይገልጻሉ። ይኸዉም ፍትህ ሚንስቴር ጠበቃ ነጋዴ አይደለም የተለየ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ነው ይላል። ገቢዎች ሚንስትር ጠበቃ እንደ ነጋዴ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት የሚል ሲሆን የሂሳብ መዝገብ ሲያዝ ደግሞ ገቢ እና ወጪው መመዝገብ አለበት። ከወጪዎች መካከል ቢያንስ ዋንኛ የሆኑትን እና ለሌሎች ግብር ከፋዮች የሚያዙ የነዳጅ እና የስልክ ወጪ ለማስያዝ ደግሞ መኪና ኮድ 3 (ሶስት) መሆን አለበት፣ ሞባይል በድርጅት ስም የተመዘገበ መሆን አለበት። ትራንስፖርት ሚንስቴር ደግሞ ኮድ 3 ታርጋ ለመስጠት ከንግድ ሚንስትር የወጣ የንግድ ፍቃድ ይጠይቃል። ንግድ ሚኒስቴር ደግሞ የንግድ ፍቃድ ለጠበቆች አይሰጥም።[67]

በትኩረት ቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ አንድ ተሳታፊ የግል ልምዳቸውን በሚከተለው መልኩ አካፍለዋል።

> *"...የ2014 ዓ.ም የገቢ ግብር ለመክፈል ከፍትህ ሚንስትር በ2011 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ እና የገቢ ግብር አዋጁን ይዤ ወደ ገቢዎች ቢሮ ሄድኩ። የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች የገቢ ግብር አዋጁ የሚለው ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ ነው ስለሆነም የፍትህ ሚንስትር ደብዳቤን አንቀበልም የሚል መልስ ተሰጠን። አማራጭ ሲጠፋ ባንክ ስቴትመንት ካላመጣችሁ ክሊራንስ አንሰጣችሁም ተብለን የሂሳብ መዝገብ ባለመያዝ 8,400 (ስምንት ሺህ አራት መቶ) ብር ተቀጥቼ በሚቀጥለው አመት የሂሳብ መዝገብ ባላመጣ ፍቃዴ ይሰረዛል የሚል ወረቀት ላይ ፈርሜ ክሊራንስ ወስጃለሁ። ለዚሁም የተወቀስኩት እኔ ነኝ። ደረሰኝ ስታወጣ ግዴታዎቼ ምንምን ናቸው የሚል ጥያቄ መጠየቅ ነበረብህ የሚል ምላሽ ተሰጥቶኛል።"*[68]

[67] የትኩረት ቡድን ውይይት, የፌደራል ጠበቆች ማህበር ቢሮ, ጥቅምት 11, 2015, 8፡00 ሰዐት.
[68] ዝኒ ከማሁ.

ይህን የወጥነት ቅሬታ በተመለከተ ለአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ሀላፊ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽም *“ቢሮዉ ገቢ የሚሰበስበዉ በህጉ መሰረት ነዉ። ህጉ ደግሞ ወጥ ነዉ። የወጥነት ችግር የሚከሰተዉ በፈጻሚዉ ነዉ። የግብር ወጥነት ችግር ካለባቸዉ ግብር ከፋዮች አንዱ ጥብቅና ነዉ።አንድ ግብር ከፋይ ሂሳብ መዝገብ ካልያዘ በግምት እንደሚከፍል በመመሪያ ተቀምጧል። በዚሁ መመሪያ ግብር ለመወሰን ከሚጠቀሙባቸዉ መረጃዎች አንዱ የጠበቃዉ የባንክ ስቴትመንት እንደሆነ እና ማንኛዉም ጠበቃ በባንክ ሂሳብ ዉስጥ ያለዉ ገንዘብ በጥብቅና አገልግሎት ያላገኘዉ ስለመሆኑ የማያስረዳ ከሆነ በአካዉንቱ ዉስጥ በተገኘዉ ገንዘብ መጠን ግብር እንዲከፍል እንደሚደረግ ተቀምጧል። ጠቅላላ ገቢያቸዉ ከአምስት መቶ ሺህ ብር በላይ የሆኑ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ አንዲይዙ ይገደዳሉ። የሂሳብ መዝገብ የማይዙ ጠበቆችን ደግሞ ቅጣት እንቀጣለን። በቀጣይ ሁለት አመት ዉስጥ አዋጁ የሂሳብ መዝገብ የማይዝ ግብር ከፋይ ፍቃዱ አንደሚሰረዝበት ስለተቀመጠ ይህንን እንተገብራለን። በተለየ መንገድ በህግ እስካልተቀመጠ ድረስ አዋጁ ሂሳብ መዝገብ እንዲያዝ ያስገድዳል። ስለዚህ እኛ ይህንን እንተገብራለን። ይህ ዳይሬክቶሬት በሁሉም ቅርንጫፎች፣ ክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች የሚሰበሰብ ግብር ወጥነት ያለዉ አንዲሆን ድጋፍ የሚያደርግ ክፍል ነዉ”* የሚል ነዉ።[69]


ጉዳዩን ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በግብር ከፋይ ጠበቆች መካከል ግብር አከፋፈል ጋር ተያይዞ የተፈጠረን አለመግባባት መፈጠሩን በተመለከተ ላቀረብንላቸዉ ጥያቄ የሰጡን ምላሽ *“በንፋስ ስልክ ላፍቶ ተከስቶ የነበረዉ ችግር ከማሳወቅያ ግዜ ጋር በተያያዘ ነዉ።ችግሩ የተከሰተዉ ከአንድ ጠበቃ ጋር ነዉ። ይህም ግብር ከፋይ ጠበቃዉ የመጣዉ ደረጃ ሐ በሚከፍሉበት ግዜ ሲሆን በእኛ በኩል ደግሞ ያልነዉ የሂሳብ መዝገብ አዘጋጅ እና በቀጣይ ወራት ና ነዉ ያልነዉ። ለጠበቆች የሂሳብ መዝገብ መያዝ ካልቻላችሁ የባንክ ስቴትመንት አምጡ ብለን አምጥተዉ ያስተናገድናቸዉ ጠበቆች አሉ። አንዳንድ ጠበቆች ደግሞ አናመጣም በማለት እምቢተኛ ነበሩ። ጠበቆቹ የመጡት በ ሐ መክፈያ ግዜ ሲሆን ግብር ለመክፍል መምጣት ያለባቸዉ ግዜ ግን በ ደረጃ ሀ እና ለ ግዜ ነበር መሆን ያለበት። ጠበቆቹ የባንክ ስቴትመንት ባያመጡም እና የሂሳብ መዝገብ ባይዙም መረጃ ሰብሰቢ*

[69] አቶ ወንድምአገኝ ካሳ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና አቶ ጌታቸዉ ግርማ የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር።

ክፍላችን መረጃዎችን ከፍርድ ቤት እና ከባንኮች በመሰብሰብ ግብር እንዲከፍሉ እንደሚደረግ" ገልጸዋል።[70]

በመጠይቁ የተሳተፉ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የማይገደዱ ከሆነ በምን አግባብ ግብር እንደከፈሉ ተጠይቀው አብዛኖቹ በቁርጥ ግብር የከፈሉ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ በግምት እና በሌሎች መንገዶች እንደከፈሉ ገልፀዋል።

ምስል 6 የመላሾችን መልስ በመቶኛ ያሳያል።



በሌላ መንገድ ግብር እንደከፈሉ የገለፁት መላሾች በምን መንገድ እንደከፈሉ ተጠይቀው በውል ሰነድ አማካኝነት፤ በቅጣት፤ በግምት፤ እና በደረሰኝ አማካኝነት መክፈላቸውን ነገር ግን ወጪዎቻቸውን ማስያዝን በተመለከተ የገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች አግባብ ነው ብለው ያሰቡትን ወጪዎች በመያዝ አግባብ ነው ብለው ካላሰቡ ደግሞ ወጪዎቹን ውድቅ በማድረግ ግብር እንደሚያስከፍሏቸዉ ገልፀዋል። በትኩረት ቡድን ውይይቱ ላይ የተሳተፉ አንድ ጠበቃ የሚከተለውን ከልምዳቸው አካፍለዋል፤

26 አመት ያገለግሉ ጠበቃ


[70] ዝኒ ከማሁ።

"... መጀመሪያ የቫት ተመዝጋቢ ስሆን ከዚያው ጋር ተያይዞ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለብህ በሚል በቁርጥ አትስተናገድም ተብዬ። ተቀጥቼ እንድስተናገድ ብጠይቅም አይቻልም ስለተባልኩ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ጀምሬ ነበር። ነገር ግን ጠበቃ ሊያቀናንስ የሚችለው ወጪ የለም። ከጠቅላላው ሂሳብ 10 በመቶ የሚሆነውን እንኳን ወጪ ማስመዝገብ አይችልም። ወጪ ተብሎ የሚቀናነሰው አምስት በመቶ እንኳን ስለማይሞላ 95 በመቶው ላይ 35 በመቶ ግብር ይጣልበት ነበር። ይህም ነጋዴዎች ከሚስተናገዱበት አግባብ ጋር የማይገናኝ እና አመክንዮ የሌለው ነው። ለምሳሌ አንድ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዝ የሚገደድ ነጋዴ የሂሳብ መዝገቡ በተለያየ መንገድ ውድቅ ቢደረግ መቀጫ ይከፍል እና ካገኘው ገቢ ላይ 65 በመቶ እንደወጪ ተይዞ በ35 በመቶው ላይ ግብር ይከፍላል። ነገር ግን የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የሚሞክር ጠበቃ በ95 በመቶ ገቢው ላይ ግብር ለመክፈል ይገደዳል። ይህም ፍትሀዊም አመክኖአዊም አይደለም። ስለዚህ ለጠበቃው የሂሳብ መዝገብ ከመያዝ ይልቅ የሂሳብ መዝገብ ባለመያዝ ምክንያት ተቀጥቶ ግብር መክፈል የተሻለ ነው።"[71]

ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት የጥብቅና አገልግሎት ባህሪያት አንጻር ጠበቆች ግብር የሚከፍሉት የጥብቅና አገልግሎትን ልዩ ባህሪያት ከግምት ያስገባ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በተግባር ያለዉ አሰራር ምን እደሚመስል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አብዛኖቹ ጠበቆች ግብር አከፋፈሉ የጥብቅናን ባህሪያት መሰረት ያደረገ አለመሆኑን የመለሱ ሲሆን ጥቂት ጠበቆች ደግሞ ከግምት ውስጥ እንደሚገባ ገልፀዋል።

[71] የትኩረት ቡድን ውይይት, የፌደራል ጠበቆች ማህበር ቢሮ, ጥቅምት 11, 2015, 8፡00 ሰዐት::

ምስል 7 የተሳታፊዎችን ምላሽ በመቶኛ ያሳያል



በግብር አከፋፈል ወቅት የጥብቅና ስራ ልዩ ባህሪያት ከግምት ገብተዋል በሚል ምላሽ የሰጡት ተሳታፊዎች ይህን ያሉበትን ምክንያት የሂሳብ መዝገብ አለመጠየቃቸው፣ የጥብቅና ውሎችን በማቅረብ ግብር እንዲከፍሉ መደረጉ፣ በመቶኛ ወጪ በመቀነስ የግብር ሂሳብ መሰላቱ እንዲሁም በቁርጥ ግብር እንዲከፍሉ መደረጉ የጥብቅና ስራን ባህሪያት ከግምት ያስገባ የግብር አከፋፈል ስርዐት መኖሩን እንደማሳያነት ጠቅሰዋል። ከዚህ በተቀራኒ በግብር አከፋፈል ወቅት የጥብቅና ስራ ልዩ ባህሪያት ከግምት አይገቡም የሚሉት ተሳታፊዎች ምክንያታቸውን ሲገልፁ፤

1. **ለስራው የሚወጡ የገንዘብ ወጪዎች አለመያዛቸው፡-** በተለይም የቢሮ ክራይ፣ የመጓጓዣ፣ የስቴሽነሪ፣ ለጉዳይ አስፈፃሚ የሚከፈል፣ ትዕዛዝ ለማስወጣት የሚከፈል እና የነዳጅ ወጪዎች፤
2. **በወጪነት ሊያዙ የማይችሉ ነገር ግን የጥብቅና ስራ አካል የሆኑ ተግባራት መኖራቸው፡-** ለምሳሌ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚጠፋው ግዜ፣ የጥብቅና ስራ የእውቀት ስራ መሆኑ፣ የነፃ አገልግሎት መስጠት ግዴታ መኖሩ እና ከዚህ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚወጣው ወጪም ከግምት ሊገባ የማይችል በመሆኑ፤
3. **የሙያው አይነት ከግምት መግባት ስላለበት፡-** የጥብቅና ስራ የሙያ ስራ እንጂ ንግድ ባለመሆኑ እንደሌላው ነጋዴ ስራውን ማስተዋወቅ የማይቻል በመሆኑ፣ እንዲሁም ከስራው የሚገኘው ገቢ የተወሰነ ጣሪያ ያለው በመሆኑ፣ ስራው ሁልግዜ የማይገኝ በመሆኑ እና ጠበቆች ሰራተኛ ቀጥረው ለራሳቸውም የውሎ አበል እየከፈሉ የሚሰሩ ባለመሆኑ፣ እንደሌሎች ነጋዴዎች የንግድ ፍቃድ ወጥቶ የሚሰራ ስራ ባለመሆኑ፣ በውል መሰረት ግብር ሲጣል ግብሩ መከፈል ያለበት በውሉ መጠን ላይ

ሳይሆን ጠበቃው በተቀበልው መጠን ላይ ብቻ መሆን ያለበት መሆኑን እንደምክያትነት አንሰተዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የትኩረት ቡድን ውይይቱ ተሳታፊ ጠበቆች ከጥብቅና ክፍያ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ የገቢ ግብር አዋጁ ክፍተት እንዳለበት ጠቁመዋል። አዋጁ አንድ ገቢ መቼ ነው ገቢ የሚባለው የሚለው ነጥብ ላይ የጥብቅና ስራን ባህሪ መሰረት ያደረገ አይደለም።የጥብቅና ውል ሲፈፀም በአብዛኛው 50 በመቶ ቅድሚያ ክፍያ ሲሆን ቀሪው 50 በመቶ ደግሞ ጉዳዩ ሲያልቅ እንደሚከፈል ውል ላይ ይጠቀሳል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በተግባር እየገጠመ ያለው ችግር ቀሪው 50 በመቶ ጠበቃው ባይቀበል እንኳን ግብር ይጣልበታል። ቀሪውን ክፍያ መቀበል ግዴታ የጠበቃው ነው በሚል እሳቤ ክፍያ ባይፈፀም እንኳን ግብር ይጣላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በተግባር የገጠሙ ችግሮች አሉ። የገቢዎች ሰራተኞች የጥብቅና ውልን የሚረዱበት አግባብ ትክክል አይደለም። ውል አለ ማለት በውሉ መሰረት ክፍያ ተፈፀሟል ማለት አይደለም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 እንዲሁም የገንዘብ ሚንስቴር የገቢ ግብር አዋጁን አስመልክቶ የሰጠው ማብራሪያን መመልከት ተገቢ ነው። የገቢ ግብር አዋጁ አንቀፅ 32 (1) ሂሳቡን በተሰብሳቢ እና በተከፋይ ሂሳብ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ከተዋዋለው የረጅም ግዜ ውል ውስጥ በግብር አመቱ የተጠናቀቀውን በመቶኛ መሰረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ስራ ገቢ ውስጥ ሲያካትት ወጪውም በዚያው በመቶኛ ልክ በተቀናሽ እንዲያዝለት ይደረጋል የሚል ድንጋጌ አስቀምጧል።[72] ይህ አንቀፅ ያብራራው የገንዘብ ሚንስትር ማብራሪያ ለርጅም ግዜ የሚደረግ ውል ማለት ከ12 ወራት በላይ የሚፈጅ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ስራ ለመስራት እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ውል ነው ብሎ ትርጉም ሰጥቷል። ምንም እንኳን ጥብቅና አመታት ሊፈጅ የሚችል ስራ ቢሆንም ከዚህ ትርጉም ውስጥ አልተካተተም። በዚሁ ማብራሪያ እንደተጠቀሰው የረጅም ግዜ ስራ ውል ላይ የሚከፈልን ግብር አስመልክቶ ግብር የሚከፈልበት አግባብ የተጠናቀቀው ስራ በምስክር ወረቀት በመቶኛ ሲለይ ወይም በምስክር ወረቀት ከተለየው በላይ የተጠናቀቀ ካለ ይህንንም አካቶ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል።[73] ነገር ግን የጥብቅና ስራ

[72] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፣ አንቀፅ 9፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 104፣ ነሀሴ 2 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

[73] በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የገንዘብ ሚንስትር፣ በግብር እና በታክስ ህጎች አፈፃፀም ረገድ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ፣ መስከረም 2014.


መቼ እንደምሚጠናቀቅ እና የተጠናቀቀው የስራው አካል በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ መለየት ፍፁም አይቻልም።

ይሁንና በጎረቤት ሀገር ኬንያ ከሂሳብ መዝገብ መያዝ ጋር ያለዉን ልምድ ስንመለከት ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸዉ ሲሆን ከወጪ አያያዝ ጋር በተገናኘ ለኢንተርቴይመንት ከወጣ ወጪ ጀምሮ በርካታ የጠበቆች እና ጥብቅና ድርጅቶች ወጪዎች ይያዙላቸዋል። በተመሳሳይ በታንዛኒያ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸዉ ሲሆን ከኬንያ በተመሳሳይ ጠበቆች ወጪዎቻቸዉን የማስያዝ መብት ያላቸዉ ቢሆንም የመዝናኛ ወጪ ግን የሚያዝበት ገደብ/ጣርያ/ የተቀመጠለት በመሆኑ የተጋነኑ ወጪዎች ተቀባይነት አይኖረዉም።

3.3. ወጪ አያያዝ እና የጥብቅና አገልግሎት

ከጥብቅና ስራ ጋር ተያይዞ የሚወጡ ወጪዎች ሊያዙ የሚችሉበትን አግባብ አስመልክቶ፣ ጠበቆች ወጪ አያያዙ እንዴት ሊሆን ይገባል ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አብዛኖቹ ተሳታፊዎች የወጪ አያያዝ በተለየ ሁኔታ ሊስተናገድ ይገባል ያሉ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ ከሌሎች ዘርፎች ጋር በተመሳሳይ ሊስተናገድ ይገባል ብለዋል።

ምስል 8 የመላሾችን መልስ ያሳያል።



በተለየ ሁኔታ ሊስተናገድ ይገባል ብለው የመለሱት መላሾች ምክንያታቸውን ሲገልፁ በዋነኝነት የጥብቅና አገልግሎት ለትርፍ የሚሰራ ስራ ባለመሆኑ፣ ማህበራዊ ፋይዳው ጉልህ በመሆኑ፣ ከስራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጪዎችን መመዝገብም ሆነ በደረሰኝ መያዝ አስቸጋሪ በመሆኑ የተለየ የወጪ አያያዝ ስርዐት ሊኖረው ይገባል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በተጨማሪነት በትኩረት ቡድን ውይይቱ እና በመጠይቁ ምላሾች የተገለፁት ምክንያቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፤

1. የጥብቅና ሙያ የውል መሰረት የጉዳዬን 10% የማስከፈል የክፍያ ጣሪያ ያለበት መሆኑ፤ ጠበቃው የሰራውን መዝገብ ከግምት በማስገባት በቁርጥ ማስከፈል አግባብ ነው።
2. የጥብቅና ሙያ ከፍተኛው ወጪ ግዜ፣ እውቀት እና ጉልበት መሆኑ እና እንደሌሎች የንግድ አይነቶች የጥሬ እቃ ወጪ ወይም የግብአት ወጪ ማስመዝገብ የማይቻል በመሆኑ ይህን ከግምት ያስገባ የወጪ አያያዝ ስሌት መተግበር አለበት።
3. የጥብቅና ሙያ ዕውቀት እና ሙያ መር ከመሆኑም ባሻገር በዋጋ ሊተመን የማይችል የነፃ የህግ አገልግሎት የሚሰጥበት የስራ አይነት ነው። ወጪ አያያዝ ላይ ያለው ችግር ከግምት ሊገባ ይገባል።
4. የጥብቅና ሙያ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ እና በሙግት የሚሰራ ስራ ከመሆኑ አንፃር ለምግብ፣ ለመጠጥ፣ ትራንስፖርት እና ለነዳጅ የሚወጡ ወጪዎች ከግምት መግባት አለባቸው።
5. የጥብቅና ስራ የንግድ ስራ ባለመሆኑ በአካውንቲንግ ስታንዳርዶች መሰረት ወጪ መያዝ አለመቻሉ ከግምት መግባት አለበት።
6. ከጥብቅና ስራ ባህሪያት አንፃር ፍርድ ቤት የሚጠፋው ግዜ እንደወጪ ሊያዝ ይገባል።

የትኩረት ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ለጥብቅና ስራ ግብአት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ወጪዎች እንዳሉ ጠቁመው፤ ምሳሌዎች ሲጠቅሱ ስራውን የሚመጥን ልብስ፣ ስለ ጉዳዩ ከደንበኛ ጋር ለመወያየት እና ምስክሮችን ለማናገር የሚያወጣቸው የግብዣ ወጪዎች፤ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ሲቀየር ሆቴል የምግብ ወጪ፣ ወደ ውጪ ሀገር የሚደረጉ የስራ ጉዞዎች ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣ ደንበኛ ቢሮ ውስጥ ለመቀበል ለሻይ ቡና የሚወጡ ወጪዎች፣ ደንበኛ ለመሳብ ቢሮ ለማሳመር የሚወጡ ወጪዎች፣ ለመጓጓዣ ወይም ለነዳጅ የሚወጡ ወጪዎች ቢሮን ለማሳመር የሚያወጣው ወጪ፤ ሴክሬቴሪያል አገልግሎት ወጪ (የኮፒ፣የፕሪንት፣ ሲዲ፣ ቀረጥ ቴምብር)፣ሰነድ ለማረጋገጥ የሚወጡ ወጪዎች፣ የስልክ እና የኢንተርኔት ወጪ (ይህ እራሱን የቻለ ችግር አለው የግል እና የስራ ወጪ ይቀላቀላል በሚል ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል)፤ ጠበቃ

ማስታወቂያ መስራት ስለማይፈቀድለት ይህን ተክቶ እራሱን ለማስተዋወቅ የሚያወጣቸው ወጪዎች፤ ግዜው ተገምቶ እንደ ወጪ ሊያዝ ይገባል በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። እነዚህ ወጪዎች ሊያዙ የሚችልበት አግባብ ከሌለ የጥብቅና ስራ እንደንግድ ሊታይ አይገባም በሚል ምላሽ ሰጥተዋል።[74]

በሌላ በኩል የትኩረት ቡድን ውይይት አባላት እንደገለፁት የጥብቅና ስራ በባህሪው ይህን ያክል የተጣራ ገቢ አገኝበታለሁ ተብሎ የሚሰራ ስራ አይደለም። ወጪዎቹን በትክክል ለይቶ ማወቅ አይቻልም። ወጪው መቼ እንደሚወጣም ማወቅ አይቻልም። ይህ በሙሉ የሚወሰነው በሌላ ሶስተኛ አካል ነው። የጥብቅና አገልግሎት በትትክል የሚፈጀውን ግዜ አውቆ በውል ውስጥ ማካተት አይቻልም ስለዚህም አገልግሎቱን ለየት ያደርገዋል። የገቢ ግብር አዋጁ የግብር ስሌት መሰረትን ያስቀመጠው ገቢ እና ወጪን እንዲሁም ትርፍን መሰረት አድርጎ ነው። ጠበቃ ግን ትርፍን መሰረት አድርጎ አይደለም አንድ ጉዳይ የሚይዘው ይህን መሰረት አድርጎ ጉዳይ ቢይዝ የስነምግባር ጥሰት ጥያቄ ያስነሳል። የወጪ አያያዝን በሚመለከት የትኩረት ቡድኑ ተሳታፊዎች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታነትን በፅኑ ተቃውመው ግዴታ ከሆነ ጠበቃው ካፒታሉ እራሱ እንደመሆኑ መጠን እና የስራው አይነት ለየት ስለሚል ከላይ የተጠቀሱት ወጪዎች በሙሉ እንደወጪ መያዝ አለባቸው ብለው ምላሽ ሰጥተዋል።[75]

በተመሳሳይ የትኩረት ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የጥብቅና ወጪ አያያዝ አሁን ካለው የአካውንቲንግ ስታንዳርዶች ጋር የማይጣጣም መሆኑን በአሁኑ ወቅት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የIFRS ስርዐትን መሰረት በማድረግ ገልፀዋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎቹ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ በአሰራር ደረጃ ከጥብቅና ስራ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑን ጠቁመው ወጪ ይያዝ የሚለው ከስታንዳርዱ ጋር እንደማይጣጣም ጠቁመዋል። IFRS ተጠቅመው የሚሰሩት የሂሳብ መዝገብ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ መጠን ለማወቅ የሚደረገው ስሌት አምስት ነገሮችን ያካትታል። ይህም contract identification, obligation identification, price of transaction እና የመሳሰሉትን ለጥብቅና ስራ መለየት አይቻልም። ጠበቃ አንድን ጉዳይ ስይዝ ወጪዎቹ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አይቻልም። አንዳንድ ግዜ አንዱ ጉዳይ ሌላውን እየደጎመ (subsidize) ነው የሚቀጥለው። ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር የሚጣልበት መጠን ለይቶ

[74] የትኩረት ቡድን ውይይት, የፌደራል ጠበቆች ማህበር ቢሮ, ጥቅምት 11, 2015, 8፡00 ሰዐት::

[75] ዝኒ ከማሁ።

ማወቅ አይቻልም። አንድን ጉዳይ በግዜ እና በገንዘብ ወጪ ምን ያህል እንደሚያስወጣ መወሰን አይቻልም። ግዜውን የሚወስነው ፍርድ ቤት ነው። ስለሆነም የግብር ስሌቱ ገቢን እና ወጪን መሰረት ያደረገ መሆን የለበትም።[76]

የወጪ አያያዝ እና የእርጅና ቅናሽን በሚመለከተ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሀላፊዎች የሚከተለውን ዝርዝር ምላሽ ሰጥተዋል። ስለእርጅና ቅናሽና ወጪ አያያዝ በተመለከተ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ከአንቀጽ 22 እሰከ 25 እና በፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ከአንቀጽ 27 እስከ 41 ስር ባሉት ድንጋጌዎች የሚሸፈን ነው።[77] እንዲሁም ይህን አዋጅና ደንብ ለማስፈጸም በገንዘብ ሚኒስቴር የወጣው ስለተቀናሽ ወጪዎች መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።[78] ይህም ሰንጠረዥ "ሐ" ስር የሚመደቡ ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ነው የሚል ነዉ።

ሀ. **የእርጅና ቅናሽ**

የግብር ከፋዩን በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው እና ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ለማድረግ እንደሚፈቀድለት በገቢ ግብር አዋጁ ላይ ተደንጓል። እንዲሁም ግብር ከፋዩ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ እንደሚሆን ሕጉ ይፈቅዳል። አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው ሀብት በከፊል የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት የተጠቀመበት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚደረገው ማስተካከያ ከግምት ውስጥ ገብቶ የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት በዋለው መጠን የእርጅና ቅናሽ እንደሚያዝ በሕጉ ተመላክቷል። ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ ምጣኔ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ላይ ተመልክቷል።[79] ዋጋቸው የሚቀንሱ ሀብቶች የሚባሉት ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸው የሚንቀሳቀሱ ሀብቶች ወይም

[76] ዝኒ ከማሁ።

[77] የሚንስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 410/2008፣ 23ኛ እትም፣ ቁጥር 82፣ ነሀሴ 18 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

[78] የገንዘብ ሚንስትር፣ ስለተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 207/2013።

[79] የሚንስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 410/2008፣ 23ኛ እትም፣ ቁጥር 82፣ ነሀሴ 18 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ሲሆኑ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ሃብቶችን የሚያካትት እንደሆነ በዚሁ አዋጅ ላይ ተመልክቷል፡፡

1. ከአንድ ዓመት የሚበልጥ የአገልግሎት ዘመን ያለው፣
2. በእርጅና ወይም ጊዜው በማለፉ ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ የሚችል እና
3. በከፊል ወይም በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት ጥቅም መዋል አለባቸው፡፡

በጥብቅና ስራ ላይ የእርጅና ቅናሽ በታክስ አወሳሰን ወቅት ከግምት እየገባ እንደማይፈጸም ግኝቱ አሳይቷል፡፡

ለ. ተቀናሽ የሚደረጉ ሌሎች ወጪዎች

ሌላው በግብር ዓመቱ ግብር ከሚከፈልበት ጠቅላላ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ ተቀናሽ እንዲደረግለት በገቢ ግብር ሕግ የተፈቀዱ ወጪዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነርሱም በንግድ ሥራው ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት እንዲሁም ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የወጣ ወጪ፣ የንግድ ስራውን ገቢ ለማግኘት በተበደረው ገንዘብ ላይ የሚከፈል የወለድ ወጪ፣ ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች እና በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች በተቀናሽ እንደሚያዙ በሕጉ ላይ ተመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም ተቀናሽ የሚደረግለት ሃብት በግብር ከፋዩ ስም የተመዘገበ መሆን እንደሚገባው የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ ላይ ተመልክቷል፡፡

ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ያለውን አፈጻጸም ስንመለከት በጥብቅና አገልግሎት የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በሰንጠረዥ ″ሐ″ ስር የሚመደቡ ስለመሆኑ ከቢሮው ያገኘነው መረጃ ያሳያል። በመሆኑም በሕጉ የተፈቀደው ወጪ እና የእርጅና ቅናሽ እንደማንኛውም ግብር ከፋይ ጠበቆችም በተመሳሳይ ሁኔታ መስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ይህም የሂሳብ መዝገብ የሚይዙ ግብር ከፋዮች ተቀባይነት ባለው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ መሰረት እስካቀረቡ ድረስ ወጪው ባቀረቡት አግባብ ተቀናሽ እንደሚደረግላቸው ተገልጸልናል፡፡ ነገር ግን በግብር ከፋዩ የቀረበው የሂሳብ መዝገብ በባለስልጣኑ ውድቅ በሚደረግበት ጊዜ እና ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት የወጣ ወጪ መኖሩ ከታመነበት በሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 መሰረት ለቋሚ የስራ ሃብት 70% እና ለሌች ወጪዎች ደግሞ

65% ወጪ በመያዝ በቀሪው ላይ ግብር የሚከፈልበት ስለመሆኑ መረዳት ተችሏል።[80] የሂሳብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ግን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ መሰረት በግብር ዓመቱ ከተገኘው ግብር ከሚከፈልበት ጠቅላላ ገቢ ውስጥ 75% በወጪ እንደሚያዝና ቀሪው 25% ደግሞ በንግድ ስራ ገቢ መሰረት በተቀመጠው መጣኔ መሰረት ግብር የሚከፈልበት መሆኑ ተገልጿል።[81]

የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የእርጅና ቅናሽ አፈጻጸም በተመለከተ የእርጅና ቅናሽ እንዲደረግበት የተጠየቀው የንግድ ስራ ሃብት ከግብር ከፋዩ የግል ሃብት የተለየ መሆን እንደሚገባው ከቢሮው ያገኘነው መረጃ ያሳያል። ይህም ተቀባይነት ባለው የሂሳብ አያያዝ መርህ መሰረት የዳበረ አሰራር እንደሆነ ተብራርቷል፡ ፡ ይህ ማለት ግብር ከፋዩ የንግድ ምዝገባ ማድረግና ፍቃድ ማውጣት እንዲሁም የእርጅና ቅናሽ የሚደረግበትን ንብረት የማስመዝገብና የንግድ ስራ ሃብቱን ከግል ንብረቱ መለየት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ጠበቆች የንግድ ምዝገባ የማያደርጉና ፍቃድ የማያወጡ በመሆናቸው የሚጠቀሙት መኪና ኮድ 2 በመሆኑ በግብር አወሳሰን ጊዜ የእርጅና ቅናሽ አይያዝላቸውም። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለመኪናቸው የሚያወጡት የጥገና፣የነዳጅና የቅባት ወጪዎችም ተቀናሽ እንደማይደረግላቸው ያገኘነው መረጃ ያሳያል።የስልክ ወጪዎችም በተመሳሳይ ምክንያት ተቀናሽ የማይደረጉ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

3.4. ስለ ደረሰኝ ምንነት፣ ዓይነትና አጠቃቀም

የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19 እና 20 ስንመለከት ስሪታቸውን መሰረት በማድረግ በአጠቃላይ ሁለት የደረሰኝ ዓይነቶች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል።[82] እነርሱም በማተሚያ ቤት የሚታተም የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ እና በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አማካኝነት የሚሰጥ ደረሰኝ ነው፡ ፡ በማተሚያ ቤት የሚታተም ደረሰኝን በተመለከተ አንድ በስሙ ደረሰኝ እንዲታተምለት የሚፈልግ ግብር ከፋይ የደረሰኞቹን አይነትና ብዛት ለባለስልጣኑ የማሳወቅ እና ደረሰኙን የሚያትመው ድርጅት ደግሞ ደረሰኞቹ በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን የተፈቀዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19 ድንጋጌ ያዝዛል።[83] ይህ ማለት የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የማያውቀውን

[80] የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ 176/2014.
[81] የሚንስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 410/2008፣ 23ኛ እትም፣ ቁጥር 82፣ ነሀሴ 18 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።
[82] የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008፣ 22ኛ አመት ቁጥር 103፣ ነሀሴ 14 2008፣ አዲስ አበባ።
[83] ዝኒ ከማሁ።

ደረሰኝ መጠቀም አይቻልም ማለት ነው። ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በገቢዎች ሚኒስቴር የወጣው የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 165/2011 በማተሚያ ቤት ስለሚታተሙ ደረሰኞች ምንነትና ዓይነት ዝርዝር ጉዳዮችን ይዟል።[84] በሌላ በኩል የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በተመለከተ የታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 20 ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደሚያወጣ በደነገገው መሰረት ደንብ ቁጥር 139/1999 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል።[85]


ደረሰኝ እንዲጠቀሙ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች

የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19 (3) ማንኛውም የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ደንግጓል።[86] የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የሚባሉት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 82 መሰረት የደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ ግብር ከፋዮች እንደሆኑ ተመልክቷል።[87] የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች በፍላጎታቸው የሂሳብ መዝገብ የሚይዙ ከሆነ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እነርሱንም የሚያካትት ይሆናል። የሂሳብ መዝገብ የመያዝና ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ የስራ ዘርፍን መሰረት ያደረገ ሳይሆን ዓመታዊ የገቢ መጠንን መሰረት በማድረግ የሚመነጭ በመሆኑ ጠበቆችም በሕጉ ከተጠቀሰው መጥን በላይ ገቢ የሚያገኙ ከሆነ የሒሳብ መዝገብ የመያዝና ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ በቀድሞው የፌዴራል ጠበቆች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አዋጅና ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጣው (አሁንም ባልተሸረው) የጠበቆች የስነ ምግባር ደንብ መሠረት ጠበቆች ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው። በእነዚህ ህግና ደንብ መሠረት ጠበቆች ከደንበኞቸው ለተቀበሉት የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ አለመስጠት እንደ አንድ የዲስፕሊን ጥፋት በመሆኑ የሚያስቀጣ ነው።

[84] ገቢዎች ሚንስትር፣ የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 165/2011፣ አዲስ አበባ።
[85] በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999፣ 13ኛ አመት ቁጥር 48፣ ጥር 18 ቀን፣ አዲስ አበባ።
[86] የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008፣ 22ኛ አመት ቁጥር 103፣ ነሀሴ 14 2008፣ አዲስ አበባ።
[87] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፣ አንቀፅ 9፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 104፣ ነሀሴ 2 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

በዚሁ መሰረት ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት የሚሰጠው የደረሰኝ ዓይነት በማተሚያ ቤት የታተመ የማኑዋል ደረሰኝ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመጠቀም የሚገኝ ደረሰኝ ይሆናል። ይሁን እንጂ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሁሉም ግብር ከፋዮች ለመጠቀም አይገደዱም። ከዚህ አንጻር የገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ ሚገደዱ ግብር ከፋዮችን በመመሪያ እንደሚለይ ወይም እንደሚወስን በደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል።[88] በዚሁ መነሻ የገቢዎች ሚኒስቴር በመመሪያ እንዲወስን የታዘዘ ቢሆንም በ2010 ዓ/ም ባስተላለፈው ሰርኩላር ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም ከማይገደዱ የስራ ዘርፎች ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል። ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ እያለበት ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ ግብር ከፋይ የወንጀል ተጠያቂነት ጭምር የሚያስከትል ስለመሆኑ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 ላይ ተመልክቷል።[89]

ከዚህ አንጻር ጠበቆች በሚሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ለሚከፈላቸው ክፍያ ደረሰኝ እንዲቆርጡ የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የሚያስገድዳቸው መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ የተዘጋጀውን መጠይቅ ከሞሉ ጠበቆች ውስጥ አብላጫው ደረሰኝ እንዲጠቀሙ የሚገደዱ ስለመሆኑ መልስ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ መላሾች የማይገደዱ ስለመሆኑ መልስ ሰጥተዋል።




ምስል 8 መልሶቹን በመቶኛ ያሳያል።

[88] በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999፣ 13ኛ አመት ቁጥር 48፣ ጥር 18 ቀን፣ አዲስ አበባ።

[89] የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008፣ 22ኛ አመት ቁጥር 103፣ ነሀሴ 14 2008፣ አዲስ አበባ።:

ይህን ምለሽ በሁለት መንገድ ማየት ያስፈልጋል። የመጀመሪያው መጠይቁን የሞሉት አብላጫው ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚጠበቅባቸው የደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ ግብር ከፋዮች መሆናቸውን ያሳያል። በዚህ መሰረት ግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት በዚህ አግባብ ደረሰኝ እንዲይዙ ማስገደዱ የሚያስነቅፍ አይደለም። ሁለተኛው ደረሰኝ ለመያዝ አንገደድም ያሉት ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የማይጠበቅባቸው የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። በሕጉ ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ ሳይኖርባቸው ደረሰኝ እንዲጠቀሙ በገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የተገደዱ ጠበቆች ስለመኖራቸው በመጠይቁ የተሰጠ ምላሽ የለም። በመሆኑም ይህ ምላሽ ከደረሰኝ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከክፍለ ከተማ ክፍለ ከተማ የአሰራር ወጥነት አለመኖሩን አያሳይም።


በሌላ በኩል መጠይቁን ከሞሉት ጠበቆች ውስጥ ከ75% በላይ የሚሆኑት በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ፍቃድ የታተመ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ የተቀሩት ደግሞ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳርያ የሚጠቀሙ ስለመሆኑ ምላሽ ሰጥተዋል። ጥቂቶች ደግሞ በሌላ መንገድ ደረሰኝ እንደሚቆርጡ ገልፀዋል።



ምስል 9 የተሳታፊዎችን ምላሽ በመቶኛ ያሳያል።


አብዛኛው መላሽ በገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ፍቃድ የታተመ የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ የሚጠቀም ከመሆኑ አንጻር አብዛኛው ግብር ከፋይ ጠበቃ ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል። የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙ መላሾች ጥቂት መሆናቸው አንድም ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም አይጠበቅባቸውም ብሎ የገቢዎች ሚኒስቴር ካስተላለፈው ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ተመላሽ በመደረጉ ወይም ደግሞ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በየዕለቱ የማይሰበሰብ ከመሆኑ አንጻር ምቹ ባለመሆኑ ምክንያት በጠበቆች የማይመረጥ መሆኑን ያሳያል። የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ

የሌለባቸው በሚል ገቢዎች ሚኒስቴር ያወጣው ዝርዝር ውስጥ ጠበቆች የተካተተ ቢሆንም በፈቃደኝት መጠቀም ሚፈልግ ግብር ከፋይን የሚከለክል አይደለም። በዚሁ አግባብ በፈቃዳቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙ ጠበቆች እንዳሉ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ይቻላል። ደረሰኝ መቁረጥ በመገደዳቸው የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ችግር መኖር አለመኖሩን ተጠይቀው አብዛኛው መላሾች ችግር የለም ብለው የመለሱ ሲሆን ጥቂት መላሾች ግን ችግር የሚያስከትል እንደሆነ ምላሽ ሰጥተዋል።




ምስል 10 የመላሾችን መልስ በመቶኛ ያሳያል።

ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው አብዛኛው ጠበቃ በህጉ የተቀመጠውን ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ እንደሚያከብርና ተግባራዊ እንደሚደርግ ያሳያል። በሌላ ቡኩል ደግሞ ጠበቆች ደረሰኝ እንዲጠቀሙ ማስገደድ የጥብቅና አገልግሎት እንደንግድ ስራ የሚያስቆጥር መሆኑ፣ በሚቆረጠው ደረሰኝ አማካኝነት የተርን ኦቨርታክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስብ መደረጉ በተጠቃሚው ላይ የዋጋ ጭማሪ በማስከተል የፍትህ ተደራሽነትን የሚገድብ መሆኑ፣ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በየዕለቱ የሚሰበሰብ አለመሆኑ ከግምት ሳይገባ ለገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት በየጊዜው ሪፖርት እንዲደደረግ መደረጉ፣ ደረሰኝ የተቆረጠበት ክፍያ ተመላሽ ቢደረግ ግብሩን ተቀናሽ ማድረግ የማይቻል መሆኑ፣ ከደረሰኝ መቁረጥ ጋር በተያያዥነት የሚመጣው የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ከጥብቅና ስራ ጋር የማይሄድ መሆኑ፣ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ጨምሮ ወጪ ኪሳራ በፍርድ ቤት ሲጠየቅ የሚቀነስበት ሁኔታ መኖሩ፣ በስልክ የሚሰጥ የማማከር አገልግሎት ላይ ደረሰኝ መቁረጥ የማይቻል መሆኑ እና የግለሰብ ደንበኞች፣ በጎ አድራጊ ተቋማት እና የውጪ ደንበኞች ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል ፍቃደኛ አለመሆናቸው በጥብቅና አገልግሎት ላይ ችግር የሚያስከትል እንደሆነ በተወሰኑ ጠበቆች የሚነሳ መሆኑን ያሳል። የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ግዴታ መሆን ወይም አለመሆኑን አስመልክቶ ተሳታፊዎች ለተጠየቁት ጥያቄ ከ89% በላይ የሆኑት መላሾች ግዴታ አለመሆኑን የጠቀሱ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ግዴታ መሆኑን ጠቅሰዋል።



ምስል 8 የመልሱን አሀዝ ያሳያል።

ቁጥሩ ትንሽ ቢሆንም የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ የሚያስገድድ ስለመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ያሳያል። ይህን በተመለከተ ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለመጠቀም የማይገደዱ የስራ መስኮች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ ከተደረገ በኋላ ማስገደዱ የሕግ መሰረት የለውም። የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ግዴታ መሆኑ በጥብቅና አገልግሎት ላይ የሚያስከትለው ችግር አለ ወይም የለም የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ አብላጫው መላሾች ችግር እንዳስከተለ ሲገልፁ የተቀሩት ችግር አላስከተለም ብለው መልሰዋል።



ምስል 9 መልሱን በአሀዝ ያሳያል።

የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ከሚጠበቅባቸው ጠበቆች ቁጥራቸው ከግማሽ ትንሽ ዝቅ የሚሉት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙ ስለመሆኑና በመጠቀማቸው የተለየ ችግር እንዳላስከተለባቸው የተሰጠው ምላሽ ያሳል። የጥብቅና አገልግሎት ስራ ላይ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀምን ግዴታ ማድረግ ከስራው ባህሪ ጋር አብሮ የሚሄድ አለመሆኑ እንደ ምክንያትነት ተጠቅሷል። በተጨማሪም

ለጠበቃው ክፍያ የሚሰበሰበው በየቀኑ ባለመሆኑ የዕለት ሪፖርት ማውጣት አስቸጋሪ መሆኑ፣ ማሽኑ በየወቅቱ መበላሸቱ፣ እና ለክፍያ ማሽኑን ይዞ መጓዝ ግዴታ መሆኑ የጠበቃውን ግዜ የሚገድል ነው የሚሉ ምላሾች ተሰጥተዋል። በዚህ ረገድ በጠበቆች የተነሳውን ምክንያት በተመለከተ ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዳይጠቀሙ የሚከለክል ሕግ አለመኖሩ እና የጠበቃ ስራ በየፍርድ ቤቱ እና ሌሎች ቦታዎች ተንቀሳቅሶ መሰራት ስላለበት በየቀኑ በቢሮ በመገኘት ዜድ ሪፖርት ማውጣት ያስቸግራል ለተባለው የዕለት ዜድ ሪፖረት ለማውጣትም ጠበቃው እራሱ የግድ ማውጣት ላያስፈልገው እንደሚችልና ማሽኑ እራሱ ፕሪንት እንዲያደርግ ማዘዝ ወይም ዜድ ሪፖርት ማውጫ ሰዓቱን መግፋት ስለሚቻል የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም የማያስችል ሁኔታ እንደሌለ አስረድተዋል። ይህ አይነቱ ችግር የሚመነጨው ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም ይገደዳሉ ወይም አይገደዱም የሚለውን ካለመገንዘብ ነው። ከላይ እንደተገለጸው ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለመጠቀም እንደማይገደዱ የገቢዎች ሚኒስቴር በ2010 ዓ/ም ባወጣው ሰርኩላር አስታወቋል። ይህ በሁለቱ ወገን ለተነሳው ሀሳብ መፍትሄ የሚሰጥ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ጠበቆች በገቢ መ/ቤቱ መመሪያ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ ካሽ ሬጅስተር መጠቀም ሳያስፈልጋቸው በባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ የታተሙ የእጅ በእጅ ደረሰኞች እንዲጠቀሙ ማድረግ ተገቢ ሆኗል።

3.5. የጥብቅና ስራ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች


የጥብቅና ስራን የሚመለከቱ ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ ናቸው። በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት አንድ ግብር ከፋይ ማናቸውም በ12 ወራት ውስጥ ግብር ያከናወነው ግብይት ከ500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ብር በላይ የሆነ ወይም በማናቸውም 12 ወራት ውስጥ የሚያከናውናቸው ግብይቶች 12 በመቶ ይሆናል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ አለበት።[90] በአዋጁ አንቀፅ 7(1) መሰረት ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ሰዎች በሚፈፅሟቸው ግብይቶች፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ አገልግሎቶች እንዲሁም ነፃ ከተደረጉት በስተቀር ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በ15 በመቶ ይጣላል።[91] የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጣልበት የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 8 እና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 ክፍል ሁለት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑ

[90] የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994፣ 8ኛ አመት ቁጥር 33፣ ሰኔ 17 ቀን 1994 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[91] ዝኒ ከማሁ።

ግብይቶችን ይደነግጋሉ።[92] በዚህም መሰረት የትምህርት፣ የህክምና፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የመጓጓዣን ጨምሮ የተለያዩ ግብይቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑበት አግባብ በእነዚህ ህጎች ተደንግጓል።

ሌላው ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር ተርን ኦቨር ታክስ ነው። በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 3 መሰረትለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ እና በአዋጁ ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ከተደረጉ ግብይቶች በስተቀር በሀገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች እና በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይየተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል።[93] ነነገር ግን የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 4 ዝቅተኛ ተርን ኦቨር የሚከፈልባቸውን ግብይቶች አስቀምጧል በዚህም መሰረት ለሀገር ውስጥ ለሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችም፣ የተቋራጮች አገልግሎቶች፣ የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ ትራክተሮች፣ እና የኮምባይን ሀርቨስተሮች አገልግሎቶች ተርን ኦቨር ታክስ የሚጣልባቸው 2 በሞቶ ብቻ ነው።[94]

የጥብቅና ስራ እንዳንድ ስራዎችን ከተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ መደረግን በተመለከተ ከ76% በላይ መላሾች ነፃ መደረግ አለበት ብለው የመለሱ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ነፃ መደረግ የለበትም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።



ምስል 13 ይህንኑ በአሀዝ ያሳያል።

በትኩረት ቡድን ውይይት ወቅት የጥብቅና አገልግሎት ልክ እንደ ትምህርት እና ህክምና አገልግሎት ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር ሊጣልበት እንደማይገባ መልሰዋል። ደንበኞች መብታቸውን ለሚጠይቁበት አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ መጠየቅ አግባብነት የለውም። ከዚህ አንጻር ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርን በተመለከተ የጥብቅና አገልግሎት በአዋጁ ነጻ ከተደረጉ የሙያ አገልግሎቶች ውስጥ እንዳልተካተተ እና ቫትም ሆነ ተርን ኦቨር ታክስ የሚሰበሰበው


[92] ዝኒ ከማሁ።
[93] የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣ 9ኛ አመት ቁጥር 21፣ ታህሳስ 22 ቀን 1995 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[94] ዝኒ ከማሁ።

አገልግሎቱን ከሚገዛው ሰው በመሆኑ በቀጥታ ጠበቆችን የሚመለከት እንዳልሆነ ተገልጿል። የጥብቅና አገልግሎት በሕጉ ከቫት ነጻ ያልሆነበት ምክነያት ሲጠቅሱ በአብዛኛው ማህበር ላይ ሰፊ ተጽዕኖ የማያሳድር በመሆኑ እና ጠበቃ ሳይኖር በፍርድ ቤት መከራከር የሚቻል በመሆኑ እና ነጻ የሕግ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ድጋፍ በመጠቀም ፍትህ ማግኘት እንደሚቻል ከቢሮው የተገኘው መረጃ ያሳያል። ስለሆነም ጠበቃ መቅጠር የሚፈልግ ሰው የመክፈል አቅም ያለው እስከሆነ ድረስ ቫት እና ቲኦቲ እንዲከፍል መደረጉ ተገቢ መሆኑን ከቢሮው የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ቫት እና ቲኦቲ ይቅር ቢባል እንኳን ጉዳዩቹ ተለይተው አንደየጉዳዩ መጠን እና ሁኔታ ለወሰን ይገባል የሚል ሀሳብ ተነስቷል። ከላይ በሕጉ እንደተመለከተው በጥብቅና አገልግሎት በሚገኝ ገቢ ላይ ከተርን ኦቨር እና ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነጻ አልተደረገም።

በዚህ ረገድ ገቢዎች ቢሮ እነዚህን ታክሶች መሰብሰቡ በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣ በመሆኑ የሚያስነቅፈው አይሆንም። ከዚህ አንጻር የሌሎች ሀገራት ልምድ ማየቱ ጠቃሚ ነው። ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርን በተመለከተ በአንድ አንድ የውጭ ሀገራት የጥብቅና የታክስ አስተዳደር ህጎችና አተገባበር ላይ ባደረግነው ጥናት ያሉ ልምዶች ያሳዩት ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ከህግ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ነጻ እንደሚደረጉ ወይም በቀነሰ ምጣኔ እንደሚስተናገዱ በጥናቱ ተመልክቷል። በህግ አገልግሎት ላይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የሚጥሉ ሀገራትም የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጫና የማያበዙ አነስተኛ ምጣኔ ያላቸውን የታክስ ምጣኔ ተግባራዊ ያደርጋሉ። ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ በህግ አገልግሎት ላይ የሚጣለው ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር በአገልግሎት ተጠቃሚው እና በድምሩም በፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አለው።

3.6. በተጨማሪ ሌላ ስራ የተሰማሩ ጠበቆች

ከጥብቅና ውጪ በሌሎች ስራዎች መሰማራታቸውን ተጠይቀው ከ90% በመቶ በላይ የሆኑት ተሳታፊዎች እንዳልተሰማሩ የመለሱ ሲሆን የተቀሩት ጥቂት መላሾች ቤት ማከራየት፣ መኪና ማከራየትን በመሳሰሉ መደበኛ ያልሆኑ ሌሎች ስራዎችም ጭምር መሰማራታቸውን ጠቅሰዋል።



ምስል 15 የመላሾቹን መልስ በመቶኛ ያሳያል።

ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው ቁጥራቸው በጣም ትንሽ የሆኑ ጠበቆች ከጥብቅና ሙያ በተጨማሪ በሌላ ገቢ በሚያስገኝ የስራ መስክ የተሰማሩ መኖራቸውን ያሳያል። ይሁን እንጂ ቁጥራቸው በጣም ትንሽ የሆኑት ደግሞ ግብር የሚከፈለው በአንድ የግብር መክፈያ መለያ በመሆኑ የተጋነነ ግብር እንደሚጣልባቸው አንስተዋል። በተጨማሪም የጥብቅና ፍቃድ እና የሌላው የንግድ ፍቃድ ማደሻ ግዜ አንድ አይነት ባለመሆኑ እድሳት ላይ መዛባት እንደፈጠረባቸው ገልፀዋል። በዚህ ረገድ ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ሌሎች ገቢዎችን በሚመለከት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሌላ የንግድ ስራ ዘርፍ የተሰማሩ ጠበቆች ግብር አከፋፈልን በተመለከተ የጥብቅና ስራው እና የንግዱ ስራ በተመሳሳይ ሰንጠረዥ የሚመደብ ከሆነ ግብሩ የሚከፈላው በተጠቃለለው ገቢ ላይ እንደሆነ ያገኘነው መረጃ ያሳያል። ነገር ግን ከጥብቅና በተጨማሪ የተያዘው ስራ ከሰንጠረዥ ሐ ውጪ ከሆነ ግብሩ የሚጣለውና የሚከፈለው ከጥብቅና አገልግሎት ግብር ጋር ተደምሮ እንደሆነ ተመልክቷል። ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እንዲያወጣ የተደረገበት ምክንያት ለአስተዳደራዊ ጉዳይ እንጂ ከሚከፈለው የግብር መጠን ጋር የሚያያዘው ነገር እንደሌለ በሕጉ ተመልክቷል። የግብር ማስታወቂያ እና ከግብር እዳ ነጻ ምስክር ወረቀት ማግኛ ጊዜ የተለያየ መሆኑ፤ የጥብቅና ስራ የሙያ ክብርን በሚነካ መልኩ ደረሰኞች ላይ "እከሌ የጥብቅናና የሽቀጣሽቀጥ መደብር...." መሰል አገላለጾች በደረሰኝ አጠቃቀም አንጻር በችግርነት ታይተዋል። የጥብቅና ስራ ሂሳቡም ለብቻው አለመሰራቱ በስራ ላይ ያሉ ህጎችን የሚጥስ እና ፍትሀዊነትን የማያሳካ ሆኖ ተገኝቷል፡

:

3.7. በህግ ድርጅቶች የግብር አከፋፈል ስርዓት

የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1249/2013 የህግ ድርጅቶች ማቋቋምን ይፈቅዳል።[95] በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 51 መሰረት ማንኛውም የጥብቅና ድርጅት ወይም የሽሪኮቹ የግብር አከፋፈል አግባብነት ባላቸው የሽርክና ማህበር የተመለከቱ የግብር ህጎች የሚወሰን ይሆናል የሚል ድንጋጌ አስቀምጧል።[96] በዚሁ ድንጋጌ መሰረት እናየገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 3 (1) (ሀ) መሰረት ማንኛውም ድርጅት ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ሲሆን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ 30 በመቶ ግብር ይከፍላል።[97] በተጨማሪም የደርጅቱ ሸሪኮች በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 51 (2) (ለ) መሰረት ከትርፍ ክፍፍሉ ላይ 10 በመቶ ግብር ይከፍላሉ።[98] ከዚህ ጋር ተያይዞ የጥብቅና ድርጅት ሸሪኮች በየግላቸው የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው በመሆኑ የሚከፍሉት ግብር የትርፍ ክፍፍል ግብር ብቻ ይሁን ወይም ሌላ የግብር ግዴታ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም።

በግል እና በህግ ድርጅት የሚሰሩ ጠበቆችን የግብር አከፋፈል በተመለከተ የትኩረት ቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች በሁለቱም አግባብ የሚሰሩ ስራዎች አንድ አይነት መሆናቸውን ገልፀው ስራዎቹ ማማከር እና ጥብቅናን መሰረት ያደረጉ በመሆኑ የግብር አከፋፈል ስርዐቱም የተለየ መሆን የለበትም ብለዋል። የጥብቅና ድርጅቶችም እንደ ሀጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም የሚሰጠው አገልግሎት ከግለሰብ ጠበቃ የተለየ አይደለም። ከህጉ አግባብ አንፃር አዋጁ ላይ ችግር አለ። እያንዳንዱ ጠበቃ ግብሩን በግሉ እንዲከፍል ይላል። አንድ ድርጅት በማህበር ከተቋቋመ በኋላ ሀጋዊ ሰውነት ካገኘ በኋላ በየግሉ ግብር ይክፈል የተባለበት አግባብ የሚያስኬድ አይደለም። ግብር ለየብቻ የሚከፈል ከሆነ ድርጅት ማቋቋም ጥቅሙ ምን ላይ ነው? የሚል ሀሳብ ተነስቷል። ድርጅት ማቋቋም የሚፈልጉ አብዛኞቹ ጠበቆች በዚህ ረገድ የህጉ ግልፅ አለመሆን ድርጅት ከመመስረት እንዲታቀቡ ዕደረገ ስለመሆኑ ተነስቷል። ከተነሱት ችግሮች አንጻር የጥብቅና አስተዳደር አዋጁ ድንጋጌ ማየት ተገቢ ነው። ይህም የአዋጁ አንቀጽ 20(1) ላይ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃድን ለማሳደስ የግብር ክሊራንስ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባቸው ይደነግጋል።[99] በዚሁ አዋጅ አንቀጽ

[95] የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አስጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013፣ አንቀፅ 39 (5) ፣ 27ኛ አመት ቁጥር 42፣ ሀምሌ 28 ቀን 2013፣ አዲስ አበባ።

[96] ዝኒ ከማሁ።

[97] የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፣ አንቀፅ 9፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ አመት፣ ቁጥር 104፣ ነሀሴ 2 ቀን 2008፣ አዲስ አበባ።

[98] ዝኒ ከማሁ።

[99] ዝኒ ከማሁ።

2(1) እና (4) ክፍል ውስጥ ጠበቃ የግል የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን እና የጥብቅና ድርጅት ደግሞ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል።[100] ይህ የሚያሳየው ጠበቃ እና የጥብቅና ድርጅት ሁለት የተለያዩ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት እንደሆኑ ነው። የትብቅና ድርጅት ሀልውና የሚኖረው ድርጅቱን በመሰረቱት አባላት ስምምነት ቢሆንም ለተገኘው ገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት የድርጅቱ ነው። በተጨማሪም አባለቱ ለሚደርሳቸው የትርፍ ክፍያ ላይ 10% ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ በመያዝ ለግብር ባለስልጣኑ የማስገባት ኃላፊነት የድርጅቱ ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ ሙሉ ኃላፊነቱ የድርጅቱ በመሆኑ አባላት በግላቸው ግብር መክፈል አይጠበቅባቸውም። አባላቶቹ የሚሰሩት ስለድርጅቱ እስከሆነ ድረስ የድርጅቱ የታክስ ክሊራንስ ለአባላቶቹ ጭምር የሚያገለግል ስለመሆኑ ግልጽ ነው። እዚህ ላይ የተነሳው ስጋት የድርጅቱ አባላት የሙያ ፍቃዳቸውን በሚያሳድሱበት ጊዜ በድጋሚ በየግላቸው የግብር ክሊራንስ ሊጠየቁ ችላሉ የሚል ነው። ይህ ደግሞ በአንድ ገቢ ላይ ሁለተኛ ግብር መክፈል (double taxation) ያስከትላል የሚል ነው። ይሁን እንጂ የገቢ ግብር ሕጉ ይህን የማይፈቅድ በመሆኑ የተነሳው ስጋት የሚፈጠርበት ዕድል የለም። በሌላ በኩል የጥብቅና ድርጅቶች በቅርቡ የተመሰረቱ ከመሆኑ አንጻር ተባለው ስጋት በተግባር ያልተፈተሸ መሆኑ ስጋቱ የተረጋገጠ አይደለም።

የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ግዴታ ስለሚሆን በድርጅት መቋቋምን ከአስቸጋሪ እንደሆነ የተነሳውን ሃሳብ በተመለከተ ጠበቆች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለመጠቀም የማይገደዱ ስለመሆኑ የገቢዎች ሚኒስቴር በሰርኩላር የተላላፈ በመሆኑ በተመሳሳይ ለጥብቅና ድርጅቶችም ተፈጻሚ የማይሆንብት ምክንያት አይኖርም። የሂሳብ መዝገብ አያያዝ የወጪ አመዘጋገብ ችግር ድርጅቱንም ይገጥመዋል። ለድርጅቶችም እንደ ግለሰብ ጠበቆች progressive taxation with schedule መሆን አለበት። አሁን ባለው ሁኔታ ድርጅቶች አዲስ እየተቋቋሙ በመሆኑ የግብር ሁኔታውን እንዲነው ብሎ ለማለት አስቸጋሪ ነው።

[100] ዝኒ ከማሁ።

ምእራፍ-4

4. መደምደሚያ እና መጠቁሞች፤

4.1. መደምደሚያ/Conclusion/:

ይህ ጥናት በፌደራል ደረጃ የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች ከግብር አከፋፈል ስርአቱ ጋር የተያያዙና ለበርካታ አመታት እየተንከባለሉ ያሉ የወጥነት፤ የፍትሃዊነት፤ የህግ አተገባበርና ሌሎች የአሰራር ክፍተቶች በተመለከተ ችግሮቹን ለመለየት እንዲሁም ለዘመናት ሲንከባለል የቆየውን ችግር በመሰረታዊነት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ለመጠቆም የተዘጋጀ ጥናት ነው። በጥናቱ የሀገር ውስጥ ህጎች፣ የፌደራልና የክልሎች ልምድ፤ የውጭ ሀገራት ተሞክሮዎች በሰፊው ተዳሰዋል። በሌላ በኩል በዘርፉ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችና የጥናት ውጤቶች ተዳሰዋል። በስራ ላይ ላሉ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች መጠይቆችን በመበተን ግብአት በመሰብሰብ፤ ከተመረጡ ጠበቆች ጋር የትኩረት ቡድን ውይይት ተከናውኗል። ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ሀላፊዎች፤ እና የኦሮሚያ ክልል የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተከናውኗል። በተጨማሪም ከሌሎች ሀገራት ከሚገኙ የጠበቆች ማህበር አመራሮች የውጭ ሀገራት ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ጋር ጥልቀት ያለው ቃለምልልስ ተደርጓል።

በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት የሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

1. ጸንተው ባሉ የህግ ማእቀፎች መሰረት የጥብቅና ስራ የንግድ ስራ አለመሆኑ ከመደምደሚያ ተደርሷል። ለዚህም የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁ. 1249/2013፤ የተሻሻለው የንግድ ህግ፤ የንግድ ምዝገባ አዋጁን እንደማሳያ ተጠቅሰዋል። የጥብቅና ሙያ ለየት ያሉ ባህሪያት ያሉት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለይም ከሌላው ግብር ከፋይ በተለየ የነፃ አገልግሎት፣ የአገልግሎት ክፍያ ገደብ እንዲሁም ጠንከር ያለ የሙያ ቁጥጥር፤ ከፍ ያለ ማህበራዊ ሀላፊነቶችን የሚያካትት በመሆኑ በግብር አጣጣል እና አከፋፈል ወቅት በግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የሚደረሰው ውሳኔ የጥብቅና ስራን ባህሪያት ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። የጥብቅና ሙያ አገልግሎት በግለሰብም ተሰጠ በድርጅት የንግድ ስራ አይደለም። ነገር ግን፣ ለግብር አሰባሰብ ሲባል አገልግሎቱ ከሌሎች ንግድ ስራዎች ጋር በተመሳሳይ በሰንጠረዥ ሐ የሚስተናገድ ነዉ።

2. በአመት ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ኖሯቸው ደረጃ "ሀ" ስር የተመደቡ ግብር ከፋይ ጠበቆች እና ከ500 ሺህ ብር በላይ አመታዊ ገቢ ያላቸው ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ይገደዳሉ። የሂሳብ መዝገብ መያዝ ወጪን እና ገቢን ማስፈር የሚጠይቅ ሲሆን ጠበቆች ከጥብቅና ስራ የሚያገኙት ቅደመ ክፍያ በሂሳብ መዝገብ የሚሰፍርበት አግባብ ከሂሳብ አሰራር መርሆች የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ በተጨማሪ የግብር ሕጉ እንደ ጥብቅና ስራ ያሉ ስራዎች በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱበት የህግ ድንጋጌዎች የሌሉት በመሆኑ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ በሚገደድበት ወቅት ወጪያቸውን ለማስያዝ የማይቻል መሆኑ ወጪን ያለካተተ ገቢን ብቻ የያዘ የሂሳብ መዝገብ ደግሞ ፍትሀዊ አለመሆኑ ከመደምደሚያ ላይ ተደርሷል።
3. የጠበቆች የስራ ውል በአብዛኛው የረዥም ጊዜ ውል ነው (ከ12 ወራት የሚሻገር)፤ ሆኖም የገቢ ግብር አዋጁ አንቀፅ 32 ላይ የተቀመጠው የረዥም ጊዜ ውል አተገባበር ለጠበቆች ተግባራዊ መደረግ አይችልም። በግብር ዘመኑ የተሰራውና የሚቀረው የስራ መጠን በመቶኛ እየተለካ ሊቀመጥ አይችልም። በጥብቅና ስራ አንድ ጠበቃ ቅድሚያ ክፍያ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩ ለምን ያህል ግዜ እንደሚቆይ እና በትክክል ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ ማወቅ እጅግ አዳጋች ነው። እንዲዘህ አይነት አሰራር ባልተዘረጋበት እና የጥብቅና ስራው በብዙ አጋጣሚዎች ከ7-10 አመት ድረስ የሚቆይ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ጉዳዮች የወጣው ወጪ/ድካም ከግምት ውስጥ ሳገባ ጠበቃው ያገኘው ገቢ በሙሉ እንደ ተጣራ ትርፍ ተቆጥሮ ግብር እንዲከፍል ይገደዳል። ይህም ከጥብቅና ስራ የባለሙያው ትክክለኛ የተጣራ ገቢ ታውቆ ታክስ ለመጣል አዳጋች እንዳደረገው መገንዘብ ተችሏል፡ :
4. የወጪ አያያዝን አስመልክቶ ከነዳጅ ወጪ፣ የስልክ፤ የኢንተርኔት እና መሰል ወጪዎችን ማያያዝ አይቻልም። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት በግብር ከፋዮች ላይ የሚጣለው ግብር በዋናነት ፍትሀዊ መሆን እንዳለበት የተደነገገ ሆኖ ሳለ ወጪን ሳንይዝ ገቢን መሰረት አድርገን ግብር እንወስናለን ማለት ፍትሀዊነትን የማያሳካ መሆኑ ከመደምደሚያ ተደርሷል።
5. የጠበቆች ደረሰኝ የመቁረጥ ግዴታን በተመለከተ፣ አንዳንድ ጠበቆች ደረሰኝ መቁረጥ ግዴታ አለመሆኑን ይጥቀሱ እንጂ ደረሰኝ መቁረጥ የአንድ ግብር ከፋይ ጠበቃ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የስነምግባር ግዴታም ጭምር ነው። በሌሎች ሀገራት የተደረጉ ምልከታዎችም ይህንኑ ያጠናከሩ ሆነው ተገኝተዋል። አንድ ጠበቃ ደረሰኝ ሳይቆርጥ ቀርቶ የሚደርስበት ተጠያቂነት የግብር ህግን

በመተላለፍ ብቻ ሳይሆን የስነምግባር ደንብ ጥሰትም ጭምር ነው። በዚህ ረገድ ጠበቆች ምንም እንኳን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መቁረጥ ባይገደዱም ለሚሰጡት አገልግሎት ህጋዊ የማኑዋል ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

6. በጥብቅና ውል መሰረት ግብር በመክፈል የሚስተናገዱ ጠበቆችን በተመለከተ፣ ምንም እንኳን ውል ክፍያ በቅድሚያ ክፍያ እና ቀጣይ ክፍያዎች የተከፋፈለ ቢሆንም፣ አንድ አንድ ወረዳዎች ውሉ ላይ በተቀመጠው መጠን መሰረት ግብር እንዲከፈል ያስገድዳሉ። ይህም ግብር ከፋዩ ጠበቃ ገና ባልተቀበለው ክፍያ ላይ ግብር እንዲከፍል ያስገድደዋል።
7. ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርን በተመለከተ ጠበቆች የሚሰጡት አገልግሎት ከፍትህ ጋር እጅጉን የተቆራኘ ስለሆነ በአገልግሎቱ ክፍያ ላይ ተርን ኦቨር ታክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስን የመሰሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች ግዴታ መሆን የአገልግሎቱን ዋጋውን ውድ ያደርገዋል፣ የአገልግሎቱ ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። በውጭ ሀገራት የጥብቅና የታክስ አስተዳደር ህጎችና አተገባበር ላይ ባደረግነው ጥናት ያሉ ልምዶች ያሳዩት ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ከህግ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በቀነሰ ምጣኔ reduced rate እንደሚስተናገዱ በጥናቱ ተመልክቷል። በህግ አገልግሎት ላይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የሚጥሉ ሀገራትም የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጫና የማያበዙ አነስተኛ ምጣኔ ያላቸውን የታክስ ምጣኔ ተግባራዊ ያደርጋሉ። ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ በህግ አገልግሎት ላይ የሚጣለው ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር በአገልግሎት ተጠቃሚው እና በድምሩም በፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አለው።
8. ከጥብቅና ስራ በተጨማሪ ሌሎች ስራዎችን የሚሰሩ ጠበቆች ከግብር አከፋፈል ጋር ተያይዞ በተለያዩ መንገዶች ችግር ሲገጥማቸው ይስተዋላል። አንደኛው በፍቃድ ማደሻ ግዜ መለያየት ምክንያት የፍቃድ እድሳት መዛነፍ የሚያጋጥማቸው ሲሆን ሁለተኛው ሁሉም የገቢ ግብር በአንድ ቲን ሰርተኬት ስለሚስተናገድ ተጨማሪ ገቢዎች የጥብቅና ገቢው ላይ ተደምሮ ከፍተኛ ግብር እንዲጣልባቸው ምክንያት ሆኗል። በሌላ በኩል ግብር ክሊራንሱም በተለያየ ሆኖ ለየዘርፉ ራሱን ችሎ ሊሰጣቸው ሲገባ አልሆነም፤ ሂሳቡም በአንድ ቲን ነምበር በሁለት የተለያየ መዝገብ ሊወሰን ባለመቻሉ የተፈጠረው ችግር መፍትሄ የሚፈልግ ነው። ከሁሉም በላይ የጥብቅና ስራን የሙያ ክብር በሚጎዳ መልኩ ሁለቱን ስራዎች በአንድ ደረሰኝ እንዲሰሩ መደረጉ ተገቢነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል።

የጥብቅና ድርጅቶችን በተመለከተም፡-

1. አሁን ባለው አሰራር የጥብቅና ድርጅቶች ከሚያገኙት አመታዊ ትርፍ ላይ በአጠቃላይ 37% የሚሆን ግብር ይከፍላሉ። የድርጅት ግብር በ30% ምጣኔ በግብር አመቱ ካገኙት ትርፍ ላይ ሲከፍሉ፣ ከዚህ በኋላ የሚተርፈው 70% ገቢ ለእያንዳንዱ አባል (ሸሪክ) የትርፍ ክፍፍል ሲደረግ 10% ግብር ይከፈላል።
2. የጥብቅና ድርጅቶች የሚቋቋሙት እንደሽርክና ማህበር በመሆኑ እያንዳንዱ አባል (ሸሪክ) የጥብቅና ሙያ ያለው እና የሕግ አገልግሎት በግሉ የማይሰጥ ነው። ይህም ማለት እያንዳንዱ አባል እንደ ባለአክሲዮን ማህበር ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን ሙያውን እና ሙሉ ጊዜውንም በማዋጣት የድርጅቱ እለታዊ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደርጋል። ከእዚህ አንፃር የአባላት ትርፍ ክፍፍል ላይ የሚጣል ግብር (dividend tax) በሽርክና ማህበር አባላት ላይ መጣሉም አግባብነት የለውም።
3. የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ላይ እና የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ላይ የተቀመጠው የተቀናሽ ወጪዎች አመዳደብ ለጥብቅና ድርጅቶችም ተግባራዊ ይደረጋል። ሆኖም ይህ አሰራር የጥብቅና ስራ ልዩ ባህርያት አንፃር ለጥብቅና ድርጅቶች ፍትሐዊ እና አመቺ የገቢ ግብር ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል። ይህም የሆነው በጥብቅና ድርጅቶች አዲስ መሆን እና የግብር ሰብሳቢ አካላት የተቀናሽ ወጪዎችን በጠባቡ ሊተረጉሙ መቻላቸው ነው። ስለሆነም የጥብቅና ድርጅቶች ተቀናሽ ወጪዎች በዝርዝር ሊቀመጡ ይገባል።

4.2. መጠቁም /Recommendations/

የዚህን ጥናት ግኝቶችን እና መደምደሚያዎችን መሰረት በማድረግ በጥናቱ ለሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት የሚከተሉትን መጠቁሞች ተሰጥተዋል።

1. የግለሰብ ጠበቆችና የህግ አማካሪዎችን ግብር አከፋፈል በተመለከተ፡-
    1.1. የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮች የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ቢሆንም ከላይ በተገለፀው መሰረት ከጥብቅና ስራ ልዩ ባህርይ አንፃር ወጪያቸው የሚያዝበት ህግ ባለመኖሩ እና አስራር ባልተዘረጋበት ሁኔታ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ሊገደዱ የማይገባ በመሆኑ ይሄው የስራውን ባህሪ ያገናዘበ ተገቢ የሆነ አሠራር በመመሪያ መልክ እስከሚወጣበት

ጊዜ ድረስ ወጥነት ባለው መልኩ በመመሪያ ቁጥር 138/2010 መሰረት የሂሳብ መዝገብ ያልያዙ ግብር ከፋዮች በሚስተናገዱበት አግባብ ጠበቆች በቁርጥ ግብር እንዲከፍሉ ሊደረግ ይገባል። ይህም የጠበቆች 75 በመቶ ገቢ እንደወጪ ተቆጥሮ በቀሪው 25 በመቶ ገቢ ላይ በሚጣል ግብር እንዲከፈል በኢ.ፌ.ድ.ሪ የገንዘብ ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ መውጣት እንደሚኖርበት ምክረሀሳብ ቀርቧል።

1.2. ጠበቆች የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸው እንዲሁም በሌላ የገቢ ሰንጠረዥ አይስተናገዱም የሚለውን አማራጭ ብንወስድ ደግሞ የጥብቅና ሙያ ልዩ ባህርያት ከግምት ገብተው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ሊወጣለት የሚገባ ነው። በዚህም መመሪያ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ አጠቃላይ የጠበቃ ወጪዎች፤ የእርጅና ቅናሽ፤ ካፒታሉ/እውቀቱ/ጉልበቱ... በሂሳብ መዝገብ ከግምት ገብተው በተቀናሽ የሚስተናገዱበት አግባብ ሊቀመጥ እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.3. ከላይ የተመለከተው አማራጭ የሚወሰድ ቢሆን ጠበቆችን ከንግድ ፍቃድ፤ የመኪና ታርጋ አይነት፤ የስልክ እና መሰል በነጋዴ ላይ ለግብር አወሳሰን ግብአት የሚሆኑ ፍሬ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የህግ ማእቀፎች ማሻሻያ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.4. ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርን በተመለከተም በበርካታ ሀገራት ልምድ እንደታየው የቀነሰ የግብር ምጣኔ /Reduced Rate/ ተግባራዊ እንዲደረግ ምክረ ሃሳብ ቀርቧል። በተመሳሳይ በሀገር ውስጥ ልምድ ከታዩት "በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ፤ የሥራ ተቋራጮች እና መሰል ዘርፎች የቲኦቲ ምጣኔ 2 በመቶ እንደመሆኑ ከነዚሁ ዘርፎች ጋር የጥብቅና ስራ ዘርፍ በተመሳሳይ ሊታይ የሚችል ነው። የተጨማሪ እሴት ታክስንም በተመለከተ በተመሳሳይ የቀነሰ የታክስ ምጣኔ (5 በመቶ) ድረስ የማድረጉ አማራጭ የህግ አገልግሎትን ተደራሽነት የሚያሰፋና ከተጠቃሚው ህዝብ ላይ ጫናውን የሚጋራ ተመራጭ አሰራር ስለመሆኑ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.5. አዲስ እየተረቀቀ ባለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ ይህው የቀነሰ የታክስ ምጣኔ ህዳግ አሰራር በረቂቁ በአስተያየት ተሰጥቶ ቢካተት በሚል ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.6. የጠበቆችን የደረሰኝ መቁረጥ ግዴታን አስመልክቶ፣ ፍትህ ሚኒስትር እና የፌደራል ጠበቆች ማህበር ለጠበቆች ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ-ግብር ማዘጋጀት እና ሁሉም ጠበቆች በወጥነት እንዲተገብሩት ተገቢ ስራዎችን ማከናወን እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.7. በውል አማካኝነት ግብር የሚያስከፍሉ የግብር ሰብሳቢው አካላት ውል ተፈፀመ ማለት ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ግብር ሊጣልበት የሚችል ገቢ ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ አለባቸው። የጠበቆች ውል በአብዛኛው የረዥም ጊዜ ውል ነው፤ ሆኖም የገቢ ግብር አዋጅ አንቀፅ 32 ላይ የተቀመጠው የረዥም ጊዜ ውል አተገባበር ለጠበቆች ተግባራዊ መደረግ ስለማይችል በዝርዝር ማብራሪያ ወይም መመሪያ ወጥቶለት ሊተገበር እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

1.8. ከጥብቅና ስራ ውጪ ሌላ ተደራቢ የንግድ ስራ የሚሰሩ ጠበቆች ከደረሰኝ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ደረሰኞቹ ሁለት የተለያዩ ሆነው መታተም እንዳለባቸው እና ግብር ክሊራንሱም በተለያየ ሆኖ ለየዘርፉ ራሱን ችሎ ቢሰጣቸው ተገቢ እንደሚሆን ተመልክቷል። በተመሳሳይ ግብሩ በአንድ የግብር ከፋይ መለያ ስር የሚታወቅ ቢሆንም የጥብቅና ስራው ከንግድ ስራው ተለይቶ በሁለት የተለያየ መዝገብ ሊወሰን እንደሚችልና እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

2. የጥብቅና ድርጅቶችን በተመለከተ፡-

2.1. የጥብቅና ድርጅቶች እና የጠበቃ ድርጅት ሽሪኮች ግብር አከፋፈል በተመለከተ ግልፅ ህግ ሊወጣ ይገባል። የጥብቅና ድርጅቶች የሂሳብ አያያዝንም በተመለከተ ተቀናሽ መሆን የሚችሉ ወጪዎች የስራውን ልዩ ባህርይ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል። የእርጅና ቅናሽ፣የባለቤቶች የሂሳብ አካውንት ጋር በተያያዘ ግልጽ አሰራሮች መዘርጋት እንዳለባቸው ምክረ ሀሳብ ቀርቧል።

2.2. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማህበራት የገቢ ግብር አከፋፈልን በተመለከተ የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ እንዲሻሻል እና እነዚህ ማህበራት ከሌሎች የንግድ ድርጅቶች ልዩ የሚያረጋቸው ባህሪይ ግምት ውስጥ እንዲገባ ምክረ-ሀሳብ ቀርቧል።

2.3. የጥብቅና ድርጅቶች (የሽርክና ማህበሩ ሸሪኮች) እንደ ህብረት ስራ ማህበራት ሸሪኮች ከማህበሩ የሚያገኙትን ገቢ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን አሳውቀው ግብር የሚከፍሉበት አሰራር (Pass – Through Taxation/ Taxation of Tansparent Entities) እንዲኖር የሚያስችል የህግ ማሻሻያ ሊኖር ይገባል።

2.4. ጥብቅና ድርጅቶች ከገቢያቸው ላይ የድርጅት የገቢ ግብር ከከፈሉ በኋላ ለሸሪኮች ከሚከፈል የትርፍ ክፍፍል ላይ ተጨማሪ ግብር ሊከፍሉ አይገባም። ስለሆነም የሕግ ማዕቀፉ ሸሪኮች በግላቸው ተጨማሪ የትርፍ ክፍፍል ግብር የማይከፍሉበት አሰራር እንዲዘረጋ ምክረ-ሀሳብ ቀርቧል። ይህም ከተለያዩ ሀገራት ልምድ እና ከሽርክና ማህበራት ልዩ ባህሪ ጋር የሚጣጣም የግብር አከፋፈል ስርዓት ነው።

2.5. የጥብቅና ድርጅቶች ተቀናሽ ወጪዎች አያያዝን በተመለከተ የጥብቅና ሙያ ልዩ ባህርያት ከግምት ገብተው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ሊወጣለት የሚገባ ነው። በዚህም መመሪያ ለስራው ገቢውን ለማስገኘት የወጡ አጠቃላይ የጥብቅና ስራ ወጪዎች፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ካፒታል/እውቀት/ጉልበት፣ የአለምአቀፍ የጠበቃ ማህበር አባልነት ክፍያዎች ፣ የጉዞ ፣ የሆቴል ፣ የሸሪክ ጠበቃ የግል ወጪዎች ፣ ወ.ዘ.ተ. በሂሳብ መዝገብ ከግምት ገብተው የሚስተናገዱበት አግባብ በግልፅ ሊቀመጥ እንደሚገባ ምክረ-ሀሳብ ቀርቧል።

2.6. የጥብቅና ድርጅቶች የድርጅት ገቢ ግብር ከከፈሉ በኋላ አባላት (ሸሪኮች) የትርፍ ክፍፍል ግብር የማይከፍሉበት አሰራር ከተዘረጋ በኋላ አባላቱ የጥብቅና ፍቃዳቸውን ሲያሳድሱ በጥብቅና ድርጅቱ የግብር ክሊራንስ ሰርተፍኬት እንዲሆን ምክረ-ሀሳብ ቀርቧል።

2.7. በጥብቅና ድርጅት ውስጥ አባል (ሸሪክ) ሳይሆኑ በሙሉ ሰዓት ተቀጥረው የሚሰሩ ጠበቆችም በተመሳሳይ በድርጅታቸው አማካኝነት የቅጥር ገቢ ግብር መክፈላቸው ተረጋግጦ የጥብቅና ፍቃዳቸው ማደስ እንደሚችሉ ምክረ-ሀሳብ ቀርቧል።

ዋቢ ሀሳቾ እና ፅሁፎች

1. The Nigerian Constitution, 1999
2. Value Added Tax Act Cap VI LFN, 2004
3. The Personal income tax Act, Cap P8, LFN, 2004
4. Value Added tax Act, Cap 41VI, LFN, Nigeria (2004)
5. Customs and Excise management Act Cap C21, LFN, 2004
6. The Nigerian Companies Income Tax, 2004
7. Stamp duties Act Cap (2004)
8. Kenya revenue authority www.kra.go.ke
9. Taxation for companies & partnerships
10. Tax administration in Kenya፣ University of Nairobi፣ Prof Migai Akech (2015)
11. Rule of law, Brian Z. Tamanah, On the Rule of Law: History, Politics, Theory (Cambridge 2004)
12. Constitution of Kenya (2010)
13. Kenyan Revenue Authority Act (1995)
14. Kenyan law, The revised Income Tax Act (2021)
15. Value Added Tax Act No. 35 (2013), Kenya
16. The Tanzania revenue Authority WWW.tra.go.tz
17. Advocates act of Rules (Professional Conduct and Etiquette) Regulation no 118 (2018), Tanzania
18. Remuneration and Taxation of Costs, Statutory Instrument 267-4, Tanzania
19. Rwanda revenue authority- https://www.rra.gov.rw
20. Tax Ethics, Legal Ethics, and Real Ethics: A critique of ABA formal opinion, Theodor C. Falk (1986)
21. Revenue Department of Ireland, exemption and marginal relief

22. American Model Rules of Professional Conduct (2007) The American Bar Association ABA

አዋጆች፡-

23. የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ አመት፣ ቁጥር 8፣ ታህሳስ 16 2001ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
24. የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ አመት፣ ቁጥር 21፣ ታህሳስ 22 1995 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
25. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ 609/2001፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ አመት፣ ቁጥር 6፣ ታህሳስ 16 ቀን 2001ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
26. የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ አመት፣ ቁጥር 33፣ ሰኔ 27 ቀን 1994ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
27. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ 1243/2013፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ 2013 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
28. የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 104፣ ነሐሴ 02 ቀን 2008 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
29. የፌደራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249-2013፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 27ኛ ዓመት፣ ቁጥር 42፣ ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
30. የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ ዕትም፣ 22 ዓመት ቁጥር 103፣ ነሐሴ 14 2008 ዓ.ም. ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
31. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት፣ አዋጅ ቁ. 1/1987፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ነሐሴ 13 ቀን 1987ዓ.ም. ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

ደንቦች፡-

32. የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1993፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ አመት ቁጥር 19፣ ታህሳስ 22 ቀን 1993ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
33. የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 23ኛ ዓመት፣ ቁጥር 82፣ ነሐሴ 19 2009 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

34. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ 57/1992፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ መስከረም 13 ቀን1992 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

መመሪያዎች፡-

35. ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
36. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰብ ታክስ ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁ. 145-2011፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ 2011 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
37. ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
38. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 148/2011፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
39. የታክስ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
40. የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

መፅሃፍት፣ መጣጥፎች እና ጥናታዊ ፅሁፎች፡-

41. ሙሐመድ ዳውድ አልቃድር፣ በኢትዮጵያ ከሕግ አገልግሎት የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ፤ አዙሪት ጥያቄዎችና መውሰብስቦች፣ Bahir Dar University Journal of Law, Vol.8, No.2 (June 2018)።

ድህረ-ገፅ፡-

https://worldjusticeproject.org/rule-of-law-index/country/2022/Ethiopia/Civil%20Justice/ - ህዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም የተገኘ።

Interviews:

Interview with Tax Lawyer in Tanzania, Adv. BAHAME TOM NYANDUGA (interview held on Sept 09 2022 & October 02, 2022)

Interview with Attorney Joyce Oduah, Nigerian Senior Lawyer, (interview held on Sept 01 2022)

Interview with Kenyan Lawyer, Mbula E. Nzuki, principal attorney, (interview held on August, 16 2022)

Interview with American Lawyer, Abby Bekele, principal attorney in San Diego, USA (interview held on October, 16 2022)

Interview with Tax lawyer, Quenn Odua, (interview held on October, 01 2022) Nigeria

Interview with Addis Ababa Tax Beaurea Tax Collection and Decision Directorate Director, Mr. Wendimagegnehu Kassaye (interview held on Sept 01. 2022) Ethiopia

Interview with Addis Ababa Tax Beaurea Tax Audit Directoret Director, Mr. Getachewu Girma, (interview held on Sept 15. 2022) Ethiopia.